አማርኛ / أمهري

# مختصر كتاب
# إحياء الآثار

مُنيرة بنت عبدالعزيز المقوشي

# ترجمة كتاب

## مختصر


# إحياء الآثار

# “ቅርሶችን ህያው ማድረግ”

## (አጥሮ የቀረበ)

تاليف: منيرة بنت عبد العزيز المقوشي

ትርጉም / ዩሱፍ አሕመድ



# ማውጫ


መግቢያ 1

መቅድም 2

ነብያዊ ቅርሶች 5

1. የሐዲስ ዘገባዎች ቅርሶች 5
2. ከነብዩ ﷺ አካል ተለይተው የወጡ ቅርሶች 8
3. የነብዩ ﷺ ቅዱስ ቦታዎች ቅርሶች 20

የጠፉ ማህበረሰቦች አሻራ 27

1. የኑህ ﵇ ህዝቦች 30
2. የሁድ ﵇ ህዝቦች 32
3. የሷሊህ ﵇ ህዝቦች 34
4. የሉጥ ﵇ ህዝቦች 38
5. የሹዓይብ ﵇ ህዝቦች 39

የጣዖታውያን እና ቅድመ ኢስላም ቅርሶች 45

1. ፈርዖናዊ ቅርስ፡ 47
2. የፊይኒቅያ ቅርሶች 49
3. የባቢሎናውያን ቅርሶች 50
4. የጃሂልያ ጥንታዊ ቅርሶች 52

የመቃብር እና የ "መሻሒድ" ቅርሶች 60

ቅርሶችን ህያው ማድረግ የሚያስከትላቸው የዓቂዳ ተቃርኖዎች 82

የተወሱል (የመዳረስ) ክፍሎች እና ሸሪዓዊ ብይኑ 115

بسم الله الرحمن الرحيم

## መግቢያ

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባው ፤ (ለሁሉም ነገር አላህ) በቃ ፣ ምርጥ በሆነው ነብዩ ላይ ውዳሴና ሰላምታ ይስፈን ፤ በቤተሰቦቻቸው ፣ በባልደረቦቻቸው ላይ እስከ ፍርዱ ቀን የአላህ ውዳሴ ይስፈን ፤ በርካታ ሰላምታና ሰላም ያስፍንባቸው…

**ከዚህ በኋላ፡**

ቅርሶችና በእርሷ ላይ ትኩረት መስጠት ፣ እርሷንም ህያው ማድረግ በዚህ ዘመን ከአንገብጋቢ አጀንዳዎች መካከል አንዱ ሆኗል። ለዲን ያለው አስፈላጊነት ከሸሪዓ አኳያ ከእምነት ገጽታ ጋር ባለው የጠበቀ ትስስር ነው። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው በምድር ገጽ የመጀመሪያው ሽርክ ፣ ቅርሶችን ሕያው በማድረግ ምክንያት የተከሰተ መሆኑ ነው። እርሱም በኑህ ﵇ ህዝቦች የተከሰተው ነው።

ወደኋላ የመጣው ማህበረሰብ ከቀደምት ማህበረሰብ ውርስ አለው። በጠፉ ማህበረሰቦች ውስጥ የነበሩ ጣዖታት ወደጀዚረተል ዓረብ ተሸጋግረዋል። በትክክለኛ ሰነድ ከኢብን ዓባስ ﵄ በቀጥታ እንደመጣው።

ጥንታዊ ቅርሶችን ማነቃቃት በእምነት ላይ የሚያደርሰውን አደጋ በማስተዋል ፣ ለተከበሩ አንባቢያን ቀላል ይሆን ዘንድ ፣ **"ኢህያኡል አሳር"** (ቅርሶችን ህያው ማድረግ) በሚል ስያሜ ለማስትሬት ዲግሪ ያዘጋጀሁትን -ዓቂዳዊ ትምህርት- ለማሳጠር ወሰንኩ።

## መቅድም

በዚህች አጭር ኪታብ ውስጥ የሚደረገው ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ፣ **“አሳር”** የሚለው ቃል የተፈለገበትን ማብራሪያ መጠቆም እወዳለሁ።

- **ቋንቋዊ ትርጓሜው፡** ከሚታዩ ማንኛውም ነገሮች የቀረው ማለት ነው።
- ከሸሪዓ ምሁራኖች ዘንድ **“አሳር”** በሚከተለው መልኩ ታውቃለች። እርሷም፡ ከነብዩ ﷺ ሱና በቀጥታ (መርፋዕ ሆኖ) የተወራ ወይም ከሶሃባ በቀጥታ (መውቁፍ ሆኖ) የተወራ ወይም ከታብዕዮች ﷺ በቀጥታ (መቅጡዕ ሆኖ) የተወራ ማለት ነው።
- ከአርኪዮሎጅስቶች ወይም ከቅርስ ጥናት ተመራማሪዎች ዘንድ ደግሞ ፡ ያለፈው ትውልድ ለቀጣዮ ትውልድ ያስረከባቸው የሚዳሰሱም ይሁን የማይዳሰሱ ውርሶች ማለት ነው።

ጥናቱ አዲስ በመሆኑ የቅርስ የአርኪዮሎጅ ሳይንስ ባለሙያዎች ወጥ በሆነ አንድ አይነት ትርጓሜ ላይ አልተስማሙም። ያለፈው ክፍለ ዘመን መወለድ ተደርጎ ይቆጠራል። ነገር ግን ከእነርሱ ዘንድ በጣም ጉልህ የሆነው ትርጉም አርኪዮሎጅ (**Archaeology**) በመባል የሚጠራው የሚዳሰሱ ቁሳዊ ቅርሶችን ብቻ ያካተተው የቅርስ ጥናት እውቀት ነው።

ልክ አንትሮፖሎጅ (**Antropology**) ተብሎ የሚጠራው የሞራል ፣ የእውቀት ፣ የእምነት እና የባህል ሰብዓዊ ትሩፋቶችን አካቶ እንደያዘው ማለት ነው።

- በዚህ መሰረት **“ኢህያኡል አሳር”** (ቅርሶችን ህያው ማድረግ) ማለት እንደ ውህድ አጠራር፡ የሚዳሰስም ይሁን የሚታዮ ቅርሶች ያለፈው ትውልድ ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስረከብ እንክብካቤና ትኩረት ማድረጉ ነው። እነርሱን በመጠበቅ እና በማቆየት ወይም ከተደበቁ በኋላ ከነበሩበት ፈልፍሎ በማውጣት የበሰበሰውን በነበረው ዓይነት አዋቅሮ እንደገና መመለስ ማለት ነው።
- ይህ ትርጓሜ ሁለት ነገሮችን አቅፏል ፡

1. **የዘገባ ቅርሶችን ህያው ማድረግ፡** በእውቀት ፣ በመሸምደድ ፣ በማስተማር እና በመተዋወስ ይገለጻል።

2. **የሚታዮ ቅርሶችን ህያው ማድረግ፡** በርካታ ትርጉሞችን ያካትታል። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡

- በጉብኝትና ወደርሷ በመመላለስ ሕያው ማድረግ፣
- ከተደበቁ በኋላ ምድርን በመቆፈርና በመፈልፈል ሕያው ማድረግ ፣
- ለእርሷ እንክብካቤ በማድረግ ህያው ማድረግ ፣ ወደነበረበት በመመለስ ፣ በማስዋብ ፣ በማሳመር ፣ በእርሷ ላይ በመገንባት ፣ በማዋቀር ፣ ወደርሷ የሚወስዱ መዳረሻዎችን ማመቻቸት ፣ በጀሶ እና በመሳሰሉ ጌጣጌጦች ማስዋብ።

ጥንታዊ ቅርስ የሚለው ቋንቋ በተለያዩ አገላለጾች እና አይነቶች ይከፈላል። ከአይነቶች አኳያ የጥንት ቅርሶች የሚወሩ እና የሚታዩ ፤ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ፣ ቋሚ እና የውሸት ፤ ቀሪ እና የጠፋ ፣…. እና በሌሎች ዓይነቶች ይከፈላል።

**የጥንታዊ ቅርሶች ዋጋ ፣ ህያው የመሆኗ ምክንያት እና በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች አያያዝ እንደ ጥንታዊው ዓይነት ይለያያል። ከእርሷ መካከል ዋጋዋ የሚከተለው የሆነ አለ፡**

1. በቅርሱ ላይ ያለው የጊዜ ክምችት እና ልዩነት። ይህ የአርኪዎሎጅስት ጥናት ባለሙያዎች ትንታኔ ነው።
2. ቅርሱ ከተወሰነ ግለሰብ ጋር ትስስር መኖሩ ፤
3. ሸሪዓው ለእርሱ የሰጠው ደረጃ ፤

በዚህ አከፋፈል የተፈለገው ፣ የተሰጠው ዋጋ የተለያየ ቢሆንም ጥንታዊ ቅርሱ ከመሰረቱ በቅርስነት የሚቆይ እንጅ ፣ የቅርሱን ትክክለኛ መሆንና አለመሆኑን ውሳኔ የተላለፈበት ተደርጎ ግንዛቤ ሊወሰድ አይገባም።

ያለፈውን ላስተዋለ -በዚህ ቦታ የተፈለገው- ከሁሉም የእውቀት ባለቤቶች ዘንድ የጥንታዊ ቅርስ

ሙያዊ ትርጓሜዎች ከሁለት ትርጉሞች የዘለለ እንዳልሆነ ያገኘዋል። እነርሱም፡-

1. **የሐዲስ ዘገባዎች ቅርሶች፡** ከነብዩ በንግግር ያወሩት ወይም በተግባር የፈጸሙት ወይም አይተው ያጸደቁት ወይም ስነ-ምግባራቸውና ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ናቸው። ይህ ነው ሸሪዓዊው ትርጉሙ።
2. **የሚታዩና የሚዳሰሱ ቅርሶች፡** እነርሱም ቁሳዊም ይሁን ሞራላዊ የሰው ልጆች ቅርሶች ናቸው። ይህ ነው ሙያዊ ትርጉሙ።

**በሁለቱ ላይ ሸሪዓው ባስቀመጠው ብይን መሰረት ለወደፊት ማብራሪያችን ስለሁለቱ ክፍሎች ይሆናል። ንግግራችንን በሚከተሉት እንጀምራለን፡**

1. **ነብያዊ ቅርሶች እና አይነቶቿ**
2. **የጠፉ ህዝቦች ቅርሶች**
3. **የጣኦትና ቅድመ ኢስላም ቅርሶች**
4. **የመቃብሮችና የመሻሂዶች ቅርሶች**

## ነብያዊ ቅርሶች

**የሚከተሉትን ያካትታል፡-**

1. የሐዲስ ዘገባዎች ቅርሶች
2. ከነብዩ ﷺ አካል ተነጥለው የቀሩ ቅርሶች
3. የነብዩ ቅዱስ ቦታዎች ቅርሶች

### 1. የሐዲስ ዘገባዎች ቅርሶች

ከሙሐዲሶች ሐዲሳዊ ትንታኔ ዘንድ ፣ ነብያዊ የሐዲስ ዘገባ ቅርሶች ትርጓሜ ሲባል ከነብዩ ﷺ ሱና ጋር የትርጉም አንድነት አላቸው።

**በዚህም የተፈለገው፡** ነብዩ ﷺ በንግግር ያወሯቸው ወይም በተግባር የፈጸሟቸው ወይም ሲተገበር አይተው ያጸደቋቸው ወይም ስነ- ምግባራዊም ይሁን ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ማለት ነው።

ይህ ነብዩ ﷺ ትተዋቸው ከሄዱቸው ቅርሶች ሁሉ ትልቁ ነው። ልክ እንደሌሎች ቅርሶች አይደለም። ምክንያቱም አላህ ወደረሡል ﷺ ያወረደው ፣ እንድንከተለው ያዘዘው የሆነ ወህይ ነው።

ለነብያዊ የህዲስ ዘገባዎች ቅርሶች ማስረጃነትና እርሷን ህያው ማድረግ ግዴታ ለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

### 1. ረሡልን ﷺ እንድንታዘዝ ከአላህ ትዕዛዝ መውረዱ

ልዕልናው ከፍ ያለው ጌታችን የሚከተለውን ተናገረ፡-

﴿أَطِيعُواْ اللهَ وَالرَّسُولَ﴾

**"አላህንና መልእክተኛውን ታዘዙ።"** *(አልኢምራን፡ 32)*

### 2. ሐዲስን እንድንከተል ትዕዛዝ መውረዱ

እርሷም የነብዩ ﷺ ሱና ነች። ከሁሉ በላይ የሆነው ጌታችን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ﴾

**"መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራቸው"** *(አል'በቀራህ፡ 129)*

3. ነብዩ ﷺ በመጡበት መመሪያ መስራት እንዳለብን ትዕዛዝ መምጣቱ

ከሁሉም በላይ የሆነው ጌታችን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا﴾

"መልእክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።" (አል'ሐሽር፡ 7)

4. ባልተግባባን ጊዜ ወደቁርዓን እና ሱና መመለስ እንዳለብን ትዕዛዝ መምጣቱ

የረሡልን ﷺ ትዕዛዝ በሚቃረኑ አካላት ላይ ከባድ የሆነ ዛቻ ወርዷል።

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَإِن تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللهِ وَالرَّسُولِ إِن كُنتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللّهِ وَالْيَوْمِ الآخِرِ ذَلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلاً﴾

"በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትሆኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና መልእክተኛው መልሱት። ይህ የተሻለ መጨረሻው ያማረ ነው።" (አን'ኒሳእ፡ 59)

5. ረሡልን ﷺ መከተል ግዴታ መሆኑ መብራራቱ

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿لَقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ اللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُو اللَّهَ وَالْيَوْمَ الْآخِرَ وَذَكَرَ اللَّهَ كَثِيراً﴾

"ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው ፤ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አልለላችሁ።" (አል'አህዛብ፡ 21)

6. ከረሡል ﷺ የተገኙ ነብያዊ የሐዲስ ቅርሶችን ህያው ያደረገ ከአላህ ዘንድ የሚያገኘው ምንዳ መብራራቱ

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል ፡-

"من سن في الإسلام سنة حسنة فعمل بعده كتب له مثل أجر من عمل بها ، ولا ينقص من أجورهم شيء ، ومن سن في الإسلام سنة سيئة فعمل بها بعده كتب عليه مثل وزر

من عمل بها ، ولا ينقص من أوزارهم شيء"

"በኢስላም ውስጥ መልካም መንገድ የመሰረተ (ማለትም ሱናቸውን ህያው ያደረገ ወይም ሱናቸውን ለመተግበር የተሽቀዳደመ) ከእርሱ በኋላ ከተሰራ ፣ ከእርሱ (ከሰሪው) ምንዳ አንድም ሳይጎደል ፣ በእርሱ የሰራው ሰው አጅር ተመሳሳይ ለእርሱ ይጻፍለታል። በኢስላም ውስጥ መጥፎ መንገድ የመሰረተ ከእርሱ በኋላ ከተሰራ ፣ ከእርሱ ሐጢያት አንድም ሳይጎደል ፣ በእርሷ የሰራ ሰው ሐጢያት ተመሳሳይ ይጻፍበታል።" (ሙስሊም፡ 1017)

**ሸይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያ** ﷺ በመጅሙዕ አልፈታዋ (19/47) የሚከተለውን ተናግሯል፡-

*"... ኪታብን መከተል በእኛ ላይ አለብን ፤ ረሡልን መከተል በእኛ ላይ አለብን ፤ ከሁለቱ አንዱን መከተል ሌላውንም መከተል ነው። ረሡል ኪታብን አድርሰዋል ፣ ኪታቡ ደግሞ ረሡልን እንድንከተል አዘዘ ፤ ኪታቡ እና ረሡል ፍጹም አይለያዩም።"* (መጅሙዕ አል'ፈታዋ፡ 19/47)

ስለነብያዊ ሱና ፣ በእርሷ ዙሪያ የሰለፎችን ትኩረት እና የእርሷን ተቀባዮች ሁኔታ በተመለከተ ተጨማሪ ለማንበብ የፈለገ ከዋናው ኪታብ ከገጽ 45 እስከ 62 ድረስ መመልከት ይቻላል። በተጨማሪ በእርሷ ዙሪያ ስለተሰራጩ ብዥታዎችና ምላሾቻቸው በዚሁ መጽሐፍ ከገጽ 382 እስከ 404 ማንበብ ይቻላል።

**<u>ማጠቃለያ</u>**

ረሡል ﷺ ትተዋቸው ከሄዱት ቅርሶች ሁሉ ትልቁና የተላቀው በትክክለኛ ዘገባ የተወሩ ሐዲሳዊና ነብያዊ መረጃዎች ናቸው። ምክንያቱም አላህ ወደረሡል ﷺ ያወረደው ከአላህ የሆነ ወህይ ነው። ልክ እንደሌሎች ቅርሶች አይደሉም።

የረሡልን ﷺ ሱና ለመከተል ፣ የአላህን ሸሪዓ ተግባራዊ ለማድረግ ፤ በመማር ፣ በማስተማር በመሽምደድ ፣ በመተግበር ትክክለኛ የተወሩ ሐዲሳዊ ነብያዊ ቅርሶችን ህያው ማድረግ የግድ ነው።

## 2. ከነብዩ ﷺ አካል ተለይተው የወጡ ቅርሶች

**ከነብዩ ﷺ አካል ተለይተው የወጡ ቅርሶች በማለት የተፈለገው፡** ከነብዩ ﷺ አካል ጋር ተያይዘው ቆይተው ፣ ከዚያም ከአካላቸው የተለዩ ፣ ከሞቱም በኋላ የቀሩ ወይም በሰውነታቸው ላይ የተጣበቁትን ወይም የተጠቀሙበትን ነው።

የሸሪዓውን መረጃ ክትትል ስናደርግ ከነብዩ አካል ጋር ተያይዘው ቆይተው ከሞቱ በኋላ ለተወሰኑ ዘመናት የቀሩ ቅርሶች ሶስት አይነቶች ሆነው እናገኛቸዋለን፡

- **አንደኛው አይነት ፡** ከነብዩ አካል ተለይተው ሲያበቁ ፣ ከሞቱ በኋላም የቀሩ ናቸው። ለምሳሌ ፡ ጸጉራቸው እና የሰውነታቸው ላበት (ያረፉባቸው ልብሶች ወይም ሌሎች ቁሶች) ናቸው።

- **የነብዩ ﷺ ጸጉር፡** የረሡልን ጸጉሮች በተመለከተ ከሶሃቦችና ከታብዕዮች የተወሱ ወሬዎች መጠዋል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ስለርሷ የሚያወራ ሰነድ በመቋረጡ ፣ በሒጅራው አቆጣጠር ከሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ በታሪክ መጽሐፎች ውስጥ ስለርሷ የተወሳ አላገኘሁም።

መጨረሻ ላይ ስለ ነብዩ ﷺ ጸጉር መኖር በትክክል የተረጋገጠ ዘገባ የተገኘው በኢማም አህመድ ﷺ ነው። ከሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ቢኖር ኖሮ ከማን ወደማን ተሸጋግሮ ማን እንዳስቀመጠው ግልጽ ይሆን ነበር። ምክንያቱም ይህ ቅርስ ወደነብዩ መጠጋቱ አንገብጋቢና በእርሱም ኩራት በመሆኑ ነው። ይህም ለእነርሱ የተገባ ነው። ነገር ግን ስለርሷ ወይም ስለጸጉሮች ያለው ወሬ እና እንቅስቃሴ የሰነድ መቋረጥ በመከሰቱ ለመጥፋቷ አመላካች ነው። ፍጻሜዋ እና መመለሻዋ ያለፉት ክፍለ ዘመናት ናቸው። ወሏሁ አዕለም

- **የነብዩ ﷺ ላበት፡** የነብዩ የላበት ቅርስ ከኡሙ ሰለማ ﵂ ዘንድ መገኘቱ ወሬ መጧል። ዓነስ ብን ማሊክ ﵁ ሊሞት ሲል በሽቶ ማኖሪያ እቃ እንዲቀመጥ ተናዘዘ።

ነብዩ በመሞታቸው ምክንያት ላበታቸውም ተቋረጠ ፣ በመሞታቸው ተወገደ ፣ የላበቱ ምንጭ በመቋረጡ። ከኡሙ ሰለማ ﵂ ውጭ የነብዩን ላበት ጠብቆ ያስቀመጠ በትክክለኛ ዘገባ አላገኘሁም።

- **ሁለተኛው አይነት፡** ከአካላቸው ጋር የተጣበቀና የለበሱት ካፖርት ፣ ጥምጣም ፣ ቀለበትና

ጫማ ናቸው።

- **የነብዩ ካፓርት፡** የካፓርታቸው መወሳት ከአንዳንድ ሶሃቦችና ታብዕዮች ዘገባዎች መጠዋል። ሌላው ***"ቢዳያ ወንኒሃያ"*** ተብሎ በሚጠራው የሀፊዝ ብን ከሲር ኪታብ ላይ (6/379) ተወስቷል። የረሡልን ካፓርት አስመልክቶ መጨረሻውና ፍጻሜውን ከሚያወሳበት ቦታ የሚከተለውን ተናግሯል ፡

*"لا يدرى ما كان من أمرها بعد سقوط الدولة العباسية"*

*"ከአባስያ ስርዎ መንገስ መፍረስ በኋላ የእርሷ ጉዳይ አይታወቅም።"*

የእርሷ መመለሻና ፍጻሜን በተመለከተ ከዱላቸው ቅርስ ጋር ለወደፊት ይወሳል።

- **የነብዩ ﷺ ቀለበት፡** ከአቡበክር ሲዲቅ ከዚያም ከኡመር ብን አልኸጧብ ዘንድ እንደነበረች ተወስቷል። ከዚያም በመጨረሻ ከኡስማን ኢብን አፋን እጅ እንደነበረችና በአሪስ የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ወድቃ እንደጠፋች ዘገባዎች መጠዋል።

የእርሷ የመጨረሻ ፍጻሜ የአሪስ የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ወድቃ መጥፋቷ ነው። ከዚህ ክስተት በኋላ ቦታው **"ቢእሩል ኻተም"** (የቀለበት ጉድጓድ) ተብሎ ተጠርቷል። አንዳንድ ሶሃቦች የጉድጓዱን ውሃ በመቀነስ ቀለበቷን ለማግኘት ጥረት ቢያደርጉም ሊያገኙዋት አልቻሉም።

- **የነብዩ ﷺ ጫማ፡** ስለነብዩ ጫማ ከአንዳንድ ሶሃቦች እና ታብዕዮች ዘገባዎች መጠዋል። ስለእርሷ መጨረሻ ላይ ካወሱት ሰዎች መካከል የ**"ፈትሁል ሙተዓል"** ኪታብ ባለቤት ነው። (ገጽ፡ 254) ላይ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

*"አሁን ባለንበት ዘመን ስለነዚህ የተላቁ ጫማዎች ጉዳይ መረጃዎችን አላገኘሁም። ስለነርሱ ከጠየቅኋቸው አካላት ሁሉ አንድም ወሬ አላገኘሁም። ግምቴ በሂጅራው አቆጣጠር 803 ላይ በተይሙረለንክ በተቀሰቀሰው ጦርነት ደማስቆን ሲያፈራርሷት እንደተወገደች ነው… ይህ የሚጠቁመው በተይሙረለንክ ጦርነት ወቅት ሁለቱም ጫማዎቻቸው እንደጠፉ ነው። የት እንደሄዱ አይታወቅም።"*

➢ **ሶስተኛው ዓይነት፡** የተጠቀሙባቸው የእቃ ቅርሶች ናቸው፡ ዲርዕ (ከብረት የተሰራ የጦር

ልብስ) ፣ ዱላ ፣ ሰይፍ ፣ ጦር እና የኩል መኳያ ናቸው።

- **የነብዩ ﷺ ዲርዕ (የጦር መከላከያ ልብስ)፡** ከአንዳንድ ሶሃቦች እና ታብዕዮች ስለዲርዑ ዘገባ መጧል። ከዚያ በኋላ ግን ስለዲርዑ ምንም የሚታወቅ ወሬ የለም።
- **የነብዩ ﷺ ዱላ፡** ስለነብዩ ዱላ በዓባስዮች አመራር በኩል ወሬዎች መጠዋል። በሀውላኩ አማካኝነት የአባስዮች ስርወ መንግስት ሲፈራርስ አድራሻዋ ያኔ ሊጠፋ ችሏል። ሀውላኩ ካፓርቱን ፣ ዱላውን በማቃጠልና አመዳቸውን በዱጅላ ወንዝ በትኖታል።

**ከመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመን በኋላ ስለሰይፉ ፣ ጦሩ ፣ የመኳያ እቃው ፣ የጥምጣሙ ፣ የዱላው ፣ የዲርዖች እና የሌሎችንም ቅርሶች በተመለከተ በታሪክ መጽሐፍቶች የሚያወሳ አላገኘሁም።**

ይህ የሚጠቁመው -ወሏሁ አዕለም- በቀደምት የታሪክ መጽሐፎች ሰነዱ እና ወሬው በመቋረጡ ከምድረ ገጽ መሰወሯ እና መጥፋቷን ነው። ብትገኝ ኖሮ ቅርስነቷ ግልጽ ይሆን ነበር። መረጃው የደረሳቸውም ሰዎች ግልጽ ያደርጉት ነበር።

በጣም የሚያስገርመው ከዚያ በፊት ሰነዱ ከመቋረጡ ጋር- የነብዩ ዲርዕ ፣ ሰይፋቸው ፣ ጦራቸው ፣ መኳያቸው እና ከፊል ሌሎችም ልዩ የሆኑ ቅርሶቻቸው እንደሚገኙ ወደኋላ ከተዘጋጁ የታሪክ መጽሀፎች ባለቤቶች ተወስቷል። ይህ የሚጠቁመው መረጋገጡ ትክክል እንዳልሆነ ነው። ትክክለኛ እና ደካማ መረጃዎች ተደባልቀው ስለሚገኙበት በታሪክ መጽሐፎች ላይ መደገፍ አይቻልም።

**የ "አስሲየር ሀለብያ" ኪታብ ባለቤት አቡል ፈረጅ (1/5) የሚከተለውን ተናግሯል፡**

*"የታሪክ መጽሐፎች መውዱዕ (በረሡል ላይ ከተዋሸ ሐዲስ) በቀር ትክክለኛውንም ፣ በሽተኛውንም ፣ ደካማውንም ፣ በላጉንም ፣ ሙርሰሉንም ፣ ሙንቀጢኡንም ፣ ሙዕዶሉንም የሚሰበስብ መሆኑ የሚደበቅ አይደለም።"*

**ሙዝየም ውስጥ የሚገበኙ የተላቁ ነብያዊ ቅርሶች ምን ያክል እውነት ናቸው?**

የሚታዩ ነብያዊ ቅርሶችን በተመለከተ የመጨረሻ ፍጻሜያቸው እና መመለሻቸውን አስመልክቶ

በመጡ ዘገባዎች አማካኝነት በቅርብ ጥቆማ አድርጊያለሁ። የሚከተሉትን ጠቅለል አድርገን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡-

1. **ነብዩ ﷺ በመሞታቸው ቅርሶቹ የተቋረጡና የተወገዱ፡** እጅ ፣ ላበት ፣ ምራቅ ፣ ዱላ እና የውዱእ ትራፊ ናቸው።
2. **በመቃብራቸው ተቀብረው የቀሩ ቅርሶች፡** አንድ ሶሃባ እንዲከፈንባት የተናዘዘበት ካፖርት ፣ ዱላ እና ጸጉር ናቸው።
3. **የተቃጠሉ ቅርሶች፡** ሀውላኮ ያቃጠለው የአይላ ካፖርት እና ዱላ ናቸው።
4. **የጠፉና ያልተገኙ ቅርሶች** ፣ የበኒ ኡመያ ስልጣን ከፈራረሰ በኋላ የጠፉ የከዕቢያ ካፖርት ፣ ጸጉር ፣ ሁለቱ ጫማዎች ፣ ዲርዕ እና ቀለበት ናቸው።
5. **ተዛማጅነቷ ትክክል ያልሆኑ ቅርሶች፡** ጦር ፣ ዱላ ፣ ጥምጣም እና ጫማ ናቸው።

ከዚህ በፊት ባሳለፍነው መሰረት የእነዚህ ከፊል የጥንት ቅርሶች ለተወሰኑ ዘመናት ኖረው ፍጻሜ ጊዜቸው በማስረጃ መረጋገጡ እርሷ ከዚያ ዘመን በኋላ እንደጠፉች ፣ እንደተወገደች ፣ እንዳልዘወተረች ግልጽ ይሆንልሀል ማለት ነው። ከነብዩ ﷺ ቅርሶች መካከል አንድ እንኳ መገኘቱን የሚጠቁም ትክክለኛ ማስረጃ እና አስረጅ አልተገኘም። ይሁን እንጅ በጣም የሚያስገርመው ከፊሉ ቅርስ በኤግዚቪሽንና በሚጎበኙ የተለያዩ ቦታዎች እንዳለ የሚሞግቱ አካላት መኖራቸው ነው።

በአንዳንድ ኤግዚቢሽን ላይ የሚቀርቡ አንዳንድ ቅርሶች ትክክለኛነታቸው ምን ያክል ነው? የሚለው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። በተባረኩ አደራ ጥበቃዎች በአንዳንድ አገሮች የሚታወቁት የሚከተሉት ናቸው ፡

የነብዩ ጥርሶች ! ነብያዊ ሁለት ጫማዎች ፣ "ኪረቀቱ ሰዓዳህ" (የነብዩ እና የሶሃቦቻቸውን እቃዎችን ያቀፈ ሳጥን) ፣ ነብያዊ ምንጣፍ ፣ ከነብዩ ሰይፎች መካከል የአንዱ ሰይፍ እጀታ ፣ የነብዩ ቀስት ፣ የነብዩ ባንዲራ እና የሌሎችም ነብያቶች ቅርሶች -በእነርሱ እና በነብያችን ላይ

በላጭ የሆነ ሶላትና ሰላምታ ይስፈን - እንዲሁም የአንዳንድ ሶሃቦች ቅርሶች ናቸው።

ከእነዚህ ቅርሶች መካከል በዚህ ባለንበት 15 ኛው ክፍለ ዘመን እንኳ! የነብዩ ትጥበት ትራፊ ውሃ ወይም ቅሪት ውሃ አልለ መባሉ አስገራሚው ጉዳይ ነው።

በእርግጥ ኡሙ ሰለማ የነብዩን ላበት በጠርሙስ ጠብቃ እንዳስቀመጠች ትክክለኛ ዘገባ መጧል። ነገር ግን ነብዩ ከሞቱ በኋላ አንድ እንኳ ሶሃባ የውዱእ ትራፊያቸውን ጠብቆ እንዳኖረ የሚገልጽ በሀዲስ ትክክለኛ ዘገባ አልተገኘም።

ከነብዩ ﷺ ሞት በኋላ የውዱእ ትራፊያቸው ቀርቷል የሚለውን ትክክል ነው ብለን ብንቀበል እንኳ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ በፍጹም አይችልም። ፈሳሽ የሆኑ ነገሮች ባህሪያቸው ለመድረቅ ፣ ለመትነን ፣ ለመፍሰስ የተጋለጡ ናቸው። እንዲሁም እርሷን የወረሷት አካላቶች በተከታታይ ሲጠቀሙበት የማለቅ እድሉ ከፍተኛ ነው። በተለይም ከረሡል ﷺ አንዳች ቅርስ የወረሰ አካል ለራሱ ይጓጓል እንጅ ሌሎችን ከነፍሱ አያበልጥም።

እንዲሁም የረሡል ﷺ ሁለቱ ጫማዎች ጥንታዊ ቅርስ በሚል በአንዳንድ ኤግዚቢሽን ያቀርቡታል። በተይሙረለንክ ጦርነት ወቅት መጥፋታቸው የተወሳ ሲሆን ፣ ከዚያ በኋላ ግን ስለነርሱ -ስለሁለቱ ጫማዎች- ተወስቶ አያውቁም።

ቆዳዎች የመቆየት ጊዜያቸው የተወሰነ ጊዜ ነው። አህመድ ተይሙር የተባለው የታሪክ ምሁር **"አልአሳሩ ነበውያ"** በተባለው መጽሐፍ (ገጽ፡ 126) ላይ ቆዳዎችን በተለያዩ መርዞች በመዘፍዘፍ ከሚታወቁ ባለሙያዎች ነቅሎ የነብዩ ﷺ ናቸው የተባሉት ሁለት ጫማዎችን በተመለከተ የሚከተለውን አስተላልፏል፡

*"እነዚህ ጫማዎች በተለዩ መርዞች ሳይዘፈዘፈ የተዘጋጁ ከሆነ ብል በቀላሉ ይበላቸዋል። ከተዘፈዘፉ እና ጸጉር የሌላቸው የስብትይ ቆዳ ከሆኑ ደግሞ ፤ ይደርቃሉ ፣ ይቆራረጣሉ። እንዲሁም የኢናን ፈረንጆች ቆዳ ከሆነ በተመሳሳይ ይደርቃሉ ፣ ይቆራረጣሉ። እነዚህ ሁለት ጫማዎች እስካሁን ለመገኘታቸው አንድም ዘገባ የለም። በዚህ ጉዳይ አንዳች ሙግት የተሟገተ ፣ የእርሱን ሙግት በተለምዶ ማንም የሚቀበለው አይደለም።"*

ቅርሶቹ ለተወሰነ ጊዜ መቆየታቸው ንግግሩ አንድና አንድ ነው፡፡ እርሱም ወደሶሃቦች ፣ ታብዒዮች ፣ ከእነርሱም በኋላ ወደመጡ ኹለፋዎችና ታላላቆች የደረሱትን ጥንታዊ ቅርሶች ጠብቀዋል ፣ ለተወሰኑ ዘመናት ትኩረት አድርገውባቸዋል። ነገር ግን በሙስሊሞች ላይ ፈተናዎች ፣ የተለያዩ ሙከራዎች ሲፈራረቅ ለጥፋት ተዳርገዋል ፣ ስለርሷ ከትውልድ ወደትውልድ መተላለፊ ሰነድ ተቋርጧል። ካለፉ ዘመናቶች ወሬዋ ሊመጡ አልቻለም። ምናልባት ለአድራሻዎቿ መጥፋት ፣ ለምልክቶቿ መሰወር ምክንያቱ ይህ ሊሆን ይችላል።

የረሡል ﷺ ቅርሶች እስካሁን ድረስ አለ ብለው የሚከራከሩ ሰዎች ፣ ክርክራቸው ትክክል እንዳልሆነ እርግጠኛ የሆኑ የቅርስ ተመራማሪዎች ለማረጋገጥ ቀርበዋል። ይልቁንም ከማስረጃ እና ከመረጃ አኳያ ፎርጅድ ሊሆን ችሏል።

**በ 267 ሒጅራ አቆጣጠር የሞተው ሙሐዲስ እና ፈቂህ ሀማድ ብን ኢስሀቅ አልአዘድይ "ታሪከቱ ነብይ"** በተባለው ኪታቡ የሚታይም ይሁን የሚዳሰስ ነብዩ ﷺ ትተውት የሄዱት ቅርስ በጣም አናሳ እንደሆነ ጠቁሟል። ቡኻሪ በትክክለኛ ዘገባ የዘገበውን ሐዲሰ ማስረጃ አድርጓል።

**ዓምር ብን አልሀሪስ ﵁ የሚከተለውን ተናግሯል፡-**

"ما ترك رسول الله عند موته درهما ولا دينارا ولا عبدا ولا أمة ولا شيئا إلا بغلته البيضاء وسلاحه وأرضا جعلها صدقة"

"የአላህ መልእክተኛ በሚሞቱ ጊዜ ነጭ በቅሎ ፣ የጦር መሳሪያ ፣ እና ሰደቃ ያደረጉትን መሬት ብቻ አንጅ ፤ ዲርሀምም ፣ ዲናርም ፣ ወንድም ይሁን ሴት ባሪያ አንድም ነገር አልተውም።" *(ቡኻሪ፡ 2873)*

ይህ ረሡል ﷺ ትተውት የሄዱት የሚዳሰስ ቅርስ አነስተኛ ለመሆኑ የሚያጠናክር ትክክለኛ እና ግልጽ ማስረጃ ነው።

**በዘመናችን የሚዳሰስ እና የሚታይ ነብያዊ ቅርስ መገኘቱ ከመረጃ የተራቆተ ባዶ ሙግት እንደሆነ ከሁለት ነገሮች አንጻር ጠቅለል አድርገን ማቅረብ እንችላለን ፤**

**ከሸሪዓ አኳያ፡** ሸሪዓዊ ህግጋትን እና ተግባራዊ የሆኑ ህግና ደንቦችን ጨምሮ የሚያመጣ በሆነና

በተሟላ ሁኔታ ወሬዎች ተዘግበው እንደሚቀርቡት ወደነብዩ የተጠጋው ወሬ ምን ያክል ትክክለኛ ነው የሚለውን ለማረጋገጥ ተጨባጭና የሚታዩ ጥንታዊ ቅርሶችን ትክክለኛና ተያያዥ በሆኑ ሰነዶች ማጽደቅ የግድ ይላል። ከነብያችን የተወራው ሐዲስ ከትክክለኛ ታማኝ ሰነዱ የተያያዘ ካልሆነ በቀር ተቀባይነት እንደማይኖረው ሁሉ የሚታዩ እና የሚዳሰሱ ጥንታዊ ቅርሶችም እንደዚሁ ናቸው ! ይህ ጉዳይ ይህች ማህበረሰብ የተለየችበት ነው። ምክንያቱም እንሆ እርሷ፡ የሰነድ ኡመት በመሆኗ ነው።

**አብደሏ ብን ሙባረክ ﵀ የሚከተለውን ተናግሯል፡-**

أخرجه مسلم في مقدمة صحيحة "الإسناد من الدين ، ولولا الإسناد لقال من شاء ، ما شاء"

*"ሰነድ ከዲን ነው ፤ ሰነዶች ባይኖሩ ኖሮ የፈለገው ሰው የፈለገውን ይናገር ነበር።"* *(ሙስሊም በሶሂህ ኪታባቸው መግቢያ ላይ አውርተውታል)*

## ከአርኪዮሎጅስቶች (ከቅርስ ተመራማሪዎች) አኳያ

የጥንታዊ ቅርስ ባለሙያዎች ለአየር የተጋለጡና ከተገኙበት ጊዜ ጀምሮ በትክክለኛ ሳይንሳዊ መንገድ ያልተጠበቁ ኦርጋኒክ ቅርሶችን ግምት ውስጥ አያስገቡም ፣ የጥንት ዘመንን መለኪያ ለማወቅ ሳይንሳዊ እርምጃዎችም በእሱ ላይ አልተተገበረም።

ለአየር የተጋለጡ የኦርጋኒክ ቅርሶች እንደሚበከሉ የታወቀ ነው። እናም ትክክለኛውን እድሜ ማወቅ እና የመትረፍ ጊዜያቸውን በዘመናዊ ዘዴዎች ለመለካት ፈጽሞ የማይቻል ነው።

ከጥንት ቅርሶች ባለሙያዎች ዘንድ ፡ የሚለካው በሬዲዮአክቲቭ አይሶቶፖች ሲሆን የኦርጋኒክ አርኪኦሎጂ ናሙናዎችን ለመተንተን የሚያገለግለው ራዲዮአክቲቭ ካርቦን ሲሆን ይህም ኮዱ **C14** በመባል ይጠራል። ይህ ልኬት በጥናታዊ ቅርሶች ባለሙያዎች ዘንድ የወቅቱን ፍጹም አሃዛዊ ቀን ለመወሰን እንደ አንድ የቅርብ ጊዜ እና ምጥን ዘዴዎች ይቆጠራል። የቅርስ እድሜ እና ለውጤቶቹ ትክክለኛነት እና በእምነታቸው መሰረት ከእውነት ጋር ያላቸው ቅርበት እጅግ በጣም አስተማማኝ ዘዴ ነው።

በዚህ መሰረት ከነብዩ ጋር የተሳሰረው ቅርስ ከቅርስ ባለሙያዎች ዘንድ እንደቅርስ አይቆጠርም

ምክንያቱም ትክክለኛ በሆነ መንገድ አልተጠበቀምና። ይልቁንም በተቃራኒው ለአየር ክፍት በመሆኑ ፣ ሁሉም ሰው ሊነካው ፣ ሊስመው እና ከእርሱ በረከትን ሊፈልግበት የሚችል በመሆኑ ነው።

ይህ በሸሪዓዊ መንገድም ይሁን በዘመናዊ የሙከራ ሳይንስ ለእርሷ ማንኛውንም ዓይነት ማረጋገጫ ያላትን የሚያስተባብል ነው። በመቀጠልም ለተመራማሪው ሐሰትነቱን በእርግጠኛነት እና ወደ ነብዩ ﷺ የተጠጋው ወሬ ትክክለኛ አለመሆኑን ይጨምርለታል።

ከሙሐዲሶች ፣ ከሙህቂቆች ፣ ከአንዳንድ የታሪክ ባለሙያዎች እና የቅርስ ባለሙያዎች ንግግራቸውን መመልከት ለፈለገ ከዋናው ኪታብ ገጽ 83 ላይ ይመልከት።

**ከነብዩ ﷺ አካል የተነጠሉ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የነብዩ ቅርሶች ህያው የማድረጉ ብይን**

ያለፈውን መሰረት በማድረግ ከነብዩ ﷺ አካል የተለዩ ነብያዊ ቅርሶች ሁለት ባህሪዎች እንዳላቸው ግልጽ ሆኗል።

**የመጀመሪያው ባህሪ፡** በሶሃቦች ፣ በታብዕዮች እና ከእነርሱ በኋላ በእርግጠኛነት ወደነብዩ የተዛመዱ እና የተረጋገጡ እንዲሁም ወደነርሱ የደረሳቸው ቅርሶች ናቸው። እነዚህን እንክብካቤ ማድረግ እና መጠበቅ ይቻላል።

ከነብዩ አካል የተነጠሉ ቅርሶች ከሌሎች በተለየ ሁኔታ አካላዊ እና የሚዳሰሱ በረከቶችን አላህ በእነርሱ ላይ በማድረግ ለይቷቸዋል።

ሶሃቦች በላበታቸው ፣ በአክታቸው ፣ በውዱኣቸው በረከትን ሲፈልጉ ፣ እርሷንም ተስፋ አድርገው ሲጠብቁ ነብዩ ﷺ አይተው ዝም ማለታቸው ከእርሳቸው በተነጠለው እንዲሁም ከሞቱ በኋላ በቀረው የሰውነት ክፍሎቻቸው ይህን መስራት ሸሪዓዊ መሆኑ ማረጋገጫ ነው።

የነብዩን ቅርሶች ህያው ማድረግ ከሌሎች ሷሊሆች ጋር ማነጻጸር የማይገባ መሆኑን ማንቃት አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ከረሡል ﷺ በኋላ ሶሃቦች ከእነርሱ መካከል ደረጃቸው

በላጭ በሆኑ ሰዎች በረከትን ፍጹም አልፈለጉም። በመሆኑም ከእርሳቸው ውጭ በረሡል ﷺ ብቻ የተለየ መሆኑ ኢጅማዕ ወይም የሁሉም ስምምነት ሆነ ማለት ነው።

**በ"መጅሙዑ ረሳኢል" (1/252) ሀፊዝ ብን ረጀብ ﷼ ይህን ጉዳይ እንደሚከተለው አጠናክረውታል፡-**

*"የረሱል ሶሃቦች ከነብዩ ጋር በተመሳሳይ እንደሚሰሩት ፣ በቅርሶች ተበሩክ ማድረግን ከፊላቸው በከፊሉ (ሶሀቦች እርስ በርሳቸው) አይሰሩም ነበር። በደረጃ ከመብለጣቸውም ጋር ታቢዒዩችም ከሶሃቦች ጋር አልሰሩትም ነበር።"*

**ሁለተኛው ባህሪ፡** አሁን ባለንበት ዘመን ነብያዊ ቅርሶች ከሚባሉት ጋር ግንኙነት ያለው ነው። ይህ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አይቻልም። ይልቁንም መረጃዎች የሚያመላክቱት ወደነብዩ ማዛመዱ ውሸትና ቅጥፈት መሆኑን ነው። ስለዚህ እነዚህን ቅጥፈቶች እንኳን በእርሷ በረከት ማግኘት ይቅርና ፣ ወደነብዩ ማዛመድ ፣ ማደስ ፣ መጠበቅ ተገቢ አይደለም። በእያንዳንዱ ሙስሊም ህብረተሰብ በህይዎት ሲኖር ያለበት ግዴታ የነብዩን የንግግር ፣ የተግባር ፣ የሱና ቅርሶችን ጠብቆ መንከባከብና መያዝ ነው።

ረሱል ﷺ ከሚዳሰሱ ቅርሶች በረከትን ከማግኘት ወደሐዲስ ቅርሶች በረከትን ማግኘት ሶሃቦችን አሸጋግረዋቸዋል። ይህም ለእያንዳንዱ ሙስሊም ተገቢውና በላጩ ነው።

ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው ነብዩ ውዱእ ማድረጊያ እንዲያመጡላቸው ሶሃቦችን ጠሯቸው። ካመጡላቸው በኋላ በእርሱ ውዱእ አደረጉ። ሶሃቦች በውዱአቸው ተሽቀዳደሙ ፤ ከእርሱም ጠጡ ፤ ፊቶቻቸውን ፣ እራሶቻቸውን ፣ ደረቶቻቸውን አበሱ። የአላህ መልእክተኛም ﷺ ሶሃቦች ይህን ሲሰሩ በተመለከቱ ጊዜ የሚከተለውን ሐዲስ ተናገሩ፡-

"إن كنتم تحبون أن يحبكم الله ورسوله فحافظوا على ثلاث خصال: صدق الحديث، وأداء الأمانة، وحسن الجوار" حديث حسن

"አላህና ረሱል እንዲወዷችሁ የምትፈልጉ ከሆነ ፣ ሶስት ባህሪያትን ጠብቁ ፡ በንግግር እውነተኛነት ፣ የታመኑበትን በመፈጸም ፣ መልካም ጉርብትና።" *(ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል "አስሲልሲለቱ አስሶሂሀ፡ 2998)*

**ሻጢቢይ ﷺ "ኢዕቲሷም" በሚባለው ኪታቡ (1/485) ላይ በዚህ ሐዲስ ላይ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጧል፡**

*"ይህ ሐዲስ በሚዳስሱ የነብዩ ቅርሶች በረከት ከማግኘት ይልቅ ፣ የበለጠ እርግጠኛ እና አስፈላጊ በሆነው የተሰጡንን ተልእኮዎች ተግባራዊ ማድረግ በላጭ መሆኑን ይጠቁማል።"*

**አልዓላማ አልሙህዲስ ናሲሩ ዲን አልባኒ ﷺ "ፈታዋ አልኢማራ" (31፣76) በተባለው ኪታባቸው በዚህ ሐዲስ ላይ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጠዋል ፡**

*"ከተበላጭ ጉዳይ ወደበላጭ ብይን ማሸጋገራቸው በትችት ጊዜ የሚታይ ደግነት ነው። የአላህ መልእክተኛ ከዚህ ተግባራቸው ፍጹም አላገዷቸውም። ይልቁንም መንገዱን እጅግ በጣም ጥሩ በሆነ መልኩ አመቻቹላቸው። 'ይህን እንድታደርጉ ያደረጋችሁ ምንድን ነው?' አሏቸው። እነርሱም በዚህ ነገር እውነተኞች ናቸው። 'የአላህንና መልእክተኛውን ፍቅር" በማለት ተናገሩ። 'ይህ ለአላህ እና ለመልእክተኛው ውዴታችሁን አይጠቁምም። በእርሱ ላይ የሚጠቁማችሁ ረሡል ﷺ ከጌታው ይዞ ባመጣው መስራታችሁ ነው' አሏቸው"*

**በነብዩ ቅርስ በረከት የሚበቃ መሆኑን ማንቃት የግድ ነው። ነገር ግን ለዚህ በረከት መስፈርቶቸ አሉት፡**

1. **ከአላህ ዘንድ ተቀባነት ያለው ሸሪዓዊ እምነት ያስፈልጋል።** ሙስሊም ፣ እውነተኛ ካልሆነ በዚህ በረከት ሰበብ ማንኛውንም መልካም አያረጋግጥለትም።
2. **የተወሰኑ የነብዩን አሻራዎች ማግኘት፡** እንደሚታወቀው የረሡል ﷺ ቅርሶች ልብሳቸው ወይም ጸጉራቸው ወይም ቀለበታቸው ወይም ዱላቸው እና የመሳሰሉ ቅርሶቻቸው በእርግጠኛነት ጠፍተዋል። አንድ ሰው በእርግጠኛነት እነዚህን ቅርሶች አግኝቻለሁ ብሎ ማረጋገጥ አይችልም።

ነገሩ እንደዚህ ከሆነ ፣ አሁን ባለንበት ዘመን በእነዚህ ቅርሶች በረከትን መፈለግ እብለት ይሆናል ማለት ነው።

ካሳለፍነው ትምህርት ወደነብዩ ትስስር ያላቸውን ተጨባጭና የሚታዩ ቅርሶችን ለምሳሌ፡ ጸጉራቸው ፣ ከፖርታቸው ፣ ጫማቸው ፣ ጥምጣማቸው ፣ ጦራቸው ፣ ዱላቸው እና የመሳሰሉ ቅርሶቻቸውን በተመለከተ አንድ ሙስሊም ሊኖረው የሚገባውን ሸሪዓዊ አቋም በሚከተለው መልኩ ጨምቀን እናቀርበዋለን።

**አንደኛው፦** በትክክለኛ ሐዲስ እንደመጣው ነብዩ ﷺ ከሞቱ በኋላ ትተውት የሄዱት ቅርስ አነስተኛ መሆኑን ማመን። ነብዩ ﷺ ትተውት የሄዱት ጥቂት ቅርሶቻቸው ደግሞ ለበርካታ አደጋዎች የተጋለጡ መሆናቸውን ማወቅ ነው።

- **ቅርሷ ለጥፋትና ለመደፈን ትዳረጋለች፡** ምክንያቱም ነብያዊ አሻራዎችን በቁጥጥሩ ስር ካዋለውም ንፉግነት ያጠቃዋል ፤ ከነፍሱ ሌሎችን አያስበልጥም። በአብዛኛው ባለቤቷ እንድትጠፋ ያደርጋታል ወይም በእርሷ እንዲከፈንባት ይናዝዛል ወይም ከእርሱ ጋር ትቀበራለች።
- ኢስላማዊ ማህበረሰብ በከሀዲዎች በሚደርስበት የተለያዩ መከራዎች፡ ጦርነቶች ፣ አደጋዎች ፣ ፈተናዎች እና ችግሮች ምክንያት መሰወር ፣ መጥፋት እና ከምድረ ገጽ መወገድ ይከሰትባታል።

**ሁለተኛው፦** በዚህ ዘመን ማንኛውም ሙስሊም የነብዩ ﷺ የሚዳሰስና የሚታይ ቅርስ ይገኛል ብሎ የሚሞግትን ሰው መቀበል የለበትም - ምክንያቱም ቅርሱ ይገኛል የሚለው አባባል ከመረጃ እና ከአስረጅ የተራቆተ ሙግት በመሆኑ። ምክንያቱም ልክ በተሟላ ሁኔታ የንግግራቸውን ትክክለኛነት በሚያረጋግጥ እና በሚጠቁም ሁኔታ በሰነድ ተዛምዶ እንደሚወራው ሁሉ ይህ የሚዳሰስ እና የሚታይ ቅርስ መኖሩን የሚያረጋግጥ መረጃ ሊኖር የግድ ነው።

**ማጠቃለያ**

- በዚህ አሁን ባለንበት ዘመናችን ከረሡል ﷺ ከአካላቸው የተነጠለ ቅርስ አለ ብሎ የሚሞግት ፣ ሙግቱ ከመረጃ እና ከማስረጃ የተራቆተ ሙግት ነው። ውሸት ከሆኑ

- ቅርሶች ውስጥ ትመደባለች።
- ከነብዩ አካል ጋር በተገናኘም ይሁን በተነጠለ አሻራዎች ሸሪዓዊ የሆነው በረከት በዘመኑ የነበሩት ሶሃቦች የተለዩበት ነው። ከእነርሱ በኋላ የመጡትም ቢሆን ከነብዩ አሻራ ያገኙት ጥቂቶች ናቸው።

ወደኋላ የመጣው ማህበረሰብ ይህ አምልጧቸዋል። ነገር ግን ይህ አይነቱ ቢያመልጣቸውም ትክክለኛ የሆነውን የህዲስ ዘገባዎች ቅርሶችን ህያው በማድረግ ፣ በመመሪያው ቀጥ በማለት ሱናውን በመከተል ፣ ትዕዛዛቸውን ተፈጻሚ በማድረግ ፣ የከለከሉትን በመከልከል የሚገኘው በረከት አላመለጣቸውም።

## 3. የነብዩ ﷺ ቅዱስ ቦታዎች ቅርሶች

***"መቃማት"*** ሲባል በአረብኛ ቋንቋ የተፈለገው ወይም በአረቦች ቋንቋ እንደመጣው፡ ማንኛውም ሰው የቆመበት ወይም ለሆነ ጉዳይ የተቀመጠበት ቦታ ማለት ነው።

***"መቃማት"*** የሚለው ቃል በኡለሞች ትንታኔ የተፈለገው የሚከተለው ነው ፡

ነብዩ - ዓለይሂሶላቱ ወሰላም - አንድን ቦታ ድንገት ሳያስቡት መርገጣቸው ወይም በዚያ ቦታ ላይ መቆማቸው በሐዲስ መረጃ የመጣበት ማለት ነው።

***"መቃማትን"*** በተመለከተ ፡ ረሱል ድንገት ሳያስቡት የቆዩባቸው ወይም የረገጧቸው ቦታዎችን አስመልክቶ ከርሳቸው የተገኙ ምሳሌዎችን በማውሳት እናንተን ለማንቃት እወዳለሁ። ይህን ስል የእውቀት ባለቤቶች በመጽሐፋቸው እነዚህን ቦታዎች ለደረጃዋ ሳይሆን ወይም እርሷ የተለየችበትን ለማውሳት ሳይሆን ፣ ለዚያራ እና ለአምልኮት አላማ አድርገው የሚጓዙ አካላትን ሸሪዓዊ ብይን ለማብራራት በኪታቦቻቸው እንደሚያቀርቡት ፣ ከአንዳንድ ሰዎች በዚህ ስያሜ ከጠሯትና ወደርሷ ለመመላለስ ጉጉት ካላቸው ሰዎች አኳያ ለማውራት እንጅ በጎነቱን አምኖ ተቀብሎ ከመርካት ወይም ከመነሳሳትና ከመንከባከብ አኳያ አይደለም። ይህ ቃል በሰዎች መካከል ተሰራጭቶ ታዋቂ ሆኖ የቆየ ቃል ነው።

**ነብያዊ ቅዱስ የቅርስ ቦታዎችን አስመልክቶ ምሳሌዎች ከሁለት ሁኔታዎች የዘለሉ አይሆኑም፡**

1. **በቁርኣን ወይም በሐዲስ የተወሩ የተረጋገጡ ጥንታዊ ቦታዎች ፡** ከእነርሱ መካከል ፡

- **እስካሁን ድረስ የሚገኙ፡** ለምሳሌ የኡሁድ ፣ የሰውር ፣ የሂራእ ፣ የሩማት ተራራዎች ፣ መስጅደል ኸይፍ ፣ መስጅደል ሙዝደሊፋ እና መስጅደል ጁዑራና ናቸው።

**በአሁኑ ሰዓት የማይገኙ የጠፉ ቦታዎች፡** ለምሳሌ፡ (ኹጥባ የሚያደርጉበት) ሚንበር ፣ የዑትባ ብን ማሊክ አልአንሷሪ ቤት ፣ ህእ የተባለው የጉድጓድ ውሃ ፣ ቢእር አልኻተም በመባል የሚታወቀው "አሪስ" የተባለው የጉድጓድ ውሃ ፣ "በደ.ዓህ" የተባለው የጉድጓድ ውሃ ፣ ዳሩል አርቀም ብን አልአርቀም እና መስጅዱ ፣ የሙርሰላት ዋሻ እና መስጅዱ ናቸው።

2. **ወሬዋ የተቋረጡ ያልተረጋገጡ የቦታ ቅርሶች፡** ለተወሰነ ዘመን ምልክቶቿ የተሰወሩ ከዚያም ከጠፋችበት ጊዜ ጀምሮ ለረጅም ጊዜ ህያው የሆነች ነች። ማለትም ወደኋላ በመጣው ክፍለ ዘመን እንደገና የተመለሰች እና በአሁኑ ሰዓት ትኖራለች ብለው የሚሞግቱላት ነች።

**ለምሳሌ፡** ረሡል የተወለዱበት ቦታ ፣ መስጅድ አልበይዓ ፣ መሳጅድ ሰብዓህ ፣ መስጅዱል ኩዕ ወይም መውቂፍ ፤ "ገርስ" በመባል የሚታወቀው የጉድጓድ ውሃ ፣ መብረኩ ናቃህ (ግመሏ የተንበረከከችበት ቦታ) ፣ ግብጽ ውስጥ የነብዩ እንደሆነ የሚወራለት የእግራቸው ዱካ ፤ በቁድስ ፣ በቀስጦንጦንያ ፣ በጧዒፍ እና በሌሎች ከዚህም ከዚያም የሚያራግቡላቸው ቦታዎች ናቸው።

**እነዚህን ጥንታዊ ቅርሶች ለይቶ መናገሩ የተረጋገጠ አይደለም። ይልቁንም ማስወገዱ ፣ ማራቁ ፣ ቅጥፈቱን ማጋለጡ ግዴታ ከሆነው ታሪክን የማጭበርበር አኳያ ሊታይ ይገባል- ምክንያቱም እርሱ ቅጥፈትና ውሸት ነውና።**

**ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ነገሮች  አንዱ የሚከተለው ነው፡-** አሁን ጥንታዊ ቅርስ ተብለው በቀሩት ቦታዎች ወደርሱ መጓዝ ፣ በውስጧ ሶላት መስገድ ፣ በእርሷ መቃረብ ፣ ከእርሷ በረካ ለማግኘት መንካት በሸሪዓ አልተደነገገም። እርሷ ልክ እንደሌሎች መሰል ቦታዎች ነች። ከሌሎች የምትለይበት አንዳች ነገር የለም። **የዚህ ዝርዝር እንደሚከተለው ነው፡-**

1. **መጅዶች፡** እነርሱም በሁለት ይከፈላሉ፡

- **ብልጫነቷ በሸሪዓ የመጣ ፣ መወሳቷ የተረጋገጠ፡** እነርሱም አራቱ መስጊዶች ብቻ ናቸው። አልመስጅዱል ሀራም ፣ አልመስጅዱ አን'ነበውይ ፣ አልመስጅዱ አል'አቅሷ እና መስጅዱ ቁባእ ናቸው።
- **ደረጃዋ ተለይቶ በሸሪዓ ያልመጣ ፣ መወሳቷም ያለተረጋገጠ፡** እነርሱም ረሡል ﷺ ድንገት ሳያስቡት የሰገዱባቸው ቦታዎች ናቸው። እነዚህን ህያው ማድረግ ፣ በእርሷም ላይ መስጅዶችን መስራት ፣ በውስጧ ለዒባዳ መለየት በሸሪዓ አልተደነገገም።

የመስጅዶች የግንባታ አላማ ሰዎችን ለሶላት መሰብሰብ ፣ በውስጣቸው ዒባዳ ለመፈጸም ነው። የሸሪዓው አላማ በውስጧ መሰባሰባቸው ነው። ልክ እንደ ሰባቱ መስጊድ በአንድ ቦታ ተቀራራቢ መስጊዶች መገኘታቸው ይህን አላማ አያረጋግጥም። ይልቁንም ለሸሪዓው ተቃራኒ ለሆነው ሙስሊሞች መከፋፈል ቀስቃሽ ነው። ሰባቱ በውስጧ ሶላት መስገድ በረካ ለማግኘት እና ለዱዓ እንጅ ለመሰባሰብ አልተገነቡም። ይህ ደግሞ ግልጽ የሆነ ቢድዓ ነው።

2. **ተራሮች እና ዋሻዎች ፡**

በዘመናችን -የኡሁድ ተራራ ሲቀር- እስካሁን ያልቀሩ ምልክቶች ተደርገው ይቆጠራሉ። ለእነርሱ ምንም አይነት ደረጃ የላቸውም። የኡሁድ ተራራ ግን ደረጃው ተወስቷል። ይህ ከመሆኑ ጋር እርሱን በመጎብኘት ህያው ማድረግ በሸሪዓ የመጣ ማስረጃ የለውም። እነዚህን ቦታዎች ቅዱሳን አድርጎ መቁጠር አይፈቀድም። ከእርሷ ዘንድ አምልኮን አላማ አድርጎ ወደነርሱ መውጣትም እንዲሁ። ከእርሷ በረከትን መፈለግ እንዲሁም መተሻሸትም አይበቃም። የጅግራፊ ምልክት ብቻ እንጅ ከሐጅ ስርዓት ጋር ትስስርም የለውም።

3. ***መኖሪያዎች ፣ ቦታዎች እና መንገዶች***

ነብዩ ﷺ የተጓዙባቸው ቦታዎች ወይም ድንገት ለጥቂት ሰዓት የተቀመጡበት ቦታ ወይም የቆዩበትን ቦታ ልዩ ደረጃ መስጠት አይገባም። በሸሪዓም የተሰጠው በላጭነት የለውም። እርሷን በመዘየር እና በመጎብኘት የተቀመጠ ምንም ዓይነት ምንዳ የለም። ከሌሎች ቦታዎች የሚለይበት አንድም ነገር የለውም። እርሷን ማነቃቃትም አይፈቀድም። በሸሪዓዊ ዚያራም አላማ አድርጎ መንቀሳቀስም አይገባም። ልክ እንደሌሎች ቦታዎች እንጅ እርሷ የምትለይበት አንድም ነገር የለም።

4. ***የጉድጓድ ውሃዎችና ምንጮች***

አንዳንድ የጉድጓድ ውሃዎችን በተመለከተ በነብዩ ﷺ ትክክለኛ ሐዲሶች መጠዋል። በሐዲስ የጸደቁ ቢሆም በሸሪዓ የተሰጣቸው ልዩ ደረጃ ግን የለም። የጠፉ የጉድጓድ ውሃ ቅርሶችን ለማነቃቃት ሙከራ ቢደረግም ከእርሱ ውሃ ለመጠጣት መፈለጉ ደረጃ የለውም ምክንያቱም

ከሌሎች የጉድጓድ ውሃዎች የሚለይበት አንዳችም ነገር የለምና፡፡

ነብዩ ﷺ ሳያስቡት ድንገት ለተወሰነ ዘመን ብቻ በዚያ ቦታ ስላለፉ ብቻ ቦታዎችን በቅርስነት ትኩረት ከሚያደርጉ አንዳንድ አካላት ነብያዊ በማለት ስያሜ መስጠታቸው መጧል፡፡ መስጊድነቱን ፈልገው ሳይሆን ረሡል ﷺ ከዚያ ቦታ ስለሰገዱበት በሚል መስጊዶችን ይገነባሉ፡፡ መስጊድ አን' ነበውይ በማለት ይጠሩታል፡፡ በዚያ መስጊድ ውስጥ ሶላት መስገድ ልዩ ደረጃ አለው ብለውም ያምናሉ፡፡ አንዳንድ የጉድጓድ ውሃዎችን ነብዩ ውሃ አውጥተው ስለጠጡ ወይም በእርሱ ውዱእ ስላደረጉ ወይም በእርሷ ላይ ቁጭ ስላሉ ብቻ ነብያዊ በማለት ሰይመዋል፡፡ ሌሎችንም ቦታዎች እንዲሁ፡፡ ይህ ሁሉ ትክክል ያልሆነ ፣ ከቀደምት ሰለፎች ያልመጣ አባባል ነው፡፡

ነብዩ ﷺ አላማ አድርገው የሚንቀሳቀሱባቸው ቅዱሳን ቦታዎች ህያው ማድረግ ፣ የነብዩን የህይዎት ታሪክ በትምህርት ቤት እንዲሰጥ ማድረግ ፣ መማር ፣ በእነርሱ ላይ ሸሪዓዊ ህግጋትን መሰረት ለማድረግ የተከሰቱ ክስተቶችን ለማጥናት እርሷን ማነቃቃት በሸሪዓ ተፈላጊ ነው፡፡

**በዚህ ምክንያት ረሡል ﷺ ትኩረት ያደረጉባቸውን ቦታዎች እና ትኩረት ያላደረቡባቸውን ቦታዎች ለይቶ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡**

**ከሶላትም ይሁን ከዱዓ ለአምልኮ ፣ ለመቃረቢያ አላማ አድርገው ነብዩ ﷺ የተንቀሳቀሱባቸውን ቦታዎች ማወቅ ዑለሞች የነብዩን ﷺ የህይዎት ታሪክ ለማጥናት ኪታብ ያዘጋጁበት ሂደታቸው ነው ፣ ህዲሶችንም የሰበሰቡበት እና የጻፉበትም መንገድ ነው፡፡ ከሶሃባ የተወረሱ እውቀቶችን በህግና ስርዓት የያዙበትም ነው፡፡ በእነዚያ ቦታዎች ላይ የሸሪዓ ህግጋቶችንም የሚገነቡበት ነው፡፡**

**ለዚህ ምሳሌ፥** የሀረም ድንበሮች ፣ ከእርሱ ጋር በተያያዘ በክልሉ ውስጥ መስገድ የሚያስገኘው ምንዳ ፣ የ"በደዓ" የጉድጓድ ውሃ እና ከውሃው ንጹህነት ጋር ያለው ትስስር ፤ የሐጅ መሻዒሮች ድንበሮች ፡ ሚና ፣ አረፋ እና ሙዝደሊፋ ናቸው፡፡

**ረሡል ﷺ ድንገት ያለፉባቸው ፣ የተቀመጡባቸው ፣ የሰገዱበት ቅዱሳን ቦታዎችን ህያው ማድረግ**

**ሸሪዓዊ ብይን፡**

**ከተፈላጊነቱ አኳያ ዝርዝሮች ይኖሩታል ፡**

1. ከሰዎች መካከል እርሷን ለመመልከት ፣ ለመጎብኘት ፣ ለመዝናናት የሚወጡ አሉ፡
2. ከሰዎች መካከል እነዚህን ቦታዎች ለአምልኮ ፣ መቃረብን እና በረከት ለማግኘት አላማ አድርገው የሚወጡ አሉ፡

ሁለተኛውን በተመለከተ የወጡበት ምክንያት አምልኮን ለመጠባበቅ ፣ ወደአላህ መቃረብንም አላማ በማድረግ በመሆኑ በሸሪዓ አልተደነገገም።

ለመጀመሪያ ጊዜ የነብዩን ቅዱሳን ቦታዎች ከእርሷ ዘንድ አምልኮን እና አሻራዋን የመጠባበቅና የመከታተል ቢድዓን የተጋፈጠው ኸሊፈቱ ራሽዲን ኡመር ኢብን አልኸጧብ ነው። ከእርሱ በኋላም እነዚህን ቦታዎች መጎብኘቷን የሚጠሉ ፣ ከቦታዎች ዘንድ አምልኮትን የሚጠባበቁ አካላትን በየዘመኑ የሚከለክሉ ከሰለፍ አዒማዎች በተከታታይ ተሹመዋል።

**ክልክልነቱ ለሀራም እንደሆነ ያረጋገጡ የታወቁ አኢማዎችን ንግግር መለስ ብሎ ለመመልከት የዚህን ኪታብ ዋና እትም (ገጽ 105-110) መመልከት ይቻላል።**

ነብያዊ ቅዱስ ቦታዎችን ሆን ብለው ለአምልኮ ሳይሆን ድንገት ለመመልከት ፣ ለመጎብኘት እና ለመዝናናት ከሆነ -ወሏሁ አዕለም- አመዛኝ በሆነው አመለካከት አደገኛ ከሆኑ ነገሮች ከመውደቅ በሚጠብቅ መስፈርቶች እና ህጎች መሰረት የሚበቃ መሆኑ ነው።

ዲናዊ ሳትሆን ዱንያዊ ጉብኝት በመሆኗ። ምክንያቱም የአምልኮ ካልሆነ መሰረቱ መፈቀዱ ነው። በተጨማሪ እርሷን ለመጎብኘት የሚከለከል መረጃ የለም። እርሷን ማነቃቃትም እንዲሁ መረጃም የለም።

እነዚህ ቦታዎች ከነብዩ ﷺ ጋር ምንም አይነት ትስስር የላቸውም። አንድ የሚጎበኝ ሰው ለቦታው ደረጃ እንዳለው ሳይገነዘብ ፣ እንደገና ይህ ቦታ ደረጃ አለው ወደሚል እምነት አላማውን ሊያዞር ይችላል። ይህ ሁሉ ያለምንም ጥርጥር የሸይጧን ማጥመም ነው።

ይህ ጉብኝት ይበቃል በሚለው ንግግር በሚጎበኘው እና በሚመላለሰው ሰው ላይ ግዴታ የሆኑ የተወሰኑ ህጎችና መስፈርቶች የተገደበ ነው። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡

1. ወደርሷ ለሰፈር የሚሆነውን ጓዝ ጭኖ ሊጓዝ አይገባም፤
2. ዒድ ተደርጎ ሊያዝ አይገባም ፤ በቀጣይነት መልኩ መመላለስን ማብዛት የለበትም ፣ ተደጋጋሚ በሆኑ ወቅቶች ደንበኛ አድርጎ ሊይዘው አይገባም፤
3. መስጅዶችን እና ነብዩ ድንገት የሰገዱባቸውን ቦታዎች ለመጎብኘት የሚል አላማ ሊኖረው አይገባም፤
4. ጉብኝቱ በዚያ ቦታ ከተደረገው ጦርነት እና ክስተት ወቅት ጋር መግጠም የለበትም። ምክንያቱም ይህን ተከትሎ በዘመንም ይሁን በቦታ ኢድ አድርጎ ለመያዝ መንገድ ይከፍታል።
5. የጎብኘው ልቦና ከቀርሱ ጋር ምንም አይነት ትስስር ላይኖረው ፤ የቦታውን ታላቅነትም ላይገነዘብ ነው።
6. በዚያ ቦታ ላይ የነብዩ አሻራ ይገኛል ብሎ ላያምን ነው።
7. ቦታው ከተለያዩ ፈተናዎች ሰላም ሊሆን ነው። የሀራምና የሽርክ መገለጫዎች በዚያ ቦታ ላይ ላይኖሩ ወይም ጉብኝቱ የቢድዓ ሰዎች በሚጎበኙበት ቀን ላይሆን ነው። በጉብኝቱ የቢድዓ ሰዎችን ሊጋራ አይገባም። ምክንያቱም ምናልባት ሊጎበኝ ሲሄድ እነርሱን ለመምከር ካልሆነ በቀር ፣ እርሱ ከእነርሱ ጋር እንደሆነ ፣ የእነርሱን ቁጥር እንዳባዛ ይገምታሉ።

**ሸይኽ ኗሊህ ፈውዛን ﵀ "አትተዕሊቁል ቀዊም ዓላ ኪታቢ ኢቅቲዷኡ ሲራጦል ሙስተቂም" በተባለው ኪታባቸው** (4/1630) **ለማስተንተን እና ለመመከር አላማ አድርጎ የነብዩን ﷺ ቅዱስ ቦታዎች መጎብኘትን በተመለከተ የሚከተለውን ተናግረዋል፤**

*"በእርሷ በረካ አገኛለሁ የሚል ሳይሆን ወይም ይጎዳል ይጠቅማል የሚል እምነት ሳኖረው ፣ ለማስተንተን እና ለመምከር ብቻ እርሷን መመልከት ከሆነ እርሱ የሚያስኬድ ነው። ነገር ግን ይህ ሲባል በተወሰነ ወቅት ቋሚ ደንበኛ ሳይሆን ፣ ይጠቅማል ይጎዳል የሚል እምነት ሳይኖረው መሆን አለበት - ምክንያቱም በመቀጠል ቅዱስ ቦታ ትሆናለች። ለእርሷ ዘበኛ ይደረግላታል ፣*

*የተለያዩ መገለጫዎች ይደረግላታል ፣ ይህ ከሆነ አይሆንም። ምክንያቱም ይህ እርሷን ወደማላቅ ፣ ትጠቅማለች ትጎዳለች ወደማለት ያደርሳል። ከዚህ ቦታ ላይ ያለው ጥንታዊ ቅርስ የቀረው ብቻ በዚያው ባህሪው ላይ ሊተው ይገባል። ለተበሩክ ፣ ከባለቤቶች ጥቅምን ፈልጎ ወይም በእነርሱ ለመማጸን ካልሆነ ለመምከር እና ለማስተንተን ብቻ መመልከት ከሆነ ይበቃል።"*

አንድ ሙስሊም እርሷን አላማ ባያደርግና እርሷን ፈልጎ ባይንቀሳቀስ የተሻለ ነው።። ይልቁንም (ከተመለከተ) እነዚያ ቅርሶች እግረ መንገዱን ቢሆኑ የተሻለ ነው።

**ሸይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያ ﷺ "ኢቅቲዷኡ ሲራጦል ሙስተቂም" በሚባለው ኪታቡ (1/268) የተናገረው ምን ምርጥ ንግግር አደረገው!**

*"ነብያቶችን ፣ እውነተኞችን ፣ ሰማዕታትን ፣ ጻድቃንን በመኖሪያ ቤታቸው ከመከታተልና አሻራቸውን ከማየት ይልቅ በተግባራቸው መከተላቸው የበለጠ ጠቃሚና ተገቢ መሆንን አታይምን?"*

**ማጠቃለያ**

- ነብዩን በማላቅ ፣ በመውደድ ፣ በመከተል ፣ ሱናቸውን ህያው በማድረግ ታዘናል። አሻራቸውን በማላቅ ፣ ተያያዥነት ያላቸውን የቆዩባቸውን ቅዱሳን የሚባሉ ቦታዎች ሆን ብለው ሳይሆን ድንገት ያረፉባቸው ፣ በሸሪዓ ከሌሎች ልዩ በመሆናቸው መረጃ ያልመጣላቸውን ቦታዎችን በማላቅ አልታዘዝንም።
- ማንኛውም ሙስሊም ፣ በቅርጽም ይሁን በአላማ ትእዛዛቸውን ለመተግበር እና ረሱልን ለመከተል አላህ በደነገገው ህግ ብቻ መወሰን ይኖርበታል። በፍቅር እና በማላቅ ሽፋን አምልኮን ወሰን አይለፍ ፤ ከሸሪዓው መውጣት የለበትም።
- በሸሪዓ ከሌሎች መለየቱ ማስረጃ ያልመጣለትን እንዲሁ ረሡል ﷺ አላማ ሳያደርጉ ድንገት አለፋበት በሚባለው ነብያዊ ቅዱሳን ቦታዎች መቃረብ እና አምልኮን ማሰብ በሸሪዓ አልተደነገገም።

## የጠፉ ማህበረሰቦች አሻራ

ከአደም ጀምሮ እስከ ኑህ ድረስ ሰዎች ጥርት ባለው ተውሂድ ላይ አንድ ህዝቦች ነበሩ። በትክክለኛ ሐዲስ እንደመጣው አስር ክፍለ ዘመን ካለፈ በኋላ ሽርክ ገባ።

***“በአደም እና በኑህ መካከል አስር ክፍለ ዘመን ነበር”***

በዘገባው ውስጥ የሚከተለው ጭማሬ አለው፤

***“ሁሉም ሀቅ በሆነ ሸሪዓ ላይ ነበሩ፤ ሲወዛገቡ ፣ ነብያትና ሩሡሎችን ላከ ፣ መጽሐፉን አወረደ ፣ አንድ ኡመት (ማህበረሰብ) ሆኑ።”***

ያለምንም ማጋራት በብቸኝነት አላህ ብቻ እንዲመለክ ጥሪ ለማድረግ ፤ ከእርሱ ውጭ የሚገኙ አምልኮዎችን ሊከለክሉ አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርጎ አላህ ነብያትን ልኳል። አንድም ነብይ ወደህዝቦች የሚላክ የለም የሚከተለውን የሚል ቢሆን እንጅ፡-

﴿يَا قَوْمِ اعْبُدُواْ اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَهٍ غَيْرُهُ﴾

**“ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ለእናንተ ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም።”** (አል’ አዕራፍ፡ 59)

**“ተገዙ”** ማለት **“ብቸኛ አድርጉት”** ማለት ነው።

ያለፉ ህዝቦች ከነብያቶቻቸው ጋር የነበራቸው ሁኔታ ፣ ሩሡሎችን እና አማኞቻቸውን አላህ ከቅጣት ነጻ እንዳወጣቸው ፣ አስተባባዮችን እንዳጠፋ በተከበረው ቁርኣን መጧል።

ከህዝቦች መካከል ለነብያቶች ጥሪ መልካም ምላሽ በመስጠቷ ከቅጣት ነጻ የሆነች አለች። ስለ ዩኑስ ህዝቦች አላህ እንደተናገረው ፡

﴿فَلَوْلاَ كَانَتْ قَرْيَةٌ آمَنَتْ فَنَفَعَهَا إِيمَانُهَا إِلاَّ قَوْمَ يُونُسَ لَمَّا آمَنُواْ كَشَفْنَا عَنْهُمْ عَذَابَ الخِزْيِ فِي الْحَيَاةَ الدُّنْيَا وَمَتَّعْنَاهُمْ إِلَى حِينٍ﴾

**“ (ከዩኑስ በፊት ካለፉት ከተሞች) ያመነችና እምነቷ የጠቀማት ከተማ ለምን አልኖረችም? ግን የዩኑስ ሕዝቦች ባመኑ ጊዜ በቅርቢቱ ሕይዎት የውርደትን ቅጣት ከእነርሱ ላይ አነሳንላቸው። እስከ ጊዜም ድረስ አጣቀምናቸው።”** *(ዩኑስ፡ 98)*

**ከህዝቦች መከከል የነብያቷን ዳዕዋ በማስተባበሏ ፍጻሜዋ ሙሉ በሙሉ መጥፋት የሆነ አለ።**

**የጠፉ ህዝቦች አሻራ ሲባል የተፈለገው፡** ካለፉ ህዝቦች ከሚታዩ ቅሪት የቅርስ ምልክቶች ማለት ነው።

**እነዚህን ቅርሶች አስመልክቶ በሁለት አይነት መናገር ይቻላል፡-**

**አንደኛው፡** ግልጽ የሆነ አሻራ ነው። የዓድ ፣ የሰሙድ እና የመድየን ቤቶች

**ሌላኛው አይነት፡** የተቀበሩ ሐውልቶች ናቸው

የኑህ ﷺ መርከብ ቅርስ እንዲሁም የሉጥ ህዝቦች ቤቶች ከምድር በታች መሰመጥ እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

ከማህበረሰብ በምድር ላይ ለመጀመሪያው ጊዜ አላህ ያጠፋቸው የኑህ ﷺ ህዝቦች ናቸው። ከዚያም የሁድ ﷺ ህዝቦች የሆኑት አዶች ናቸው። ከዚያም የሷሊህ ህዝቦች የሆኑት ሰሙዶች ናቸው። ከዚያም የሉጥ ህዝቦች ናቸው። ከዚያም የሹዓይብ ህዝቦች የሆኑት መድየኖች ናቸው። እንደነርሱ ከእነርሱ በኋላም የተጠፉ ህዝቦች አሉ። እነዚህ በአጠቃላይ የተቀጡ ህዝቦች ናቸው። በጥፋት የተከታተሉ ፣ የጌታቸውን ትእዛዝ ያመጹ ፣ መልእክተኛቸውን ያስተባበሉ ናቸው።

የዱንያን ቅጣት አላህ አፋጠነባቸው። በአኼራ ያስቀመጠላቸው ደግሞ ከባድ እና ትልቅ ቅጣት ነው። ከመሞታቸው በፊት ካጋጠማቸው የከፋ ነው። ሰላምና ጤንነትን ከአላህ እንጠይቃለን።

ነብያቶች ከህዝቦቻቸው ጋር ያሳለፉት ህይዎት በተከበረው ቁርኣን እንዲሁም በትክክለኛ ሐዲሶች ውስጥ የተሞላ ሆኖ ታገኘዋለህ።

ቁርኣን -ለመገሰጽና ለማስተንተን እንዲሁም ለጥፋትና ለቅጣት ከዳረጋቸው ምክንያቶች ሰዎች እንዲርቁ ለማድረግ- ከመጀመሪያቸው እስከመጨረሻቸው የጠፉ ህዝቦችንና የመጨረሻው መውደቂያቸው ምን እንደነበረ ታሪኩን ያወራል።

ያለፉ ህዝቦች በቂያማ ቀን እሳት አልተዘጋጀላቸውም ፣ ለጥፋትም አልተዳረጉም በሽርካቸው ፣ ከተውሂድ በማመጻቸው ፣ በአላህም በመካዳቸው ፣ በረሡልም በማስተባበላቸው ፣ በወንጀል ድንበር በማለፋቸውና ሀጢያተኛ በመሆናቸው እንጅ።

**ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያ** ﷺ *"መጅሙዕ አል'ፈታዋ"* (16/249-250) የሚከተለውን ተናግሯል፡-

*"የሉጥ ﷺ ህዝቦች ከሽርክ በተጨማሪ ማንም አካል ያልቀደማቸውን ጸያፍ ተግባር ፈጽመዋል። የአድ ህዝቦች ከሽርካቸው ጋር አምባገነኖች ፣ ኩራተኞች ፣ ዱንያን በሐይልና በስፋት የያዙ ነበሩ።* ***"ከእኛ ይበልጥ በሀይል ብርቱ ማን ነው!" በማለት ተናግረዋል*** *(ፉሲለት፡ 15) ። የመድየን ህዝቦችም ከሽርክ በተጨማሪ በገንዘቦች በደል ፈጽመዋል....*

*የሁሉም ህዝቦች ቅጣት በወንጀላቸው እና በግፋቸው መጠን ነው። የዓድ ﷺ ህዝቦች ለእርሷ አንድም ነገር በማይቆምላት ብርቱ ነፋስ እንዲጠፉ ተደረገ። የሉጥ ህዝቦች ሌሎች ህዝቦች ባልተቀጡበት የተለያዩ ቅጣቶች ተቀጡ። ከሰማይ በወረዱ ዲንጋዮች ተደበደቡ ፣ አይናቸው እንዲጠፋ ተደረገ ፣ የታቹን ወደላይ የላይኛውን ወደታች በማድረግ በእነርሱ ላይ አገራቸው እንዲገለበጥ ተደረገ ፣ መሬት ተደርምሶ ወደታችኛው አዘቅጥ እንዲዋጡ ተደረገ....*

*የሹዓይብ ﷺ ህዝቦች በእሳት ተቀጡ። ይህች እሳት እነርሱንም በበደልና ወሰን በመተላለፍ የሰሩትንም ንብረት አቃጠለች።*

*ሰሙዶች በጩኸት እንዲጠፉ ተደረገ ወዲያው ሞቱ። ይህ ለእነዚህ ህዝቦች የደረሰባቸው ቅጣት ነው። ከሽርካቸው በተጨማሪ አላህ ለእነርሱ ተዓምር ያደረጋትን ግመል ወግተው ገደሉ። የአላህን*

*ክልክል የጣሰ ፣ ትእዛዙን እና ክልከላውን ያቃለለ ፣ ባሮቹን የወጋ እና ደማቸውን ያፈሰሰ ቅጣቱ ብርቱ ነው።*

*የቀደሞውንም ይሁን የአሁኑን የዓለም ሁኔታ በደንብ ላስተነተነ ፤ ቅጣት የሚደርስባቸው በወንጀል ምድርን ለማበላሸት የሚንቀሳቀሱ ፣ ደም ያላግባብ የሚያፈሱ ፣ ፊትና እንዲሰራጭ የሚያደርጉ ፣ የአላህን ክልክሎች እንደቀላል የሚመለከቱ መሆናቸውን የተገነዘበ ፣ በዚህ አለምም ይሁን በወዲያኛው አለም ከቅጣት ነጻ የሚሆኑት አማኞችና ጥንቅቆቹ ብቻ እንደሆነ ያውቃል።"*

- **አላህ ካጠፋቸው ህዝቦች**

**1. የኑህ ﷺ ህዝቦች**

የኑህ ህዝቦች በአላህ በማጋራታቸው ምክንያት አላህ ካጠፋቸው ማህበረሰቦች የመጀመሪያዎቹ ሆኑ። ሽርካቸው የተመሰረተው በማሕይምነት ፣ ዝንባሌን በመከተል ፣ መልካም ስራቸውን ለማስታወስ በሚል የነበራቸውን አሻራ ህያው በማድረግ ነበር። ከዚያም ድንበር በማለፍ ሷሊሆችን አመለኳቸው።

እንዲህ አይነቱ ዓላማ ሙስሊሙን ህብረተሰብ ቀስ በቀስ እንዲቃቃር ፣ በዱንያም በአኺራም የጥፋት አዘቅት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል። ምክንያቱም ኢብሊስ እና ተከታዮቹ ፣ ከሰው እና ከጅን የሆኑ ሰይጣናቶች የሙስሊሙን ድክመት ለዚህ ተግባር በፍጥነት ይጠቀሙበታል። የሰው ልጅ ማስታወሻዎችን ይወዳል ፣ በዚህ ምክንያት ፎቶ ግራፍ ይነሳል ከዚያም ለማስታወሻነት በሚል በህውልት መልክ መንገዶች ላይ ይተክለዋል ፣ ግድግዳ ላይ ያንጠለጥለዋል ፣ በትልቁ በማሰራት ግልጽ ከሆነ ቦታ ያንጠለጥለዋል። ከጊዜ በኋላ ማስታወሻ ህውልት ይሆናል። በዙሪያው ያሉት ሰዎች በተመለከቱት ቁጥር ትንሹም ትልቁም የእርሱ ውዴታ ፣ ታላቅነት እና ፍቅር በነፍሳቸው ውስጥ ይሰርጻል። ከዚያም ቅዱስ ያደርጉታል። ከዚያም ልክ የምስሉ ባለቤት እንደሚሰማ ፣ ወሬያቸው እንደሚደርሰው ሁሉ ስለሁኔታቸው

እንዲሁም የደረሰባቸውን ችግር ሁሉ ለሀውልቷ ያናግሯታል። ከዚያም ይማጸኗታል። ቁርባን በማቅረብ በረካ ከእርሷ ይፈልጋሉ። ለአላህ እንጅ ለማንም የማይገባውን አምልኮ አሳልፈው ለእርሷ ይሰጣሉ።

የግዙፍ እሳት መነሻ በትንሿ ቃንቄ መሆኑ ይታወቃል። ስለዚህ እያንዳንዱ ሙስሊም ይንቃ። ወደሽርክ የሚያደርሱ ነገሮችን እንደቀላል አይመልከት።

ለኑህ ﷺ ህዝቦች መጥመም ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ሽርክ በምድር ገጽ እንዲከሰት በር ከፋች የሆነው የሷሊሆችን ሀውልት ህያው በማድረግ ነው። ኑህን ሲያስተባብሉ ፣ ሲኮሩ ፣ የጌታቸውን ትዕዛዝ ሲነቅፉ አላህ በውሃ መጥለቅለቅ ከምድረ ገጽ አጠፋቸው።

**አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿وَأُوحِيَ إِلَى نُوحٍ أَنَّهُ لَن يُؤْمِنَ مِن قَوْمِكَ إِلاَّ مَن قَدْ آمَنَ فَلاَ تَبْتَئِسْ بِمَا كَانُواْ يَفْعَلُونَ۞وَاصْنَعِ الْفُلْكَ بِأَعْيُنِنَا وَوَحْيِنَا وَلاَ تُخَاطِبْنِي فِي الَّذِينَ ظَلَمُواْ إِنَّهُم مُّغْرَقُونَ۞وَيَصْنَعُ الْفُلْكَ وَكُلَّمَا مَرَّ عَلَيْهِ مَلأٌ مِّن قَوْمِهِ سَخِرُواْ مِنْهُ قَالَ إِن تَسْخَرُواْ مِنَّا فَإِنَّا نَسْخَرُ مِنكُمْ كَمَا تَسْخَرُونَ﴾

**“ወደኑህም እንሆ “ከህዝቦችህ በእርግጥ ካመኑት በስተቀር (ወደፊት) አያምኑም፤ ይሰሩትም በነበሩት (ክህደት) አትዘን ማለት ተወረደ።።” (አለህም) “በጥበቃችንና በትእዛዛችንም ሆነህ መርከቢቱን ስራ፤ በእነዚያም በበደሉት ሰዎች ነገር አታናግረኝ እነሱ በእርግጥ ሰማጮች ናቸውና” (አለው)። ከወገኖቹም መሪዎቹ በእርሱ አጠገብ ባለፉ ቁጥር ከእርሱ እየተሳለቁ መርከቢቱን ይሰራል ፤ “ከእኛ ብትሳለቁ እኛም እንደተሳለቃችሁብን ከናንተ እንሳለቅባችኋለን አላቸው።።”** *(ሁድ፡ 36-38)*

አላህ ኑሕ እንዲሰራት ያዘዛትን የመርከብ ሁኔታ የታሪክ ባለሙያዎች እና ሙፈሲሮች በኪታባቸው ላይ አውስተዋል። ኑህ አላህ ባዘዘው መሰረት ከዚህ በፊት የእርሷ አይነት ታይቶ የማይታወቅ ፣ ለወደፊትም የማይታይ ትልቅ መርከብ ገነባ- ምክንያቱም የነብዩ ተዓምር ነችና። ይህች መርከብ ሩሡሎችን ላስተባበሉ ህዝቦች እርሷን በመመልከት ትምህርት ይሆን ዘንድ ለተወሰኑ ዘመናት ከመከራ ተርፋ ተጠብቃ ቆይታ ነበር።

የመርከቧ መቆየት ለመገሰጽም ይሁን ለማስፈራራት ትምህርትና ተዓምር ነው። የዚህች መርከብ አሻራ በግልጽ ይታይ ነበር። የመጀመሪያዎቹና ቀዳሚዎቹ አግኝተዋታል። አካሏ እስከአሁን ድረስ ከመገኘት አልተወገደም።

አላህ የመርከቧን አካል ከጌታቸው በሆነ እዝነት ምክንያቶቿን በማቀራኘት ፣ ነገሮቿን በማግራት ፣ እነርሱን እና እቃዎቿን ተሸክማ ከአንድ አህጉር ወደሌላ አህጉር እንድትንቀሳቀስ በማድረግ በእርሷ እንዲገመግሙ ለዓለማት ተአምር እንድትሆን አደረገ።

ቀታዳ ﷺ የሚከተለውን እንደተናገረ ቡኻሪ ﷺ በተዕሊቅ የሚከተለውን ትክክለኛ ሐዲስ ዘግቧል፡-

*"أبقى الله سفينة نوح حتى أدركها أوائل هذه الأمة"*

*“የዚህ ኡመት የመጀመሪያዎች እንዲያገኟት ፣ የኑህን መርከብ አላህ ዘውታሪ አደረጋት።”*

የመርከቧ አሻራ ግልጽ ቢሆንም ባይሆንም እኛ የኑህን ህዝቦች በውሃ ማእበል እንዳጠፋ ጁድይ ተራራ ላይ የተደላደለች በሆነች እና ቀደምቶች ያገኟት በሆነች መርከብ ኑህን እና አማኞችን እንዳዳነ በእርግጠኛነት እውነት እንላለን። ለሚያስተነትኑ ሰዎች የእርሱና የህዝቦቹ ታሪክ ተግሳጽና መመከሪያ ሆነ።

## 2. የሁድ ﷺ ህዝቦች

በሌላ ጊዜ ከውሃው መጥለቅለቅ በኋላ በዓድ ህዝቦች አማካኝነት ሽርክ እንደገና ተከሰተ። አላህ ከመካከላቸው ሽርክን እንዲተው አላህን በብቸኛነት እንዲያመልኩ ጥሪ የሚያደርግ ሁድ የተባለውን ወንድማቸውን መልእክተኛ አድርጎ ላከ። ለኑህ ﷺ ህዝቦች ምትክ ነበሩ።

**አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿وَاذكُرُواْ إِذْ جَعَلَكُمْ خُلَفَاء مِن بَعْدِ قَوْمِ نُوحٍ وَزَادَكُمْ فِي الْخَلْقِ بَسْطَةً فَاذْكُرُواْ آلاء اللّهِ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ﴾

**“ከኑህም ህዝቦች በኋላ ምትኮች ባደረጋችሁና በፍጥረትም ግዙፍነትን በጨመረላችሁ ጊዜ አስታውሱ። የሻችሁትንም ታገኙ ዘንድ የአላህን ጸጋዎች አስታውሱ”** (አል ‘አዕራፍ፡ 69)

አካላቸው ብርቱ መጠናቸውም ትልቅ ነበር። በልማትና በግንባትም የተካኑ ምሁራኖች ነበሩ። ነገር ግን ይህን እውቀታቸውን እና ሙያቸውን ለክህደት ፣ ለአምባገነንነት ፣ ለአመጽ ፣ ወሰን ለማለፍ ታገዙበት። በኑህ ﷺ ህዝቦች አምሳያ የ "አድ" ህዝቦችም ሙሽሪክ ሆኑ። ከአላህ ውጭ አምላክ አድርገው ጣዖትን ይገዛሉ። በዚህ ምክንያት ሽርክና ጥመት ተሰራጨ። ተውሂድ ከእነርሱ ዘንድ እንደእንግዳ እና መጥፎ ድርጊት ሆኖ ተስተዋለ።

**ነብያቸው ሁድ ﷺ ወደተውሂድ ጥሪ ሲያደርግላቸው የህዝቦቹ ምላሽ የሚከተለው ነበር፡-**

﴿قَالُواْ أَجِئْتَنَا لِنَعْبُدَ اللّهَ وَحْدَهُ وَنَذَرَ مَا كَانَ يَعْبُدُ آبَاؤُنَا فَأْتِنَا بِمَا تَعِدُنَا إِن كُنتَ مِنَ الصَّادِقِينَ﴾

***"አላህን ብቻውን እንድንገዛ አባቶቻችንም ይገዙት የነበረውን (አማልክት) እንድንተው መጣህብን ከውነኞች ከሆንክ የምታስፈራብንን (ቅጣት) አምጣብን" አሉ።*** *(አል'አዕራፍ፡ 70)*

ይህችን -ሀያል የሆነውን አላህ በጠላትነት በአደባባይ የተጋፈጠች ፣ ተኣምሮችንም የካደች ፣ መልእክተኛዋን የነቀፈ ፣ በሀይሏ እና በብርታቷ ድንበር ያለፈች ፣ አስቀያሚ የሆነ ንግግር የተናገረች አምባገነን እና ኩራተኛ ህዝብ አላህ አጠፋ።

አላህ የሚከተለውን ተናገረ፡-

﴿فَأَمَّا عَادٌ فَاسْتَكْبَرُوا فِي الْأَرْضِ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَقَالُوا مَنْ أَشَدُّ مِنَّا قُوَّةً أَوَلَمْ يَرَوْا أَنَّ اللَّهَ الَّذِي خَلَقَهُمْ هُوَ أَشَدُّ مِنْهُمْ قُوَّةً وَكَانُوا بِآيَاتِنَا يَجْحَدُونَ﴾

***"ዓድም በምድር ላይ ያለ አግባብ ኮሩ ፤ "ከእኛ ይበልጥ በሀይል ብርቱ ማን ነው?" አሉም። ያ የፈጠራቸው አላህ እርሱ በሀይል ከእነርሱ ይበልጥ የበረታ መሆኑን አያዩምን? በተአምራታችንም ይክዱ ነበር።"*** *(ፋሲለት፡ 15)*

የሁድ ﷺ ህዝቦች የሆኑት ኣዶች ጥፋት እና የቅጣቱ ባህሪ የተግባራቸው ፣ የንግግራቸው እና የኩራታቸው አይነት እንደሆነ አንዳንድ ሙፈሲሮች አውርተዋል። በሀይል ከእነርሱ የበለጠችና የበረታች ነፋስን አላህ በነርሱ ላይ ሾመባቸው። ከብርታቷ ፣ ከሀይሏ ከአስደንጋጭነቷ የተነሳ በልብ ውስጥ ሀዘን እና ጭንቀትን ፣ በነፍስ ውስጥ ሽብርን የምትቀሰቅስ ነበረች።

በአፋቸው ገብታ ሆዳቸውን ሰንጥቃ በመጸዳጃቸው ትወጣ ነበር።

ከእነርሱ መካከል ግለሰቡ ወፍራም ከመሆኑ ጋር ነፋሷ ወደሰማይ ተሸክማ ወስዳ እንደገና ወደመሬት መልሳ ከምድር ላይ በአናቱ ፈጥፍጣ ትሰባብራቸው ነበር። የሰው አካል ልክ እንደተጎለሰሰ የተምር ግንድ ይመስላል። ከፊሎቹ በዚህ አይነት ቅጣት የሚቀጡትን በአይናቸው እየተመለከቱ ሳያስቡት ነፋስ በሰማይና በምድር መካከል ይዛቸው ትበራለች። በየቤቱ ፣ በየዋሻው እና በየጉድጓዱ ለመደበቅ እና ለመሸሽ የሚሞክሩትን ከገቡበት እየገባች አውጥታ ትጥላቸዋለች።

**አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፦**

﴿تَنزِعُ النَّاسَ كَأَنَّهُمْ أَعْجَازُ نَخْلٍ مُّنقَعِرٍ﴾

**"ሰዎቹን ልክ ከስሮቻቸው የተጎለሰሱ የዘንባባ ግንዶች መስለው (ከተደበቁበት) ትነቅላቸዋለች።"** *(አል'ቀመር፡ 20)*

## 3. የሷሊህ ﷺ ህዝቦች

የአድ ﷺ ህዝቦች በነፋስ እንዲጠፉ ከተደረገ በኋላ በመካከል ሰሙዶች ብቅ አሉ። አላህ ካጠፋቸው የዓረብ ነገዶች መካከል ሲሆኑ መኖሪያቸውም ከኢስላም በፊት ከነበሩ ዓረቦች ዘንድ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ወቅት ድረስ ይታወቃል።

አላህ ሷሊህን ወደሰሙድ ላከው። በእውነተኛነት ፣ በታማኝነት ፣ በክብሩ እና በዘሩ የተሟላ ሰው በመሆኑ ከእነርሱ ዘንድ የሚመሰከርለት ሰው ነበር።

**ነገር ግን ወደአላህ ብቸኛ አምልኮ ሲጠራቸው የሚከተለውን ይናገራሉ፦**

﴿قَالُواْ يَا صَالِحُ قَدْ كُنتَ فِينَا مَرْجُوًّا قَبْلَ هَذَا أَتَنْهَانَا أَن نَّعْبُدَ مَا يَعْبُدُ آبَاؤُنَا وَإِنَّنَا لَفِي شَكٍّ مِّمَّا تَدْعُونَا إِلَيْهِ مُرِيبٍ۝قَالَ يَا قَوْمِ أَرَأَيْتُمْ إِن كُنتُ عَلَى بَيِّنَةً مِّن رَّبِّي وَآتَانِي مِنْهُ رَحْمَةً فَمَن يَنصُرُنِي مِنَ اللهِ إِنْ عَصَيْتُهُ فَمَا تَزِيدُونَنِي غَيْرَ تَخْسِيرٍ﴾

**"ሷሊህ ሆይ! ከዚህ በፊት በእኛ ውስጥ (መሪ ልትሆን) በእርግጥ የምትከጀል ነበርክ።**

**አባቶቻችን የሚገዙትን ከመገዛት ትከለክለናለህን? እኛም ወደርሱ ከምትጠራን ነገር በእርግጥ አወላዋይ በሆነ መጠራጠር ውስጥ ነን" አሉ፡፡ "ህዝቦቹ ሆይ! ንገሩኝ ከጌታዬ በሆነ ማስረጃ ላይ ብሆን ከእርሱም የሆነን ችሮታ (ነብይነት) ቢሰጠኝና ባልታዘዘው ከአላህ (ቅጣት) የሚያድነኝ ማነው? ከማሳሳትም በስተቀር ምንም አትጨምሩልኝም" አላቸው፡፡"** *(ሁድ፡ 62-63)*

ይህ ከእርሱ የሆነ ወደመልካም ጥሪ ለማድረግ በመልካም የመጣ መሆኑን ለመግለጽ ከእርሱ የሆነ ጎኑን ለዘብ የማድረግ እና የእዝነት የሆነ አገላለጽ ነው፡፡

የሰሙድ ህዝቦች አንድ ቀን በአደባባያቸው ተሰባሰቡ፡፡ የአላህ ነብይ ሷሊህ ወደአላህ ጠራቸው ፣ አስታወሳቸው ፣ ገሰጻቸው ፣ አዘዛቸውም አስጠነቀቃቸው፡፡

ቋጥኙን በማመላከት **"እንዲህ እንዲህ ያለ ባህሪ ያላት ግመል ከዚህ ቋጥኝ አውጣልን"** አሉት፡፡

**"እስኪ ንገሩኝ እናንተ ወደጠየቃችሁኝ በምትፈልጉት መልኩ መልካም ምላሽ ብሰጣችሁ በእርሱ ወደእናንተ በመጣሁበት ነገር ታምናላችሁ ፣ በእርሱ በተላክኩበት እውነት ትሉኛላችሁ?"** አላቸው የአላህ ነብይ ሷሊህ፡፡

አዎ! አሉ፡፡ በዚህ ላይ የጠነከረ ቃልኪዳን በእነርሱ ላይ ያዘባቸው፡፡ ከዚያም ወደመስገጃው በመሄድ አላህ የወሰነለትን ያክል ሰገደ፡፡ እነርሱ የፈለጉትን ነገር እንዲያደርግላቸው ጌታውን ተማጸነ፡፡

እነርሱ በገለጿት መልኩ የአስር ወር እርግዝና ያላት ትልቅ ሴት ግመል እንዲያወጣ አላህ ቋጥኙን አዘዘው፡፡

እነርሱ በሚፈልጓት አይነት በተመለከቷት ጊዜ የድንጋጤ እና የመገረም ፣ አስደናቂ የሆነን ችሎታ፣ ቀራጭ የሆነን አስረጅ እና አንጸባራቂ የሆነ መረጃን ተመለከቱ፡፡ ከእነርሱ መካከል የተወሰኑ ጀማዓዎች አመኑ፡፡ አብዛኞቹ ደግሞ በክህደታቸው እና በአመጻቸው ቀጠሉ፡፡

**የአላህ ነብይ ሷሊህ የሚከተለውን አላቸው፤-**

﴿وَيَا قَوْمِ هَذِهِ نَاقَةُ اللّهِ لَكُمْ آيَةً﴾

**"ሕዝቦቼም ሆይ! ይህቺ ለእናንተ ተዓምር ስትሆን የአላህ ግመል ናት፡፡"** (ሁድ፡ 64)

ይህች ግመል በመካከላቸው ቆየች። ከምድራቸው እንደፈለገች ትግጣለች። ከአንድ ቀን በኋላ ለአንድ ቀን ያክል ውሃ ለመጠጣት ወደባህሩ ትወርዳለች። በራሷ የወረፋ ቀን ከባህሩ ውሃን ትጠጣለች። ፡ ከውሃ ላይ ያላቸውን ፍላጎት በተሰጣቸው የወረፋ ቀን ያደርጉ ነበር። ነገሩ ሲራዘም ሹማምንቶችን ጠርተው ስብሰባ አደረጉ። ውሃቸው እንዲበዛ ፣ ከእርሷም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመገላገል ግመሏን ለመውጋት በአንድ ድምጽ ተስማሙ። ይህን ተግባራቸውን ሰይጣን አሳመረላቸው።

**የእነርሱን ስራ አላህ እንደሚከተለው ይነግረናል፤-**

﴿فَعَقَرُواْ النَّاقَةَ وَعَتَوْاْ عَنْ أَمْرِ رَبِّهِمْ وَقَالُواْ يَا صَالِحُ ائْتِنَا بِمَا تَعِدُنَا إِن كُنتَ مِنَ الْمُرْسَلِينَ﴾

**"ወዲያውም ግመሊቱን ወጓት፡፡ ከጌታቸውም ትዕዛዝ ወጡ፡፡ አሉም፡- "ሷሊህ ሆይ! ከመልእክተኞቹ እንደሆንክ የምታስፈራራብንን (ቅጣት) አምጣብን፡፡"** (አል'አዕራፍ፡ 77)

እነርሱን በመስማማትና በማገዝ ጠማማዎቻቸው ግመሏን ወጓት። በዚህ ምክንያት ነው ተግባሩ (ድርጊቱ) ወደሁሉም እንዲጠጋ የተደረገው።

ጥመታቸው እና አመጻቸው በዚህ ልክ አላቆመም። ይልቁንም ከዚህ በከፋ ሁኔታ ነገሩ ድንበር አለፈ። በሶስቱ ቀናት ውስጥ ፣ አላህ በሚከተለው ቁርኣን ስለነርሱ የነገረን ቡድኖች ተሰባሰቡ።

﴿وَكَانَ فِي الْمَدِينَةِ تِسْعَةُ رَهْطٍ يُفْسِدُونَ فِي الْأَرْضِ وَلَا يُصْلِحُونَ﴾

**"በከተማይቱም ውስጥ በምድር ውስጥ የሚያበላሹና የማያሳምሩ ዘጠኝ ሰዎች ነበሩ፡፡"**

*(አን'ነምል፡፤ 48)*

ነብያቸውን ለመግደል ተመካከሩ። የአላህ ነብይ ቤተሰቦች ከድርጊታችን ይከለክሉናል በሚል ስጋት የውይይታቸውን ሚስጢርም ድብቅ አደረጉ። ምክንያቱም ልቅና እና ክብር ካላቸው ወገኖች ውስጥ ናቸውና።

**ስለውይይታቸው አላህ የሚከተለውን ነግሮናል፡-**

﴿قَالُوا تَقَاسَمُوا بِاللَّهِ لَنُبَيِّتَنَّهُ وَأَهْلَهُ ثُمَّ لَنَقُولَنَّ لِوَلِيِّهِ مَا شَهِدْنَا مَهْلِكَ أَهْلِهِ وَإِنَّا لَصَادِقُونَ ۞ وَمَكَرُوا مَكْرًا وَمَكَرْنَا مَكْرًا وَهُمْ لَا يَشْعُرُونَ ۞ فَانظُرْ كَيْفَ كَانَ عَاقِبَةُ مَكْرِهِمْ أَنَّا دَمَّرْنَاهُمْ وَقَوْمَهُمْ أَجْمَعِينَ﴾

**“እርሱንና ቤተሰቦቹን ሌሊት ልንገድል ከዚያም ለዘመዱ የቤተሰቦቹን ጥፋት (መገደላቸውን) አላየንም ፤ እኛም እውነተኞች ነን ልንል በአላህ ተማማሉ” አሉ። ተንኮልንም መከሩ። እነርሱም የማያውቁ ሲሆኑ በተንኮላቸው አጠፋናቸው፡፤ የተንኮላቸውም መጨረሻ እንዴት እንደነበረ እኛ እነርሱንም ሕዝቦቻቸውንም በሙሉ እንዴት እንዳጠፋናቸው ተመልከት።”** (አን’ነምል፡ ከ49-51)

ይህን ታላቅ የሆነ ሴራ አሴሩ። የአላህን ነብዩ ሷሊህን የመግደል እድል ለመጠቀም በተራራው ስር ተደበቁ። ወደጀሐነም እሳት ለህዝቦቻቸው መሪ እንዲሆኑ እና የጥፋት ቀዳሚዎች ይሆኑ ዘንድ አላህ በእነርሱ ላይ ቅጣትን አወረደ። ቋጥኝን አላህ ከተራራው ላይ ላከ። ፈነከተቻቸው ፣ በአስቀያሚ ሁኔታ ተገደሉ።

ሶስት ቀናቶች ሲሞሉ ከበላያቸው ጩኸት መጣቻቸው ፣ ከስር ደግሞ የመሬት መንቀጥቀጥ አጋጠማቸው። ወደቁ ፣ ሩሀቸው ወጣች ፣ ነፍሳቸው ከአካላቸው ተለየች ፣ በአገራቸው ነፍስ የሌላቸው ጥንቦች ምንም የማይንቀሳቀሱ የተንበረከኩ እና ከሰል መስለው አነጉ።

ከጥፋታቸው በኋላ የአላህ ነብዩ ከህደታቸውን በማርዳት ከእነርሱ ዞረ።

﴿فَتَوَلَّىٰ عَنْهُمْ وَقَالَ يَا قَوْمِ لَقَدْ أَبْلَغْتُكُمْ رِسَالَةَ رَبِّي وَنَصَحْتُ لَكُمْ وَلَٰكِن لَّا تُحِبُّونَ النَّاصِحِينَ﴾

**“(ሷሊህ) ከእነርሱም ዞረ። (እንዲሁም) አለ “ወገኖቼ ሆይ! የጌታዬን መልክት በእርግጥ አደረስኩላችሁ። ለእናንተም መከርኳችሁ፤ ግን መካሪዎችን አትወዱም።”**

(አል’ አዕራፍ፡ 79)

ከቅንነት እና ከኢማን ፣ እውርነትን እና ድንበር ማለፍን ወደዱ። ቅጣቱ እና ኪሳራው በእነርሱ ላይ ወደቀ።

## 4. የሉጥ ﷺ ህዝቦች

ጸያፍ ተግባርን በመፍጠር ከሰው ልጆች አንድም ያልቀደማቸው ወደሆኑ ህዝቦች አላህ ነብዩ ሉጥን ላካቸው። እርሱም ከዓለማት ወንዶችን (በግብረ ሰዶም) መገናኘት ነው። ያለማጋራት በብቸኛነት አላህን እንዲገዙ ሉጥ ጥሪ አደረገላቸው። ሀራሞችን ፣ ጸያፎችን ፣ መጥፎ እና አስቀያሚ ተግባራቶችን ከመተግበር ከለከላቸው። በጥመታቸው ፣ ድንበር በማለፋቸው ፣ በክህደታቸው እና በአመጻቸው ላይ ቀጠሉ። ሽርካቸው ከሴራቸው ክፋት ፣ ከተግባራታቸው አስቀያሚነት ጋር ተሰባሰበ።

እነርሱ ከሰዎች ሁሉ በጣም አመጸኛ ፣ በጣም ከሀዲ ፣ ሴራቸው በጣም የከፋ ፣ ውስጣቸው በጣም የከፋ ፣ ታሪካቸውም በጣም የወረደ ነው። መንገድን ዘግተው በአደባባይ ክፉ ተግባራትን ይፈጽማሉ። ከመጥፎ በሚሰሩት ስራ እርስ በእርስ አይከላከሉም ፣ ሲሰሩት የነበረው ምን ከፋ!

አላህም በአዕምሯቸው ውስጥ ትዝ ብሏቸው የማያውቅ መከራ አወረደባቸው። በዓለማትም ምሳሌና የዓለማት አባቶች የሚማሩበት ትምህርት አደረጋቸው።

አላህ መልእክተኛውን መርዳት እና ጠላቶችንም ለማጥፋት በፈለገ ጊዜ ፣ ወጣት የሆኑ የሰው ልጅ ቅርጽ የተላበሱ እና እንግዳ የመሰሉ መላኢካዎችን ወደሉጥ ላከ። አስቀያሚ የሆነውን የወገኖቹን ድርጊት በማወቁ ሉጥ ከፋው።

**በአላህ ነብይ ሉጥ ላይ ነገሩ እና ሁኔታው ሲያሳስበውና ሲያጨናንቀው፡**

﴿قَالَ لَوْ أَنَّ لِي بِكُمْ قُوَّةً أَوْ آوِي إِلَى رُكْنٍ شَدِيدٍ۞قَالُواْ يَا لُوطُ إِنَّا رُسُلُ رَبِّكَ لَن يَصِلُواْ إِلَيْكَ فَأَسْرِ بِأَهْلِكَ بِقِطْعٍ مِّنَ اللَّيْلِ وَلاَ يَلْتَفِتْ مِنكُمْ أَحَدٌ إِلاَّ امْرَأَتَكَ إِنَّهُ مُصِيبُهَا مَا أَصَابَهُمْ إِنَّ مَوْعِدَهُمُ الصُّبْحُ أَلَيْسَ الصُّبْحُ بِقَرِيبٍ﴾

**"በእናንተ ላይ ለኔ ሀይል በኖረኝ ወይም ወደ ብርቱ ወገን ብጠጋ ኖሮ (የምሰራውን በሰራሁ ነበር)" አላቸው። "ሉጥ ሆይ! እኛ የጌታህ መልእክተኞች ነን። (ህዝቦችህ) ወደ አንተ (በክፉ) አይደርሱብህም፣፤ ቤተሰብህንም ይዘህ ከሌሊቱ በከፊል ውስጥ ይዘህ ሂድ። ከእናንተም አንድም (ወደኋላው) አይገላመጥ። ሚስትህ ብቻ ስትቀር። እነሆ እርሷን (እነሱን) የሚያገኛቸው ስቃይ ያገኛታልና። ቀጠሯቸው እንጋቱ ላይ። ንጋቱ ቅርብ አይደለምን?" አሉት።"** *(ሁድ፡ 80-81)*

ከእነርሱ ሌላ ያለ ማህበረሰብ ባልተቀጣበት የቅጣት አይነቶች ተቀጡ። አይናቸውን በማጥፋት ፣ በጩኸት ፣ ምድራቸውን ላዩዋን ወደታች በማድረግና በእነርሱ ላይ በመገልበጥ ፣ ከሰማይ በመጣ ዲንጋይ በመደብደብ ፣ የመሬት ክፍል ተደርምሶ ወደታችኛው የመሬት አዘቅጥ እንዲዋጡ በማድረግ የቅጣት አይነቶችን አነባበረባቸው። ሰላምን እና አፊያን ከአላህ እንጠይቃለን።

ጸያፍ ተግባር የፈጸመውን ፣ መጥፎ ስራ ሲሰራ የወደደውን ፣ ዝም ያለውን ሁሉ ቅጣቱ አዳረሰ። ሁሉንም ጨረሳቸው። ለሚገመግሙ ሰዎች ታሪካቸው ቀሪ እንዲሆን ተደረገ።

የሉጥ ህዝቦች የከተማ ቅሪት በጣም ከሚሸትና በውሃው ሰዎች ከማይጠቀሙበት እንዲሁም አካባቢዋ ለጥፋቷ ፣ ለወራዳነቷ ለምንም የማይሆን ባህር ስር እንደሆነች አንዳንድ ተንታኞች ፣ ሙፈሲሮች እና የታሪክ ምሁራኖች አውስተዋል። ይህን ጉዳይ ሀፊዝ ብን ከሲር ﷺ ጠቁሞታል። ይህ አካባቢ በአሁኑ ሰዓት በዮርዳኖስ እና በፍልሲጤም መካከል ሙት ባህር በመባል ይታወቃል። በእርሷ አካባቢ ያለችው ከተማ በምድረ ገጽ በጣም የወረደች እና ከሌላው አለም ግንኙት የሌላት ከተማ ነች።

## 5. የሹዓይብ ﷺ ህዝቦች

አላህ ሹዓይብን -ከእርሱ በፊት የነበሩት ነብያቶች እና ሩሡሎች ሁሉ ዳዕዋ ባደረጉበት ጥሪ ላይ- መልእክተኛ አድርጎ ወደመድየን ህዝቦች ላከ።እርሱም ተውሒድን አጥብቀው እንዲይዙ

፣ ሽርክን አሽቀንጥረው እንዲጥሉ። እንዲሁም እነርሱ እየፈጸሙ ያሉትን በደልና ግፍ ፣ በስፍር እና በሚዛን ዙሪያ እየፈጸሙት ያለውን ማጭበርበር አነቃቸው።

ነብዩ ሹዓይብ ለጥመታቸው መፍትሄ ለመስጠት ከፍተኛ የዳዕዋ ጥረት ቢያደርጉም ከህዝባቸው እምቢተኝነት እና ማስተባበል ፣ ማገድ እና ማመጽ እንጅ ሌላ አልገጠማቸውም። ከሽርካቸው ፣ ከማስተባበላቸው ፣ ሚዛን እና ስፍር ከማጉደላቸው ፣ በስራ ከማታለላቸው ፣ የአላህን ነብይ ሹዓይብ ከማሰቃየት ፣ በእነርሱ ላይ ቅጣት አምጣብን እያሉ ከማስፈራራታቸው ጋር በዚህ አልተቆጠቡም የቅጣት አይነቶችን አስጠነቀቁ። ስለነርሱ ቁርኣን እንደሚከተለው ያወሳዋል፡

﴿فَأَسْقِطْ عَلَيْنَا كِسَفًا مِّنَ السَّمَاءِ إِن كُنتَ مِنَ الصَّادِقِينَ۞قَالَ رَبِّي أَعْلَمُ بِمَا تَعْمَلُونَ۞ فَكَذَّبُوهُ فَأَخَذَهُمْ عَذَابُ يَوْمِ الظُّلَّةِ إِنَّهُ كَانَ عَذَابَ يَوْمٍ عَظِيمٍ۞﴾

**"ከእውነተኞችም እንደሆንክ በእኛ ላይ ከሰማይ ቁራጭን ጣልብን። "ጌታዬ የምትሰሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው" አላቸው። አስተባበሉትም። የጥላይቱ ቀን ቅጣትም ያዛቸው። እርሱ የከባድ ቀን ቅጣት ነበርና።"** *(አሽ'ሹዓራእ፡ 187-189)*

የአጠፋፋቸው ሁኔታ በተከበረው ቁርኣን በተለያዩ መልኮች ፣ በተለያየ የቅጣት አይነቶች መጧል። አንዳንዴ በጩኸት ፣ አንዳንዴ በመንቀጥቀጥ ፣ አንዳንዴ በጥላው ቀን ቅጣት። ስለዚህ በአንድ ወቅት ይህ ሁሉ የተለያየ እና አይነቶቹ የተለያዩ ቅጣቶች መከሰታቸው የሚቃረን አይደለም። የቅጣቱ አይነት መለያየት የሚቀጡ ሰዎች የተለያዩ ናቸው የሚል ያስፈርዳል ብለን እንዳንገነዘብ።

**ሀፊዝ ብን ሀጀር ﵀ እንደጠቆመው በፈትሁል ባሪ (6/450) የሚከተለውን ተናግሯል፡-**

*"የቅጣት አይነቱ መለያየት በሚቀጡት ሰዎች ውስጥ መለያየትን የሚያስፈርድ ከሆነ በመሬት መንቀጥቀጥ የተቀጡት በጩኸት ከተቀጡት ይለያሉ ፤ እውነታው ግን ሁሉም ቅጣት ሁሉንም አካል አግኝቷቸዋል የሚለው ነው። ብርቱ ሙቀት አግኝቷቸዋል። ከቤቶች ወጡ*

*ደመና አጠለላቸው ከስሯ ተሰባሰቡ ምድር አንቀጠቀጣቸው። ከበላያቸው ጩኸት ያዘቻቸው።"* ሩሃቸው ወጣች። ነፍሶቻቸው ከአካላቸው ተለየች ፤ አካላቸው አመድ ሆነ።

➢ **የጠፉ ህዝቦችን አሻራ ህያው ማድረግ ብይኑ**

ካሳለፍነው ትምህርት ግልጽ የሚሆነው ማስረጃው ፣ ግልጽ አስረጅው ይፋ ከመሆኑ ጋር የጠፉ ህዝቦች በፈተናው ላይ የከሰሩ ከቅንነት እና ከኢማን ይልቅ፣ እውርነትን መርጠዋል ፣ ጥመትን ወደዋል በዚህ ምክንያት በእነርሱ ላይ ቅጣቱ እና ኪሳራው ወደቀባቸው።

በሙስሊሞች ላይ ያለባቸው ግዴታ በእነርሱ ላይ የሚታይ የቀረ አሻራ ባይኖርም በእነርሱ ላይ በተገኘው ቅጣትና መቀጣጫ በኪታብ እና ካለፉ ወሬዎች በትክክለኛው ሱና በመጣው ማመን እና እውነት ማለት ነው። ከቦታዎች ፣ ከመኖሪያቸው ፣ ከአገራቸው ላይ የቀሩ አሻራዎች ካሉ ግዴታው ቀጥ ባለው ነብያዊ ጎዳና መጓዝ ነው።

በጠፉ ህዝቦች አሻራ ወይም ፋና መቆየት እንደማይቻል ፣ በመንገድ ላይ ካልሆነ በቀር እንደማይገባ በትክክለኛው ሐዲስ ተጠቁሟል። በተቀጡ ህዝቦች ያለምንም ሐጃ ለማስተንተን ቢሆንም እንኳ መግባት በውስጧ መቆየት ክልክል ነው።

ከተከበሩት ረሡላችን ተግባር እና አላማ ጋር ተስማሚ የሆነው ለተቡክ ዘመቻ በወጡ ጊዜ በሰሙድ መንደር አለፉ ፣ በልብስ ተሸፈኑ ፣ ሶሃቦች በፍጥነት እንዲያልፋ አዘዙ። በመንገዱ ለመጣ አካል የነብዩ ﷺ መንሐጅ ነው ተግሳጹና ማስተንተኑ።

እንደዚሁ እርሷን ለመገሰጽ አላማ እንድትዘየር ወይም ለማስተንተን ወደርሷ መግባትን የአላህ መልእክተኛ አላዘዙም። ከመግባት ከልክለዋል ፣ አስጠንቅቀዋልም። ይህ ህጋዊ ቢሆን ኖሮ ቀብሮች አኼራን ለማስታወስ እንዲጎበኙ እንዳዘዙት ሁሉ ነብዩ ባዘዙ ነበር። አንድም ቀን የአድ ፣ የሰሙድ ፣ እና የሌሎችም የተቀጡና ጥፋት የደረሰባቸውን ህዝቦች ቦታዎች ጎብኙ የሚል አንድም ቀን አልተናገሩም። ለማስተንተን አላማ በማድረግ ላይም ቢሆን እርሷን ጎብኟት የሚል ወሬ እስከማውቀው ድረስ ከአንድም ሰለፍ አልመጣም።

**ክልክል ለመሆኑ የሚጠቁሙ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው ፡**

1. ከኢብን ዑመር رضي الله عنهما የተላለፈው ሐዲስ፡ "ነብዩ በተቡክ ዘመቻ መንገድ ላይ እያሉ ፤ ሀጅር በሚባለው ቦታ አለፉ። ከጉድጓዷ ውሃ እንዲይዙ ሶሃቦችን አዘዙ። በእርሱም እንዲያቦኩ አደረጉ። ከጉድጓዱ ያወጡትን ውሃ እንዲደፉ አዘዙ። የተቦካውን ግመሉ እንዲመገበው ፤ ግመሎች ሲወርዱበት ከነበረው ጉድጓድ ውሃ እንዲይዙ አዘዟቸው።"

ትክክለኛ በሆነው የቡኻሪ ሐዲስ ደግሞ የሚከተለው መጧል ፡ "እነርሱ የደረሰባቸውን አይነት መከራ ከመጠንቀቅ ፣ አልቃሾች ሆናችሁ እንጅ ነፍሳቸውን በበደሉ ሰዎች መኖሪያዎች አትግቡ።" ከዚያም አስጠነቀቋቸው። ወደኋላቸው እስከትቀር ድረስ እየፈጠኑ አለፉ። *(ቡኻሪ፡ 4419)*

በሌላ ዘገባ በትክክለኛ የቡኻሪ ሐዲስ፡ "አልቃሽ የማትሆኑ ከሆነ በእነርሱ ላይ አትግቡ" *(ቡኻሪ፡ 4702)*

በሙስነድ ኢማም አህመድ በትክክለኛ ሰነድ የሚከተለውን ዘግበዋል፡ የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናገሩ ፡ -

"እኔ እነርሱ የደረሰባቸው ዓይነት እንዳይደርስባችሁ እፈራለሁ ፤ በእነርሱ ላይ አትግቡ።" *(አህመድ፡ 5984)*

በኢብን ሂባን ትክክለኛ በሆነ ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"በእነዚያ በተቀጡ ህዝቦች ላይ አትግቡ - እነርሱ የደረሰባቸው አይነት ይደርስባችኋልና።" *(ኢብኑ ሂባን፡ 6203)*

2. ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ኢብን ዑመር رضي الله عنهما ባስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"የቀዱትን ውሃ እንዲደፉ አዘዟቸው። ግመሎቹ ሊጡን እንዲበሉ አዘዙ። ግመል ከሚወርድበት ወንዝ ውሃ እንዲጠቀሙ አዘዙ።"

ኢብን ሂባን በትክክለኛ ሐዲስ በዘገበው፡ "ግመል ከሚጠጣበት ቦታ እስከሚያርፉ ድረስ ከዚያም ጉዞ ቀጠሉ ፣... ."

ትክክለኛ የቡኻሪ እና የኢብን ሂባን ዘገባ፡ "ረሡል ራሳቸውን ሸፈኑ ፣ ግመል ከሚጠጣበት ቦታ

ደርሰው እስከሚያርፉ ሸለቆውን ለማለፍ ፈጥነው ተጓዙ" ዘገባው ከፊሉ ከፊሉን ያብራራዋል፡፡

3. የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡- "አላህ ወደተቆጣባቸው ህዝቦች ለምን ትገባላችሁ?"

**"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእነርሱ እንገረማለን"** በማለት አንድ ግለሰብ ጥሪ አደረገላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም የሚከተለውን ተናገሩ፡- "ከዚህ የበለጠ በጣም አስደናቂውን አነግራችኋለሁ፡፡ ከራሳችሁ የሆነ ሰው ከዚህ በፊት የሆነውን ፣ ከአናንተ በፊት የሚሆነውንም ይነግራችኋል፡፡ ቀጥ በሉ ፣ አስተካክሉ ፣ አላህ አናንተን በመቅጣቱ ቦታ አይሰጠውም፡፡ ከዚያም ከነፍሳቸው አንዳም ነገር መከላከል የማይችሉ ህዝቦች ይመጣሉ፡፡" ሐዲሱን በሙስነዱ ኢማም አህመድ ዘግቦታል ሰነዱም ሀሰን ነው፡፡

**በተጠፉ አገሮች በሚገኙ ህዝቦች የማለፍ ሁኔታ ፡**

1. **ማለፉ የሚበቃ፡** የግለሰቡ ማለፍ ከረሡል ተግባርና አላማ ጋር ከተስማማ ማለፉ ይበቃል፡፡ ረሱል እና ሶሃቦች የሷሊህን የተጠፉ ከተሞች -ማስተንተንን እና በተቀጡት ሰዎች ቅጣት መገሰጽን አጥብቀው በመያዝ ፣ የቅጣትን ቦታዎች እስከሚተው ድረስ በግንባታቸው መደነቅን በመራቅ እንዲሁም ከእርሷ አንድም ነገር ሳይዙ ፣ በእርሷም መጥቀም እና መጠቀም ሳይኖር- ቦታዎችን አላማ ሳያደርጉ በአንድ በኩል አልፈዋል፡፡

2. **ማለፉ አዲስ ፈጠራ** የሆነ፡ ጎብኝው ቅጣት የደረሰባቸውን ሰዎች መንደር ወደአላህ ለመቃረብ ለመገዛት አላማ አድርጎ ማለፉ በዲን ላይ አዲስ ፈጠራ ነው፡፡

3. **ሙሽሪኮችን መመሳሰል፡** መደነቅን ፣ መኩራትን ከዚህ ጀርባ የሚገኙ ነገሮችን አላማ አስቦ ማለፍ ከሆነ ሙሽሪኮችን እና ካፊሮችን መመሳሰል ነው፡፡

**ማጠቃለያ**

የጥፋት ቦታዎችን መጎብኘት ፣ ለእርሷ ብሎ የአካል ጉዞን መጀመር አይፈቀድም፡፡ ለጉብኝት ብሎ ወደርሷ መግባት ሸሪዓዊ አይደለም፡፡

ከረሡል ተግባር ጋር የሚገጥመው፥ ረሡል ﷺ ለተቡክ ዘመቻ ወጡ ፣ በሰሙድ መንደር እርሷን አላማ ሳያደርጉ አለፉ ፣ ራሳቸውን ተሸፋፈኑ ፣ ከፍርሀት እና ከለቅሶ ጋር ፈጥነው እንዲጓዙ አዘዙ ፣ በቦታዋም ላይ እረፍት አላደረጉም።

በእርሷ ለማስተንተንም ይሁን ለመገሰጽ አላማ አድርጎ ወደርሷ መግባት በሸሪዓ አልመጣም። ወደርሷ መግባት የተከለከለ መሆኑና ከእርሷም መቆየቱን የሚያስጠነቅቅ በሸሪዓ መጧል። በነብዩ ﷺ ጎዳና የመጣው ቦታዋን አላማ ሳያደርግ በዚያ ቦታ ለሚያልፈው ተግሳጽና ማስተንተኑ ነው።

## የጣዖታውያን እና ቅድመ ኢስላም ቅርሶች

ሙስሊሞች ለቅድመ ኢስላም ራሳቸውን ከፍ ሳያደርጉ ፣ ለአሻራዋ ትኩረት ሳይሰጡ ፣ ስለርሷ ምንም ቦታ ሳይሰጡ ለረጅም ዘመን ኖረዋል። ምናልባት ካወሷትም የነበሩበትን ጥመት ግልጽ ለማድረግ እና አላህ እንዴት እንደመራቸው ፤ በኢስላም ጸጋውን እንዴት እንደዋለላቸው ለመዘከር ብቻ ነው።

ካፊሮች የሙስሊም አገሮችን በቅኝ ግዛት እስከሚወሩ ፣ አመለካከታቸው እና እምነታቸው እስከሚቀየር ፣ ፍላጎታቸው እንደነርሱ አባባል የጃሂልያ አሻራዎችን ህያው ለማድረግ ፣ የቀደምት ታሪኮችን ፣ የተደበቁ እና ያልታወቁ ታሪኮችን ለማወቅ የመሬትን ድልብ ሀብቶች ቆፍሮ ለማውጣት አቅጣጫ እስከሚይዙ ድረስ ሰዎች በእስልምና ውስጥ እያሉ በመሬቶቻቸው ስር ቅርሶች ነበሩ። ይሁን እንጅ ስለነርሱ የሚወራው ታሪካዊ ንግግሮች በምንም አይነት ወደጎጠኝነት ፣ ዘረኝነት እና ስሜታዊነት አላነሳሳቸውም።

ለዚህ ጉዳይ የቅርስ አጥኝ ቡድኖች ምንም ጊዜ አልሰጡም። የሙስሊም አገሮችን መሬት በመቆፈር የድሮ የጃሂልያ ጣዖት ቅርሶችን ህያው ለማድረግ ተከታታይ አጥኝዎችን ላኩ። በኢስላም ውስጥ ያለው ወዳጅነት እንዲናጋ ፣ የሙስሊሙን አንድነት ለመበታተን ፣ የአገር እና የጎጥ ጨኸቶችን ለማቀጣጠል እና ኢራቅ ባቢሎናዊ ፣ ግብጽ ፊርዓውንያ ፣ ሻም ፊይኒቅያ እንደሆኑ እና እንዲሰነጣጠቁ ከሁሉም አገር ጋር ተዛማጅ የሆኑ አካላትን ሰንቀውና የልኡካን ቡድን አድርገው ይልካሉ።

ቀስ በቀስ አንዳንድ ሙስሊሞች ለኢስላም ያላቸው ወዳጅነት ተሸረሸረ ፣ ሙስሊም አገሮች ከኢስላም ይልቅ በጃሂልያ ልቅና እና ኩራት እንዲሰማቸው ሆነ። ከዚያም በጎጥ እና ዘረኝነት በመከፋፈል ግጭት ተጀመረ። ይህ ፊርዓውንያ ነው ፣ ይህ ባቢሎናዊ ነው ፣ ይህ ፊይነቅያ ነው በሚል ጃሂልያ ጎጠኝነት ጎጆውን ቀለሰ።

በራሳቸው ቋሚ የሆነ እስትራክቸር እንዲኖራቸው ለዘመናት ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ የሙስሊም

አገሮች በኢስላም ምድር የድሮ ቅርሶችን ህያው በማድረግ የካፊር አገሮችን እቅድ ማሳካት እና በዚህ ተግባራቸውም እርካታ ይሰማቸው ጀመር። ወዳጅነት እና ጠላትነት የአርኪዮሎጅ ግኝቱ ከተያያዘባቸው ባህሎች ጋር የተያያዘ ሆነ። በዚህም በሙስሊሞች መካከል ጣዖታዊ እና ቅድመ-እስልምና ብሄረሰቦች መነቃቃት ተገኘ።

“ቅርስን ሕያው ማድረግ” ወይም “እርሷን መጠበቅ” ወይም “እያንዳንዱ አገር ቀደምት ታሪኩን ማወቅ አለበት” ወይም “ከዝምድና ጋር የተቆራኘ ስልጣኔን እንዲሁም በእርሱ የሚሸለሙበት የሆነ የእውቀት እና የእድገት ቀዳሚነት ማስገኘትን ይፋ ማድረግ” የሚለው ግልጽ የሆነው ቅስቀሳቸው ሆነ። በቅርስ ጥበቃ ማዕከል ማስቀመጡም ቁሳዊም ይሁን ኢኮኖሚያዊ ፍሬ ያስገኛል ይላሉ።

ነገር ግን የውስጥ አላማቸው ሽርክን ፣ ሌሊትም ይሁን ቀን ካፊሮች የሚኖሯትን ጃሂልያ ጣዖቶች ህያው ማድረግ ነው። ድብቅ የሆነና ተንኮል ያዘለ አላማን እና በምድር ላይ የበላይነት ማረጋገጥ ነው ወይም በሙስሊሞች መካከል የዘረኝነትን ጉራ እና ኩራት ህያው ማድረግ ነው። አላማቸው በሙስሊሞች መካከል የአረማውያን እና የጃሂልያ ስርዓት በማስገባት የጠላትነት ፣ የጦርነት እንዲሁም ጎጠኝነት እንዲመሰረት ነው። በኢስላም አገሮች ውስጥ ፍላጎታቸው እንዲረጋገጥ ነው።

ቅርሶችን ለማውጣት ጥልቅ መሬቶችን በመቆፈር ታላላቅ መጠን ያለው ገባቸው መሳካቱ የሚያሳዝን ነው። ጃሂልያን የሚቃረን እና የሚያፈርሰውን ወደኢስላም መጠጋቱን በመርሳት ፣ የአገሮችን ታሪክ ለመመልከት በጣዖት የጃሂልያ እይታ ሁሉም የሚኮራ ሆነ።

የፈራኢኖች የልጅ ልጅ ነን በማለት አንዳንድ ግብጻውያን የሚያሳዩት ኩራት ፣ የፊይነቅይ የልጅ ልጆች ነን በማለት አንዳንድ ሊባኖሳውያን የሚያሳዩት ኩራት ፤ የባቢሎናውያን የልጅ ልጆች ነን በማለት አንዳንድ ኢራቃውያን የሚያሳዩት ኩራት እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

እነዚህን ቅርሶች ህያው ማድረግ ልክ የኑህ ህዝቦች ጣዖቶችን ህያው ካደረጉት ጋር የሚመሳሰል ነው።

እነርሱ የአለማት ጌታን በብቸኛነት መመለክ የሚጠሉ በመሆናቸው የእንቅስቃሴያቸው ፈጣን መሰረት ቅርሶችን ፈልፍሎ ማውጣት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ይህም ጥመት እና ከአላህ ውጭ አምልኮት ነው። ለዚህ ነው ሰይጣን ከጣኦቶች ላይ የሚያደርገውን ምርምር እየተመራመሩ የምታገኛቸው። የአረብ ሙሽሪኮች እንዲያመልኩት ሰይጣን በጅዳህ ዳርቻ ከሚገኘው አሸዋ ስር ለአምር ብን ሉህይ እንዳወጣለት ማለት። አንዳንድ የሙስሊም አገሮችን ቅኝ ግዛት የያዙ ካፊሮች ፣ የሸይጧን ወዳጆች እና ረዳቶች ናቸው። ለዚህ አላማ እነርሱን አገልጋይ ማድረጋቸው የሚያስገርም አይደለም።

**የጣዖት እና የጃሂልያ ቅርሶች ሲባል ካለፉ የጣዖታዊያን ህዝቦች የቀሩ የሚታዩ ምልክቶች ነው። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፦**

1. **ፈርዖናዊ ቅርስ፡**

ፈራዒና የሚባለው በአፍሪካ ሰሜን ምስራቅ ከናይል ወንዝ ዳርቻ ነዋሪ በመሆን የሚታወቁ ፣ ታሪካቸው ከኢሳ መወለድ በፊት ከሶስት ሽ አመት በላይ የሆናቸው የግብጽ አመራሮች ቅጽል ስም ነው። በአሁኑ ሰኣት የግብጽ አረብ ህዝባዊ ሪፓብሊክ በመባል ትታወቃለች።

ከፈራኢናዎች ዘንድ በበላይነት ተንሰራፍቶ የነበረው የጣዖት እና የኹራፋት (የተረት ተረት) እምነት የሚከተሉት ናቸው የነፍስ አትሞትም እና ከዚህ አለም በላይ ያለው የዘላለም ህይወት የነፍስ ሽግግር ትምህርት እና ነፍስ ከሞተች በኋላ ተመልሳ ሙሉ በሆነ አካል ውስጥ እና በህውልቶች ውስጥ ትኖራለች የሚል እምነት ነው።

ልክ እንደዚሁ የጣኦት አምላኪዎች ቁጥር እና ልዩነታቸው የጥንት ግብጽ ህዝቦች በግልጽ በሚታዩ በተፈጥሮ ክስተቶች እና በአካባቢ እቃዎች ተጽእኖ በመደረጉ ነው። ስለዚህ አማልክትን መቀበላቸው በፍቅር እና በታማኝነት ለነገሩ ባላቸው ስሜት ነው።

እርሱ ይወድልናል ፣ መጥፎን ነገር ያስወግዳል ፣ ይከላከልልናል ፣ ይሰጣል ፣ ከእነርሱ ያለውን ይወዳል ብለው ስለሚጠረጥሩ እና ስለሚያምኑ ይቀድሱታል ፣ በማህይምነት ይገዙታል፡፡ ከሚስተዋሉ ነገሮች አንዱ የድሮ የግብጽ እምነቶች ከአንድ አምላክ ወደሌላ አምላክ ወይም ወደሽርክ እና ጥመቶች መሸጋገሩ ነው፡፡ ይህም አንድን ነገር አምላክ አድርጋ ትይዛለች ከዚያ ሶስት ፣ ከዚያም ዘጠኝ ፣ ከዚያም ይነባበራል ፣ ቁጥራቸው መቶ እስከሚደርስ እና ከዚያ በላይ እስከሚተላለፍ ድረስ ታመልካለች፡፡

- **ማን ነው የፈርዖናዊ ቅርሶችን ህያው ለማድረግ የተንቀሳቀሰ? ፣ ለማውጣት ምክንያት የሆነ?**

እኔ እስከማውቀው ድረስ ሙስሊሞች ግብጽን ሲቆጣጠሩ ፈራኢናዊ ቅርሶች ተገኝተዋል ወይም አይተዋታል የሚል በታሪክ መጽሐፎች ተዘክሮ አያውቅም፡፡

ዘርከልይ "ሽብሁል ጀዚራ ፊ አህዱል መሊክ አብዱልዓዚዝ" በተባለው ኪታብ (4/"188) ያንጊዜ የተወሰኑ ቅርሶች አለመገኘታቸውን እንደሚከተለው ጠቁሟል፡

*"በርካታዋ በአሸዋ ተሸፍኖ ነበር በተለይም "አባልሀውል"*

**የግብጽ ታሪክ አዋቂው አቡል ዓባስ አልመቅሪዝይ "መዋኢዝ ወልኢዕቲባር" በተባለው ኪታብ (1/129) የሚከተለውን አውስቷል፡ -**

*"በሒጅራው አቆጣጠር በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ላይ "**አቡልሀውል**" ራሱ እና አንገቱ ብቻ እንጅ ሌላው አካሉ ግልጽ እንዳልሆነ መወሳቱ ይህንን እውነታ ያጠናክረዋል፡፡"*

በጎርጎሮሳዊያን አቆጣጠር በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የምእራባውያን የቅርስ ተመራማሪ የጉዞ ቡድን እንቅስቃሴ እስኪጀምር ድረስ የድሮ ታሪኮችን ህያው ማድረግ በፈረንሳዮች እጅ እንደነበር ይታወቃል፡፡

የፈራኢናዎችን ቅርስ ህያው በማድረግ ላይ በምስራቃዊያን እጅ መሆኑ ትልቅ እድል ነበር፡፡ በሙስሊም አገሮች የተደረገው የመጀመሪያውና ታዋቂው የአርኪዖሎች ቡድን በጎርጎሮሳዊያን አቆጣጠር በ1798 ግብጽ ውስጥ ነበር፡፡ ይህን የመስቀላዊያን የአርኪዮሎጅ የምርምር ቡድን

የመራው ናቢሎዮን የተባለው ግለሰብ ነበር። ቅርስ ለማውጣት እና የተጻፈውን ለማንበብ ቁጥራቸው ከመቶ በላይ የሚሆኑ ተመራማሪዎች ተሳትፈዋል።

ከዚያ በኋላ በጎርጎሮሳዊያን አቆጣጠር በ19ኛው ክፍለ ዘመን የፈርኦናውያን ቅርሶችን ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት የውጭ አርኪዮሎጅስቶች ተልእኮዎች ተከታተሉ። አሁን እስካለንበት ክፍለ ዘመን ድረስ በፈርኦናዊያን የጣዖታት ቅርሶች ያላቸውን አድናቆት ይፋ ለማድረግና ቅርሶችን ለማጠናከር ምስራቃውያን እንዲሁም አውሮፓውያን ተመራማሪዎች የአርኪዎሎጅ ምርምር ለማድረግ ወደግብጽ ከመግባት አልተወገዱም።

## 2. የፊይኒቅያ ቅርሶች

ፊይነኒቅያ የሚለውን ስም የሚናገሩት ግሪኮች ናቸው። እነዚህ ማህበረሰቦች በመካከለኛው ነጭ ባህር ዳርቻ ኗሪ ነበሩ። በካፒቴንነት ፣ በመርከብ ስራ እና በሀምራዊ ቀለም የተዋቡ ልብሶችን በማዘጋጀት ይታወቁ ነበር። ታሪካቸው ከእየሱስ ልደት ከሁለት ሺ ክፍለ ዘመን ቀደም እንደሚል የታሪክ ምሁራኖች ይገልጻሉ።

ፊይኑቅያ ከመካከለኛው ነጭ ባህር ዳርቻ ላይ የከተሞች ስብስብ እንጅ ራሷን የቻለች የነጻነት ፖለቲካዊ ግዛት አልነበረችም። ሁሉም ከተሞች ከሌላው ከተማ በተለየ ሁኔታ ራሱን የቻለ ንጉስ ፣ የተለያየ አምላክ አለው። እነዚህ የተለያዩ ክልሎች ተሰባስበው በአንድነት በፖለቲካም ይሁን በኢኮኖሚም የጋራ አስተዳደር እንደነበራቸው ይታወቃል። ልክ በፈርኦናውያን እና ባቢሎናውያን ስርአት ዓይነት አልነበረችም። የተለያየ ክፍል ቢኖራቸውም በሐይማኖት ስርአት እና በቅርስ ቅሪቶች ስምምነት ነበራቸው።

**በፊይነቂያ ውስጥ ጎልተው የወጡና የበላይነትን ተቆጣጥረው የነበሩ የጣዖት እምነቶቻቸው ፣ የጃሂልያ ኹራፋቶች (ተረት ተረቶች) የሚከተሉት ነበሩ ፡**

በአማልክት ምክር ቤት ውስጥ በተደራጁ በርካታ አማልክት ውስጥ የተካተቱት የደጋፊዎች ክብር እና ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ልቅና መስጠት ፣ እያንዳንዱም የራሱ የሆነ ደረጃ ያለው እና

በአጉል ሃይማኖታዊ ስርዓቶች መሰረት የሚተገበር መሆኑ ፣ በተጨማሪ ፊይነቂያን በፈራኢኖች ዓቂዳ ወይም እምነት ተጽእኖ ተጠልፈው የሩህ ዘላለማዊነት ፣ የዘላለማዊ ህይዎት አመለካከት የሚያራምዱ መሆናቸው።

**የፊይኒቂያ ቅርሶች ህያው እንዲሆኑ ማን ተንቀሳቀሰ? ፣ እርሷን ለመውጣትስ ማን ምክንያት ሆነ?**

ፊይኒቂያዎች ከግሪኮች እና ከሮማኖች የድሮ መጽሐፎች የተገኘው እንጅ ሌላ የሚዘከር ታሪክ የላቸውም።

ይፋ መሆን የጀመረው ግብጽ ውስጥ በናቢሊዮን መሪነት የፈራኢኖችን ቅርስ ለማውጣት የፈረንሳይ አርኪዮሎጅስቶች ቡድን እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረ በኋላ ነው። በዚያ ወቅት በፊይኒቂያ እና በፈራኢን መካከል ግንኙነት እንዳለ ፣ ፊይኒቂያ የነበሩበትን ቦታ የሚጠቁሙ ጣውላ ላይ የተጻፉ የተቀረጹ ጽሁፎች እና ቋጥኝ አገኙ።

ከእነዚህ የአርኪዮሎጂያዊ የምርምር ጥናት አንጻር ከ 19-20 ክፍለ ዘመን ከፈረንሳይ እና ከጀርመን የመጡ የአርኪዮሎጂ አጥኝ ቡድኖች በሜዲትራኒያን ባህረ ዳርቻ ያሉትን ከተሞች ከጎበኙ በኋላ አንዳንድ ጥንታዊ ቅርሶችን ወደ ፈረንሳይ ሉቭር ሙዚየም ማስተላለፋቸው ታውቋል።

የእነዚያ ክልሎች ህዝቦች በምርምር ፣ በቁፋሮዎች እና ለበርካታ ዘመኖች ከጠፋ በኋላ የወጡ የተቀበሩ ጥንታዊ አረማዊ እና ከእስልምና በፊት የነበሩ ቅርሶችን ሙዚየሞች በማቋቋም በርካታ ፈተናዎች ደርሰባቸዋል።

## 3. የባቢሎናውያን ቅርሶች

ባቢሎን በባግዳድ ደቡብ ኢራቅ ፣ በኤፍራትስ በግራ በኩል በሚገኘው ዳርቻ በሁለቱ ወንዞች መገናኛ ታች ላይ ይገኛል። ታሪካቸው ከእየሱስ ልደት ከሶስት ሽ አመት በላይ ቀደም እንደሚል ይታወቃል።

ባቢሎን በተከበረው ቁርኣን እንደሚከተለው ተወስቷል፡

﴿يُعَلِّمُونَ النَّاسَ السِّحْرَ وَمَا أُنزِلَ عَلَى الْمَلَكَيْنِ بِبَابِلَ هَارُوتَ وَمَارُوتَ وَمَا يُعَلِّمَانِ﴾

**“ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲሆኑ ካዱ፡፡ ያንንም በባቢል በሁለቱ መለእክት በሃሩትና ማሩት ላይ የተወረደውን ነገር (ያስተምሯቸዋል) ፡፡”** (አል'በቀራ፡ 102)

አላህ ያን ጊዜ ኢራቅ ውስጥ በምትገኝ ባቢል የተባለች ምድር ድግምትን በማስተማር በሁለት መላኢካዎች ሰዎችን ፈትኗል፡፡ ከእነርሱ አላህ ነጻ እንዲወጣ ያደረገው በኢማን ስኬታማ ይሆናል ፣ ከክህደት ይድናል፡፡ ለእነርሱ ተገታች ሆኖ በድግምት እውቀት የተፈተነው በክህደት እድለ ቢስ ይሆናል፡፡ ሁለቱ አስተማሪዎች በማስተማራቸው ቅጣቱ የበለጠ ይጨምራል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ አስተማሪውም ተማሪውም ፈተና ውስጥ ይወድቃሉ፡፡

በተጨማሪ ባቢል የተባለችው አገር አላህ ነምሩድ የተባለውን አመጸኛ ግለሰብ ያሰመጠበት አገር እንደሆነ ከአንድ የቁርኣን ተንታኝ ተዘግቧል፡፡ ባቢል በሚል ስያሜ የተጠራችበት ምክንያት የነምሩድ ህንጻ በሚፈርስበት ጊዜ ከድንጋጤ የተነሳ ምላሶች (ተናጋሪዎች) ግራ ስለተጋቡ እና ስለተከፋፈሉ እንደሆነ በተጨማሪ ተዘግቧል፡፡

ባቢል የድግምት እና የመደርመስ አገር እንደሆነች ከዚህ በፊት ባሳለፍነው ትምህርት ተገንዝበናል፡፡

- **በባቢሎን ውስጥ ተንሰራፍተው ከሚገኙ የጣዖት እና የአረማውያን ልብ ወለድ እምነቶች ጉልህ ከሆኑት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡**

የተፈጥሮ ክስተቶች ከአምላካዊ ሀይሎች ጋር ግንኙነት አላቸው ፤ ችሎታቸውን በተፈጥሮ ክስተቶች ላይ ተጽእኖ የማሳደር አቅም አለው፡፡ እርሷም በድግምት ትታገዛለች ብለው ያምናሉ፡፡ እነዚህ ከአምልኮታቸው መሰረቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ከእነርሱ ዘንድ ቁጥር አንድ የሐይማኖት ሰው ደጋሚ ነው፡፡ ሁለተኛው ኮከብ ቆጣሪ እና ሟርተኛ ነው፡፡

የስነፈለክ ጥናትና የኮከብ ቆጠራን ተጽዕኖ ያቋቋሙት እና የመሰረቱት ባቢሎናውያን እንደሆኑ

ብዙ የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ። በሰዎች ተፈጥሮ ላይ ተጽዕኖ እንዳላቸው በማመን እና እጣ ፈንታቸውን በመተንበይ በሰማይ አካላት ላይ ማስታወሻ ለመያዝ ይንከባከቡ ነበር።

በዚህ ምክንያት በባቢሎን ምድር ካገኙዋቸው ጽላቶች አብዛኞቹ አጋንንትን በማባረር ፣ የማይታዩትን ትንበያዎች እናውቃለን ፣ እንጠነቁላለን ፣ የሰማያትና የምድር መልካም ተስፋዎችን እናውቃለን በሚል ሽፋን በእርሷ ላይ ጠልሰም ፣ ሚስማራዊ ፊደላቶች ፣ ድግምታዊ ዘየዎች ተጽፈው እናገኛቸዋለን። ይህ የማይታየውን ስውር እናውቃለን እና በአላህ የማጋራት ሙግት መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

**የባቢሎናውያንን ጥንታዊ ቅርሶች ለማነቃቃት እና ከተቀበሩበት እንዲወጡ ያደረገው ማን ነው?**

ከ (1899-1917) ጥንታዊ ቅርሶችን ለማደስ እና ቅርሶቹ በቁፋሮ እንዲወጡ እንዲሁም በባቢሎን ፍርስራሾች ላይ ለተደረጉት የአርኪዮሎጂ ቁፋሮዎች አስተዋጽዖ ለማድረግ የጀርመን የመሬት ቁፋሮ ተልእኮዎች ወደ ኢራቅ ይጎርፉ ጀመር። የባቢሎን አማልክት እንደ አንዱ ተደርጎ ይቆጠር ነበር። እናም የልኡካን ቡድኑ ከአሸዋ በታች ያለውን ጥንታዊ ቅርሶች እና ጣዖታት መቆፈር እና ማውጣት ቀጠሉ። ከዚያ በኋላ የቁፋሮ ተልእኮው ከፈርንሳይ ፣ ብሪታንያ ፣ ዴንማርክ እና ሌሎች አገሮች የልኡካን ቡድኖች መጡ። እስካሁን ድረስ ኢራቅ ውስጥ ይገኛሉ።

## 4. የጃሂልያ ጥንታዊ ቅርሶች

ጃሂልያ ሲባል የተፈለገው ፡ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ከመላካቸው በፊት የኢብራሂም ዲን ከተቀየረ በኋላ በጀዚራ ዓረባዊያን ሙሽሪኮች ያለፉበት የድንቁርና እና የጥመት ህይዎት ነው።

ጃሂልያዎች ካሳለፏቸው እምነቶች ይፋ የሆነው፡ አላህን እየተገዙ ከእርሱ ጋር ወደአላህ ያቃርቡናል ፣ ያማልዱናል ብለው ሀያኪሎችና ምስሎችን በመጥረብ ሌሎችን አማልክቶች ይገዙ ነበር።

የጃሂልያን ቅርሶች ወይም ባእድ አምልኮን ለመጀመሪያ ጊዜ በዓረብ ባህረሰላጤ ህያው እንዲሆን ያደረገው ጠማማ የሆነው **ዓምር ብን ሉሃይ አልኹዛዒይ** ነው። አምስቱን በኑህ ዘመን ሲመለኩ የነበሩ ጣዖታትን -ወድ ፣ ሱዋዕ ፣ የጉስ ፣ የዑቅ እና ነስራ- ህያው በማድረግ ለመጀመሪያ ጊዜ እንቅስቃሴ አድርጓል። አውጥቶም ለዓረብ የተለያዩ ጎሳዎች አድሏል። በአምልኮም አዘዛቸው። ትዕዛዙንም እሺ ብለው ተቀበሉት።

## የጣዖታውያን እና የቅድመ ኢስላም ጥንታዊ ቅርሶችን እንዲያንሰራሩ ማድረግ ሸሪዓዊ ብይን

ምስሉ ወይም ቅርጹ ካልተወገደ ወደዚያ ቦታ መግባትን ስለከለከሉ ጣዖቶችና ምስሎች ወደሚገኙበት ቦታዎች መሄድ አይፈቀድም። ይህ ከመጥፎ ተግባራት እንደሆነ እና ወደዚያ ቦታ መሄድ የማይፈቀድ መሆኑ ማስረጃ ነው። ለመገኘቷ ነብዩ ﷺ ማረጋገጫ ስላልሰጡ እርሷንም መውደድ አይገባም። ይልቁንም እንድትወገድ ነው ትዕዛዝ ያስተላለፉ። ወደርሷ መግባት ክልክል እንደሆነም ከነብዩ ﷺ ተግባር ጋር በተያያዘ በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ መጧል።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ በቁረይሽ ከሐዲዎች ላይ አላህ ረድቷቸው መካ በገቡ ጊዜ ወደከዕባ አቅጣጫ ተጓዙ። ጣዖቶች እያሉ ካእባ ውስጥ አልገባም አሉ። ጣዖቶች እንዲወገዱ አዘዙ። ከወጡ ጣዖቶች መካከል -እነርሱ እንደሚሞግቱት- አዝላም (የእድል መፈለጊያ እንጨቶችን) የጨበጡ የኢብራሂምና የኢስማኢል ጣዖቶች ነበሩ።

**ረሡል ﷺ የሚከተለውን ተናገሩ፥-**

"قاتلهم الله ، أما والله قد علموا أنهما لم يستقسما بها قط"

"አላህ ያጥፋቸው ፣ በአላህ እምላለሁ በእርግጥ አውቀዋል በእርሷ (ኢብራሂምም ይሁን ኢስማኢል) አንድም አድሎን እንዳልፈለጉ።" *(ቡኻሪ፡ 1601)*

ወደካዕባ ገቡ ፣ በየአቅጣጫው አሏሁ አክበር አሉ ፣ በትክክለኛ የቡኻሪ ሐዲስ እንደመጣው በውስጡ ሶላት አልሰገዱበትም።

በተጨማሪ ረሡል ﷺ ምስል በሚገኝበት ቤት ውስጥ አይገቡም ነበር። የአላህ መልእክተኛ የምስል ባለቤቶችን የቂያማ ቀን እንደሚቀጡ ዝተውባቸዋል።

"إن البيت الذي فيه الصور لا تدخله الملائكة"

"ምስል ያለበት ቤት ውስጥ መላኢካ አትገባም።" *(ቡኻሪ፡ 2105, ሙስሊም፡ 2107)*

ይህ ሐዲስ -ለመመልከት እና ለመጎብኘት እንኳ ቢሆን- ጣዖትና ምስል ወደሚገኝበት ቦታ መሄድ እንደማይፈቀድ ማስረጃ ነው። አብዛኞቹ ሙዚየሞች ደግሞ ከእስልምና በፊት እንደአምላክ የሚመለከቷቸው ወይም ሊከበሩ የሚችሉ እንደ ንጉስ አድርገው የሚቆጥሯቸውን አካላት ሐውልቶችን ያስጎበኛሉ።

መተግበሩ እና መያዙ ሀራም የሆነ ነገር ፣ መመልከቱም ፣ መጎብኘቱም ሀራም ይሆናል። ምክንያቱም አንድን ነገር ጠልቶ በመመልከት እና በመደነቅ ደስታን ማግኘት ሁለቱ ይቃረናሉ። ምስሎችንና ጣዖቶችን መመልከትም እነርሱን ለመጠበቅና ለመንከባከብ አጋዥ የሆነ ስልትና ዘዴ ነው። በተለይም ወደአንዳንድ ሙዝየሞች ለመግባት ክፍያ ይጠይቃሉ። የሚከፈለው ገንዘብ ቅርሶችን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ምንም ጥርጥር የለውም። እነዚያን ጥንታዊ የጣዖት ቅርሶች መንከባከብ እና እነርሱን ለመጠበቅና ለማስቀጠል መርዳት ነው።

**ከእስልምና በፊት የነበሩ የጣዖት ቅርሶችን በቱሪዝምና በጉብኙት መልክ እንዲያንስራሩ ማድረግ በሸሪዓ የተከለከለ ነው። ክልክልነቱ ጣዖቶቹ ባሉበት ቦታም ይሁኑ ወይም በሙዝየሞች ፣ ወይም በቤተመቅደሶች ወይም በማንኛውም ቦታ የሚያካትት ነው።**

ጃሂልያ የሚለው ቃል የዓረብ ባህረ ሰላጤ ውስጥ የነበረውን የድንቁርና እና የማታለል ሁኔታ ተፈልጎበት ከሆነ ጥቅል በሆነው ትርጉሙ የፈርዖንና ፣ የባቢሎናውያንን እና የፊይኒቅያ ጥንታዊ ቅርሶችን ሁሉ ያካትታል።

እነዚህ ከመለኮታዊ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ጥንታዊ ቅርሶች ናቸው። ስለዚህ ማንኛውም ከነብዩ ﷺ ተልእኮ በፊት የተከሰቱ ጥመቶች እና ክህደቶች ጃሂልያ በመባል ይጠራሉ።

በአርኪዮሎጅ ጥናት መሰረት የቅርስ ቁፋሮና አወቃወሮችን በዘመናዊ መልኩ ማደራጀት የምእራባውያን ሳይንስ ብቻ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። በዚህ ላይ ሙስሊሞች ትኩረት

አላደረጉም ፤ ይልቁንም አንገብጋቢም ስላልሆነ ቸል ብለውታል።

ሙስሊሞች **"አሳር"** በማለት በስድ የሚናገሩት የነብዩን ንግግር ፣ ድርጊት እና ከህይዎታቸው የተውጣጡ ታሪኮችን ነው። በዚህ መሰረት የመልእክተኛውን ሱና እና የሷሊሆችን ደጋግ የቀድሞ አባቶችን ንግግር የሰበሰቡ ኪታቦች የ "አሳር ኪታቦች" ናቸው።

የቋንቋ ሊቃውንት የ"አሳር"ን ትርጉም በተለጠጠ መልኩ ያቀርቡታል። እርሱም የጥልቅ እውቀት ባለቤቶች ንግግሮች ፣ ተግባሮች እና የዲን እንዲሁም የዱንያ ታሪኮቻቸው የሚጠናበት የእውቀት ዘርፍ በማለት ይገልጹታል።

**ከሁለት መቶ አመታት በፊት አርኪኦሎጂ ከሚለው ቃል የምንገነዘበው ይህ ነው፡**

አርኪዮሎጂ እንደ ገለልተኛ ሳይንስ መመስረትን በተመለከተ ቅድመ ሁኔታዎቹ ፣ መሳሪያዎች ፣ ንድፈ ሐሳቦች እና በዘመናዊ ቃል ከሚታወቁ የሰው ልጅ ሳይንሶች መካከል መፈረጁ ፣ ከምዕራቡ ዓለም ፈጠራዎች አንዱ ነው።

የመነጨው እና የተመሰረተው በእነርሱ ነው። በሙስሊሞች ቤት ሳይቀር ተረክበው ከፍተኛውን ቦታ ያገኙበት ፣ ደራሲዎቻቸውም ጽሑፎችንና ደብዳቤዎችን ያጠናቀሩበት ነው። እርግጥ ነው ፣ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ፣ በሙስሊሞች ፍላጎትና ቅርሶችን በተመለከተ በሚኖራቸው ግብ እና ስለ ጥንታዊ ቅርሶች የምእራቡ አለም የሚያደርገው ጥናትና እነሱን እንደ ስልጣኔ በመቁጠር መካከል ያለው ሰፊ አለመግባባት ምን ያህል እንደሆነ ግልጽ ይሆናል።

ሙስሊሞች በጊዜው ተንሰራፍቶ የነበረውን የፍጡራን ባርነት በመዘንጋት ምድራቸው የደበቀውን ግንብ ፣ ምሽግ ፣ ምስል ፣ ሀውልት እና ሌሎችም ከነሱ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ቅርሶች የስልጣኔ መለኪያ ማድረጋቸው በጣም ያሳዝናል።

እስልምና የመጣው ጣዖታትን ለማፍረስ እና ለመሻር ነው። ሰውን ከፍጡር አምልኮና እስራት ነጻ ለማውጣት ነው። ይህ ነው ሀሳቡን ለማበልጸግ ፣ ጠቃሚ ሳይንሶችን ለማስፋፋት ፣ ሰዎችን ለማስተማር ፣ ድህነታቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን ለመሙላት እና የአዕምሮ ሰላም እና የህይወት

ደህንነት ለመስጠት ትክክለኛው እስልምና ዋስትና የወሰደለት ነጻነት።

በዚህ ምክንያት የጥንት ጣዖት አምላኪዎችና ቅድመ እስልምና ሀውልቶች ድንቁርና እስኪስፋፉ ፣ ኋላ ቀርነት እስኪፈጠርና ጥመት እስኪሰፍን ድረስ የሰው ልጅን የሚጎዱ የእምነት ልዩነቶች ፣ ቅርጾች እና የተለያዩ መልኮችን ያካተቱ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ኢስላማዊው ማህበረሰብ በስልጣኔ ጊዜ ጠቃሚ እውቀትን ይዞ ብቅ ይላል። በውስጡ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች በተለያዩ ሙያዎች ይከፈታሉ ፤ ጠቃሚ ስነ-ጽሑፍም እየተበራከቱ ይሄዳሉ።

የመጣንበት ድምዳሜ የአርኪዮሎጂ ሳይንስ መነሻው ምዕራባዊ ነው። ሙስሊሞችም ምእራባዊያን ኦሬንታሊስቶች ከሚወረውሩት ጽንሰ ሐሳብ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም በሚለው ነው።

ታሪክ የአርኪዮሎጂ የጀርባ አጥንት እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን ከዚህ በመነሳት የታሪክን እውቀት ለማሳነስ ወይም ለመካድ እና ለማስጠንቀቅ ሳይሆን ታሪክ እንደሚታወቀው ተተኪውን ከቀደምት ጋር ለማስተሳሰር መሳሪያ ነው። የብሔሮች ታሪክ አስፈላጊ ነው። **“ባለፈው የሌለው ፣ የአሁኑም የለውም”** እንደሚባለው።

ታሪክ ፡ ጥቅሙ ብዙ ፣ አላማው የተከበረ ጥበብ ነው። ታሪክ በዚህ ዓለም ያለውንም ይሁን የወዲያኛውን ሁኔታ ፋይዳው እንዲሟላ አላማ ለሚያደርግ አካል ስለአለፉ ህዝቦች ስነምግባር ፣ ስለነብያቶች ታሪክ ፣ ንጉሶችን ስለግዛታቸው እና ስለፖሊካቸው እንድናውቅ ያደርጋል።

**ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያህ ﷺ የሚከተለውን ተናግሯል ፡**

*"ينبغي للعقلاء أن يعتبروا بسنة الله وأيامه في عباده، ودأب الأمم وعاداتهم"*

*“በአላህ በባሮች ላይ ያለውን ሱናና ቀናቶች ፤ የአህዛብን ተግባር እና ልማዶቻቸውን ማጤን ለዓቅለኞች ይገባል።”*

ታላቁ አምላክ ለሙስሊሞች አእምሯቸው ስለታማ የሚያደርግ እጅግ በጣም ጥሩ ታሪክና የሰው

ልጅ ምርጥ የሆኑትን የነብያችንን ሙሀመድን ህይወት እና የተተኪዎቻቸውን የህይወት ታሪክ እና ከነሱ በኋላ አኢማዎችን ፣ የህፊዞችን ፣ መሪዎችን ፣ ድል አድራጊዎችን እና የተከበሩ ኡለሞችን ህይወት የሚተርክ ታሪክ አጎናጸፏቸው።

ይህን ያደረገው ከታሪካቸው ፣ ከስነምግባራቸው ፣ ከትዕግስታቸው ፣ ከትጋታቸው ፣ ከልፋታቸው ፍሬ እንዲመገቡ እንዲሁም ሙስሊሞች ያልተወገዱበትን ለወደፊትም የማይወገዱበትን የጥቅም አዝመራቸውን እንዲያጭዱ ነው። ለዚህ ነው ታሪክ የሚፈለገው።

ዛሬ ለሙስሊሞች በክህደታቸው እና ወሰን በማለፋቸው ምክንያት ከደረሰባቸው ቅጣት አስተንትነው እና ተገስጸው ለመራቅና ለመጠንቀቅ ካልሆነ በቀር ስለጠፉ አገሮች ፣ ከእስልምና በፊት ስለነበሩ የፈርዖኖችን ፣ የባቢሎናውያን ታሪኮችን እና ሌሎች አረማውያንን ጥንታዊ ቅርሶችን በተመለከተ ምንም አያስፈልጋቸውም።

ስለቀደምት ታሪክ ፣ የጠፉ ህዝቦችን ማድነቅ ፣ በእነርሱም መኩራራትና የበላይነት ስሜት መሰማት የመጣው ለጥንታዊ ቅርሶች እውቀት ትኩረት መስጠት ይፋ መሆን ከተጀመረ ጀምሮ ነው። ይህ ነገር አልተከሰተም ሰዎች የዲን እና ትክክለኛ አቂዳ ተቃራኒ በሆኑ ነገሮች በመፈተናቸው እንጅ። ጣኦታትን ቆፍሮ በማውጣት ፣ ለአረማውያን ወገንተኝነት ማሳየት ፣ መቃብሮችን ህያው ማድረግ ፣ በእርሱም ድንበር ማለፍ ፣ እርሷን ማላቅ እና መቀደስ እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

**ሲጠቃለል ፡ ከኢስላም ውጭ በሆኑ ነገሮች ክብር መስጠት እና ወገንተኝነት ማሳየት የጃሂልያ ባህሪዎች ናቸው።**

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

"አንሷሮች ሆይ" ፤ "ሙሀጅሮች ሆይ!" በማለት የተጣሩትን ሶሃቦች በሚከተለው መልኩ መከልከላቸው ነው።

"ما بال دعوى الجاهلية" ثم قال "دعوها فإنها منتنة"

"የጃሂሊያ ጩኸት ምንድን ነው!? ከዚያም የሚከተለውን ተናገሩ "እርሷ ጥምብ ነችና ተዋት" *(ቡኻሪ፡ 4905)*

ከላይ በተገለጹት በጣዖት አምላኪዎች ወይም በጎሳ ወይም በብሄርተኛነት ወይም በዓረብነት ወይም በሰብዓዊነት መኩራት የድንቁርና ጉዳይ እንደሆነ ይቆጠራል።

ድንቁርናና ባለቤቶቹ ተወቅሰዋል። በአጠቃላይ ወደጃሂልያ የተጠጋ ሁሉ የተወገዘ ነው። የጃሂልያ ደራ ፣ የጃሂልያ ጥርጣሬ ፣ የጃሂልያ መገላለጥ ፣ የጃሂልያ ታዕዚያ ፣ የጃሂልያ ጩኸት ፣ የጃሂልያ ፍርድ ሁሉም የተወገዘ ነው።

ሙስሊሞች በጃሂልያና በህዝቦቻቸው እየኮሩ በእስልምና ያላቸውን ኩራት እና ልቅና እንዲተው አይፈቀድላቸውም። ይህ ከእነርሱ ጋር የሚስማማ አይደለም።

ምክንያቱም ይህ አላህ በኢስላም ያዋረደውን እና ሙስሊሞችን በመልካም የተካውን ጃሂልያ ህያው ማድረግ ነው የሚሆነው።

የአላህ መልእክተኛም ﷺየሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"الإسلام يعلو ولا يعلى"

"ኢስላም የበላይ ይሆናል አንጅ በአርሱ ላይ የበላይ አይኮንም" *(ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል "ሶሂህ አልጃሚዕ፡ 2778)*

ሀኪም "ሙስተድረክ" በተባለው ኪታብ የሙእሚኖች አዛዥ ዑመር ኢብን አልኸጧብ ﵁ የሚከተለውን እንደተናገረ ዘግቧል፡

*"نحن أمة أعزنا الله بالإسلام فمهما ابتغينا العز بغيره أذلنا الله"*

*"እኛ አላህ ያላቀን ማህበረሰቦች ነን ፣ ልቅናን ከእርሱ ውጭ ከፈለግን አላህ ያዋርደናል።"* *(ኢብኑ ሐባን ፊ' ስሶሂህ፡ 6564)*

**ማጠቃለያ**

- አላህ በትልቅ እና አስደናቂ እንዲሁም የሙስሊሞችን ዓቅል ስለታማ በሚያደርግ ፣

መኖሯ ቢረጋገጥ የሰው ልጆችን ለማስተካከል እና ቀጥ ለማድረግ የማትችል ከሆነችው የቀደምት የጃሂልያ ታሪክ የሚያብቃቃ የሆነ ታሪክ ለሙስሊሞች አጎናጽፏል። እርሱም ከሰው ልጆች ሁሉ በጣም ምርጥ የሆኑት ሙሐመድ ፣ እንዲሁም ምክትሎቻቸው እና ከእነርሱ በኋላ የመጡ የሙስሊም መሪዎች ፣ ሀፊዞች ፣ መሪዎች ፣ ድል አድራጊዎች እና ልዩ የሆኑ ዑለሞች ታሪክ ነው።

- ከእስልምና ውጭ በሌሎች ነገሮች መተሳሰር እና መኩራራት ፣ አላህ በእስልምና አማካኝነት ካጠፋቸው ፣ ሙስሊሞችን ከርሱ የተሻለ በሆነ ነገር እንዲተካ ካደረጋቸው የጃሂልያ ነገሮች አንዱ ነው። ጃሂልያ በሁሉም ሁኔታ ተወቃሽ ነው።

ከእስልምና በፊት የነበሩ የጣዖት ቅርሶችን -በተገኙበት ቦታም ይሁን. በሙዚየሞች ወይም በቤተመቅደሶች ወይም በሚታዩበት ቦታ- ህያው ማድረግ ፣ መጎብኘት እና መመልከት በሸሪዓ የተከለከለ ነው።

## የመቃብር እና የ "መሻሒድ" ቅርሶች

**መቃብር** ማለት ምን ማለት ነው? ፡ በቀጥታ ወይም በጎን በኩል ሟች የሚቀበርበት ቦታ ማለት ነው።

**መሻሂድ** በማለት የተፈለገው ደግሞ መቃብሮች ላይ የተገነቡ ነገሮች ሁሉ ለምሳሌ፡ ህንጻ ፣ ጉልላት ፣ ከመቃብር ከፍ ተደርገው የተሰሩ ትዕይንቶች እና ሌሎችም ናቸው።

- ***መቃብሮች እና መሻሂዶች እንዲንሰራሩ ማድረግ ሸሪዓዊ ብይኑ ፡*** በዚህ ዙሪያ ሶስት ነጥቦችን ማቅረብ ይቻላል፡ -

**የመጀመሪያው ጉዳይ፡-** በእርሷ ላይ በመገንባት ፣ ጀሶ በመቀባት እና መብራቶችን በማብራት መቃብሮችን ህያው ማድረግ፡

በመቃብሮች ላይ የተለያዩ ግንባታዎችን መገንባት ፣ መስጊድ አድርጎ መያዝ ክልክል እንደሆነ የእስልምና ኢማሞች ተስማምተዋል። መቃብር ላይ መገንባት ፣ መቃብሩን መቀባትን ሲከለክሉ እንዲሁም የተገነቡ ነገሮች እንዲፈርሱ ሲስማሙ የሸሪዓ ማስረጃዎች ላይ በመደገፍ ነው።

**መቃብር መገንባት ፣ በጀሶ መቀባት እና መብራት ማብራትን የሚከለክሉ መረጃዎች በሁለት ይከፈላሉ ፡**

**የመጀመሪያው ክፍል፡** በመቃብር ላይ መገንባት እና በጀሶ መቀባት ክልክል መሆኑን የሚመለከቱ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው ፡

1. የጃቢር ﵁ ሐዲስ ነው። የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"نهى رسول الله أن يجصص القبر، وأن يقعد عليه، وأن يبنى عليه" أخرجه مسلم في صحيحه

"ቀብር በጀሶ መቀባት ፣ በአርሱም ላይ መቀመጥን ፣ በአርሱም ላይ መገንባትን የአላህ መልእክተኛ ከልክለዋል።" *(ሙስሊም፡ 970)*

**ከዚህ ሐዲስ በርካታ ብይኖች ተወስደዋል። ከእነዚህም ውስጥ፡**

1. ነብዩ ﷺ በመቃብር ላይ ግንባታን እንዲሁም በጀሶ መቀባትን ከልክለዋል። የክልከላ መሰረቱ የሚተገብረው ሰው ሐጢያተኛ የሚሆንበት ነው።

2. **ጥቅል የሆነው ሀራምነት በሁለት ገጽታ ማየት ይቻላል፤**

**አንደኛው ገጽታ፡** አጠቃላይ የተቀበሩ አካላት ፣ የተቀበሩት ነብያት ፣ ቅዱሳን ወይም የጻድቃን መቃብር ቢሆንም ሀራም ነው ምክንያቱም ለሽርክ መዳረሻ ሰበብ ይሆናሉና።

**ሁለተኛው ገጽታ፡** በመቃብር ላይ የተገነቡ ግንባታዎች በአጠቃላይ፡ መስጊዶች ፣ ጉልላቶች ፣ የማዕዘን ምሰሶዎች ፣ መቅደሶች እና የመቃብር የግንባታ ዲንጋዮች እና ከመቃብር በላይ ከፍ ብሎ የተሰራውንና ከበላዩ የተተከለውን ሁሉ ያጠቃልላል።

**2-በነሳኢይ ሱነን ውስጥ ጃቢር ﷺ ያስተላለፈው ትክክለኛ ሐዲስ ነው ፤**

"نهى رسول الله صلى الله عليه وسلم أن يبنى على القبر أو يزاد عليه ..."

"የአላህ መልእክተኛ በቀብር ላይ መገንባትን ወይም በእርሱ ላይ መጨመርን ከልክለዋል..."

*(ሙስሊም፡ 970, ነሳኢይ፡ 2027, ቃሉ የነሳኢይ ነው)*

ከራሱ አፈረ ውጭ መጨመርን መከልከል መሆኑን የሚያስረዱ ሐዲሶችም መጠዋል። ቀብሩ እንዲታወቅ እና ውርደት እንዳይደርስበት እንዲጠበቅ ከምድር በላይ ከስንዝር ወይም ከሁለት ስንዝር በላይ ከፍ መደረግ የለበትም። በመቃብር ላይ መገንባቱን በሚከለክለው እና ስንዝር ወይም ሁለት ስንዝር መጨመሩ መካከል ምንም የሚጋጭ ነገር የለውም። ማስተካከል ሲባል ሸሪዓው ከወሰነው ከፍታ በተጨማሪነት ተገንብቶ የተገኘውን ነው።

**3-በሶሂህ ሙስሊም የሚከተለው ሐዲስ መጧል ፤ -**

"...ألا وإن من كان قبلكم كانوا يتخذون قبور أنبيائهم وصالحيهم مساجد، ألا فلا تتخذوا القبور مساجد، إني أنهاكم عن ذلك."

**የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐደስ ተናግረዋል፤-**

"...ንቁ! ከእናንተ በፊት የነበሩት የነብያቶቻቸውን ፣ የደጋግ የአላህ ባሮችን መቃብሮች መስጊዶች አድርገው ይይዙ ነበር ፤ ንቁ! መቃብሮችን መስጊዶች አድርጋችሁ አትያዙ ፤ እኔ ከዚህ አስከለክላችኋለሁ።" (ሙስሊም፡ 532)

وقوله صلى الله عليه وسلم عن الكنيسة التي وصفت له بأرض الحبشة : "أولئك إذا مات منهم الرجل الصالح بنوا على قبره مسجدا ، ثم صوروا فيه تلك الصورة ، أولئك شرار الخلق عند الله"

በሀበሻ ምድር ስላለው የቤተክርስቲያን ጉዳይ ለእርሳቸው በተገለጸላቸው ጊዜ የአላህ መልእክተኛ ﷺ የተናገሩት ነው፡- "እነዚህ ሰዎች ከመካከላቸው ደግ የአላህ ባሪያ በሞተ ጊዜ ከቀብሩ ላይ መስጊድ ይገነቡበታል። ከዚያም ያንን ምስል በውስጡ ቀረጸው (አደረጉበት)። እነዚህ ሰዎች ከአላህ ዘንድ በጣም ክፉ ፍጡሮች ናቸው።" (ቡኻሪ፡ 427)

እነዚህ ሰዎች ሁለት ፈተናዎችን ሰብስበዋል። የመቃብር እና የምስል።

እነዚህ ሁለት ሐዲሶች ወደቀብር ቂብላ አድርጎ ሶላት መስገድ ፣ በእርሱ ላይ ሱጁድ ማድረግ ፣ በመቃብሮች ላይ መስጊዶችን መገንባት ሀራም እንደሆኑ ይጠቁማሉ። ከከባድ ወንጀሎች አንዱ ነው። ይህንን የተገበረ ሰው የቂያማ ቀን ከአላህ ዘንድ በጣም ክፉ ከሆኑ ፍጡሮች አንዱ ነው።

**ቀብሮችን መስጊዶች አድርጎ መያዝ ሶስት ትርጉሞች አሉት ፤**

1. በመቃብር ላይ ሶላት የሚለው ትርጉም በእርሱ ላይ ሱጁድ ማድረግ ማለት ነው።
2. ወደቀብር ሶላትን አላማ ማድረግ ማለት ደግሞ ለሶላት እና ለዱዓ እርሷን ቂብላ ማድረግ ማለት ነው።
3. በእርሷ ላይ መስጊዶችን መገንባት፡

በመቃብሮች ላይ መስጊዶችን መገንባት ወይም ያለግንባታ ቀብሮችን መስጊድ አድርጎ መያዝ ፣ ሁለቱም ነገሮች በሸሪዓ ሀራሞች ናቸው። ከከባድ ወንጀሎች ናቸው። በበርካታ ሐዲሶች እንደመጣው ይህን ተግባር የሚፈጽም ሰው ሐጢያተኛ ነው።

**- የኢብን ዓባስ እና የዓኢሻ ﵄ ሐዲስ ነው።**

*ሁለቱም የሚከተለውን ተናግረዋል፡ ሞት በረሡል ላይ በተገኘ ጊዜ ካባ በፊታቸው ላይ መጣል ጀመሩ ፤ ሲሸፍናቸው ከፊታቸው ላይ ይገልጡታል ፤ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ የሚሰሩትን ለማስጠንቀቅ የሚከተለውነ ተናገሩ፡*

**"لعنة الله على اليهود والنصارى ، اتخذوا قبور أنبيائهم مساجد"**

**"በአይሁድ እና በነሷራ ላይ የአላህ አርግማን ይውረድ ፤ የነብያቶችን ቀብሮች መስጊድ አድርገው ያዙ"** (ቡኻሪ፡ 435፣3453, ሙስሊም፡ 531)

**ዓኢሻ ﵂ የሚከተለውን ተናገረች ፡** *"ይህ ባይሆን ኖሮ ፣ ቀብራቸው ይፋ ይሆን ነበር። ነገር ግን መስጊድ ተደርጎ ይያዛል ብለው ፈሩ።"* ሐዲሱን ቡኻሪ በሶሂህ ዘግበውታል።

ይህ አይሁዶች እና ነሷራዎች የተገበሩትን አይነት ተግባር እንዳይፈጽሙ ለኡመታቸው ከረሡል ﷺ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው። ይህ ተግባር ከዚህ ኡመት የእነርሱን ተመሳሳይ ስራ በሰራ ሰው ላይ ሁሉ የአላህን እርግማን ያመጣል።

5 - **በመቃብር ላይ መብራት የሚያበራ አካል የተረገመ መሆኑ በሚከተለው ሐዲስ መጧል ፤**

**"لعن رسول الله صلى الله عليه وسلم زائرات القبور، والمتخذين عليها المساجد والسرج"** صحيح ابن حبان

**"የአላህ መልእክተኛ መቃብሮችን የሚዘይሩ ሴቶችን ፣ በእርሷ ላይ መስጊድ እና መብራት አድርገው የሚይዙትን ረግመዋል።"** (አህመድ፡ 2030, አቡዳውድ፡ 3236, ቲርሚዚይ፡ 320, ነሳኢይ፡ 2043, ኢብን ሒባን ሶሂህ ብለውታል "አስሶሂሀ፡ 3180, አልባኒ ሐዲሱን ሰነዱ ደካማ ነው "መብራት" ከሚለው ውጭ ያለው ሶሂህ ነው ብለዋል "ኢሰላሁ አል' መሳጅድ፡ 267)

**ለሚከተሉት ምክንያቶች በመቃብሮች ላይ መብራት ማብራት የአላህ እርግማን ያመጣል ፡**

- መቃብርን ማብራት ለእርሷ ክብር መስጠት ነው፡ ክብር መስጠት ደግሞ ወደድንበር ማለፍ ይወስዳል ፣ በእርሷ ምክንያት ሰዎች ፈተና ላይ ለመውደቅ ጠንካራ መንገድ ነው።
- ከከባድ ወንጀሎች አንዱ ነው። ማስረጃው ይህን ተግባር ነብዩ ﷺ መራገማቸው ነው።

- በዚህ ተግባር ከመጁሶች ጋር መመሳሰል ነው።
- በዚህ ተግባር ያለምንም ጥቅም ገንዘብ ማባከን ነው።

**ሁለተኛው ክፍል፡** መቃብር ላይ የተገነባ ግንብ መፍረሱ ግዴታ እንደሆነ እና ከምድር ጋር መስተካከል እንዳለበት ትእዛዝ የተላለፈበት ማስረጃ፡

أوصى أمير المؤمنين علي رضي الله عنه أحد تابعين، قائلا: ***"ألا أبعثك على ما بعثني عليه رسول الله صلى الله عليه وسلم أن لا تدع تمثالا إلا طمسته ، ولا قبرا مشرفا إلا سويته"*** أخرجه مسلم في صحيحه

1-**የምእመናን ዓሚር ዓልይ ﵁ ለአንድ ታብዕይ የሚከተለውን አደራ ብሎታል፡** *"የአላህ መልእክተኛ በላኩኝ አይነት መልክት ልላክህን? ምስልን እንዳትተው የደመሰስከው ቢሆን እንጅ ፤ ከፍ ያለ ቀብር አይኖርም ፣ ያስተካከልከው ቢሆን እንጅ"* (ሙስሊም፡ 969)

በቀብር ላይ መገንባት የአላህ መልእክተኛ ﷺቀብርን ከፍ ከማድረግ በመከልከላቸውና እንዲስተካከል ካዘዙበት ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ ይካተታል። ይህን ተግባር አለማጽቃቸውም ሀራም ለመሆኑ አመላካች ነው።

2-**ሶሂህ በሆነው የሙስሊም ሐዲስ የሚከተለው መጧል ፡** ሱማማ ብን ሽፋ ﵀ የሚከተለውን ተናገረ ፡ *"በሮማ ቡርዱስ መሬት ከፈዷላ ብን ዑበይድ ጋር ነበርን። የእኛ ጓደኛ ሞተ። ፈዷላ ብን ዑበይድ እንዲቀበር እና ቀብሩም እንዲስተካከል አዘዘ። ከዚያም የሚከተለውን ተናገረ፡ "እንዲስተካከል የአላህ መልእክተኛ ሲየዙ ሰምቸ ነው"* (ሙስሊም፡ 968)

3-**የአላህ መልእክተኛ ﷺ መስጅደ ዲራርን ማፍረሳቸው** ከእርሱ የከበደ ብልሹነት በውስጡ ያለበትን ማፍረስ እንደሚቻል ማስረጃ ነው። እነርሱም ከመቃብሮች ላይ የሚገነቡ መስጊዶች እና ቁባዎች ናቸው። ምክንያቱም የአላህን መልእክተኛ ﷺ በመንቀፍ እና የእርሳቸውን ትዕዛዝ በመቃረን የተመሰረቱ በመሆናቸው ኢስላም እንዲፈረሱ እና ከመሬት ጋር እንዲስተካከል ወስኗል።

4 -**የሙእሚኖች አሚር ዑስማን ﷺ ቀብሮች እንዲስተካከሉ አዘዘ የኡስማን ﷺ ሴት ልጅ ኡሙ አምር ቀብር ሲቀር ሁሉም ቀብሮች ተስተካክለዋል።** “ይህ ቀብር ምንድን ነው?” አለ። እነርሱም “የኡሙ አምር ቀብር ነው።” በማለት መለሱለት። እንዲስተካከል አዘዘ ተስተካከለ። በትክክለኛ ሰነድ አቡሸይባ በሙሶነፉ ዘግቦታል።

5- **ኢብን ኡመር ﷺ ከቀብር ላይ ድንኳን ተደርጎ ተመልክቶ አውግዟል።** *“አንተ ልጅ ሆይ! (ይህን ድንኳን) አስወግደው ፣ ስራው ነው ጥላ የሚሆነው”* በማለት ተናገረ።

እነዚህ ዘገባዎች ሁሉ በመቃብሮች ላይ ግንባታ መገንባት ፣ መስጊድም አድርጎ መያዝ ሀራም ለመሆኑ እንደ ቀን ጠራራ የጸሐይ ብርሃን ግልጽ እና ቀጥተኛ የሆኑ ዘገባዎች ናቸው።

ያሳለፍናቸውን ሀዲሶች በትርጉም ደረጃ የሚያጠናክሩ በሱና መዛግብት ውስጥ በርካታ ሀዲሶች አሉ። ብይኑን በማብራራት በኩል በዚህ ማሳጠሩ በቂ ነው የሚል እምነት አለኝ። ሀቅን ለሚፈልግ እንዲሁም ግልጽ መረጃን ለሚፈልግ ይኼው ያብቃቃል።

**ከዚህ በፊት ያሳለፍናቸው ከሆኑ የሐዲስ እና የሰለፎች ንግግሮች የተገኙ የተወሰኑ ጥቅሞችን እና የሀራም አይነቶች በሚከተለው መልኩ ጥቆማ ማድረጉ አስፈላጊ ነው።**

1. ከመቃብር ላይ መገንባት የአይሁድ እና የነሷራ ተግባር ነው። የእነርሱ ተግባር በዚህ ኡመት ውስጥ የእነርሱ መሰል ተግባር በፈጸሙ አካላት ላይ እርግማንን ያረጋግጣል።

   ይህን ለሚያስተነትን ሰው በመቃብር ላይ መገንባት ፣ ከመጽሐፍ ባለቤቶች ጋር መመሳሰል እንዲሁም ሙታንን ማላቅ ፣ በውስጡ ከጣዖት አምላኪዎች ጋር መመሳሰል መሆኑን ያገኝዋል።

2. በመቃብር ላይ መገንባት -በአንዳንድ መሻሂዶች እና መቃብሮች ዘንድ በተጨባጭ እንደሚስተዋለው- በመቃብሮች ላይ ድንበር ለማለፍ ድልድይ ነው። ከቢድዓ እና ሽርክ ተግባራት ላይ ለመውደቅ ጥርጊያ መንገድ ይከፍታል።

3. መጀመሪያ ላይ ቁባ የመገንባት አላማው ከእርሱ ለመጠቀም ሳይሆን ፣ ሚቱን ለመጥቀም

ነበር። ግንባታው ከዚያ በኋላ ከተከሰተው ክስተት በተቃራኒ ለቋሚነት ሳይሆን ለተወሰነ ጊዜ ነበር የሚያገለግለው። በሂደት ቋሚ የሆነ ግንባታ ሆነ። መስጅዶች ፣ ቁባዎች ፣ ዛውያዎች ፣ መቃማቶች በቋሚነት መገንባት ጀመሩ። ከሟች ጥቅም ይገኛል በእርሱ መዳረስ ፤ የችግር ጊዜ የሙጥኝ ማለት ፣ ከአላህ እንጅ ከሌላ የማይፈለግን መፈለግ እና የመሳሰሉ አዳዲስ አመለካከቶች ተፈጠሩ።

4. ከመቃብር ላይ መገንባት ቢድዓ እና ጸያፍ ተግባር ነው። በሶሃቦች ዘመን መጨረሻ ላይ ከተመሰረቱ ቢድዓዎች መካከል አንዱ ነው። ከተራው ማህበረሰብ ይህን ተግባር የሚተገብርን አካል ሶሃቦች ያወግዙ ነበር።

ኢብን ዑመር ﵄ ድንኳን ከመቃብር ላይ ተደርጎ ባየ ጊዜ *"አንተ ልጅ ሆይ! አውርደው ጥላ የሚሆነው ስራው ነው"* በማለት እንዳወገዘው።

5. ከፍ ያለ ቀብር ፣ መሽሐድ ፣ ሙቀደስ የሆነ ሀውልት በአጠቃላይ ወደማላቅ እና ድንበር ወደማለፍ የሚያደርስ ሁሉ ማፍረሱ ግዴታ ነው።

6. የጣዖት አምልኮ ሁሉ መነሻው የቀብር ፈተና በመሆኑ ነብዩ ﷺ ሰዎች በእርሷ ከፈተና ላይ እንዳይወድቁ የተውሂድን ገጽታ ለመጠበቅ ወደሽርክ የሚያደርሱ መንገዶችን እና ቀዳዳዎችን ሁሉ ለመዝጋት ክልከላን አወጁ። እነዚህን መዳረሻዎች ቸል ማለት ወደትልቁ ሽርክ እና ወደተበላሸ እምነት ያደርሳል።

7. ማንኛውም ሰው መቃብሮችን መስጊድ አድርጎ መያዝ ፣ በእርሷ ላይ መብራት ማድረግ መከልከሉ የባለቤቶቿን ክብር መቀነስ ነው ብሎ እንዳይጠረጥር። ይልቁንም ይህ እነርሱን ማክበር እና ማላቅ ነው። ወደነርሱ አቅጣጫ ቀጥተኛውን መንገድ መከተል ነው።

የዚያራ አላማው በሟች ላይ ሰላም ማለት ፣ ለእርሱ ዱዓ ማድረግ ፣ ማስተንተን ፣ በሞት መመከር ፣ አኼራን ማስታወስ ነው።

8. በሸሪዓ እንደመጣው በመቃብሮች ላይ የዚያራን አደብ በመጠበቅ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። መቃብሮችን አስመልክቶ ስርዓት መጠበቅ ማለት ቢድዓዎችን ህያው ማድረግ፣

በእርሷ ላይ በመገንባት ፣ መስጊድ አድርጎ በመያዝ ሳይሆን በእርሷ ላይ ባለመቀመጥ ፤ ባለመረማመድ ፤ ቆሻሻ በእርሷ ባለመጣል ነው።

**ሁለተኛው ነጥብ፡ መቃብሮችን ምልክት አድርጎ መያዝ እና የቱሪስት መጎብኛ በማድርግ ህያው ማድረግ።**

የዚህ ነጥብ ብይኑ ካሳለፍነው ነጥብ ብይን ጋር ተያያዥነት አለው። መቃብሮችን እና መሻሂዶችን ህያው ማድረግ ነው። የሀውልት ምልክት ፣ የቱሪስት መጎብኛ አድርጎ በመያዝ መቃብሮችን እና መሻሂዶችን ህያው አድርጎ መያዝ ቢያንስ ቢያንስ በእርሷ ላይ መገንባትን እና ለእርሷም መብራቶችን ማድረግንም ያስይዛል።

በመቃብር ላይ መገንባት በእርሷም ላይ መብራት ማብራት እና ሌሎችም ወደሽርክ የሚያደርሱ ነገሮች ሁሉ ሀራም መሆናቸው ባሳለፍነው ነጥብ በማስረጃ ተብራርቷል።

**መቃብርን የአርኪዮሎጂ ምልክት አድረጎ መያዝ ሁለት አደጋዎች አሉት፡**

**አንደኛው፡** ከመቃብር ላይ መገንባት በተመለከተ ማብራሪያው ከዚህ በፊት አልፏል ፤

**ሁለተኛው፡** ለወደፊት ማብራሪያው እንደሚመጣው የሸሪዓ ተቃራኒዎችን ህያው ማድረግ ነው።

ቀብሮችን እና መሻሂዶችን የአርኪዮሎጂ ሀውልት ፣ የቱሪስት መስህብና መጎብኛ አድርጎ በመያዝ ህያው ማድረግ ለኢስላማዊ ሸሪዓ አላማዎች ተቃራኒ ነው። **መቃብሮችን የአርኪዮሎጂ ሀውልት እና የቱሪስት መስህብ መጎብኛ ማድረግ በሚከተሉት መልኩ ሀራም መሆኑን ይጠቁማል**

1. ሸሪዓችን መቃብሮችን ማላቅ ፣ በእርሷም ላይ መገንባት ፣ እርሷን በጀሶ መቀባት ፣ ይፋ ማድረግ ፣ መብራት ማብራት በመከልከል ፣ እርሷን ለማላቅ በር የሚከፍቱ ነገሮችን ሁሉ በመዝጋት ነው የመጣው። ይህ ሁሉ እርሷን ወደማላቅ የሚወስድ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።
2. **የመቃብር ጉብኝት ከሁለት ነገሮች አንጻር የሸሪዓን አላማዎችን ያፈርሳል ፤**

- በውስጡ ፋክክር ፣ የይስሙልኝ እና ውድድር አለበት። መቃብሮች ደግሞ ለዚህ የተፈቀዱ ቦታዎች አይደሉም። ምክንያቱም የዱንያ ውበት በሞት ተነስታለች ፤ ቀብሮች ከአኼራ ደረጃዎች አንዱ ነው። ቀብር የመፎካከሪያ ቦታ አይደለም።
- በውስጡ ልዩ ለሆነው የሸሪዓ ባህሪ ተቃራኒ ነው። የሙስሊሞችን መቃብሮች በመዘየር ፣ ከመመከሪያነት አላማ ውጭ ከሆነ ክልክል ከሆነው ይገባል። ከዚህ አላማ ውጭ ከሆነ ደግሞ አዲስ የተፈጠረ ነው። በሸሪዓ ተፈላጊ አይደለም።

3. ቀብሩ የሚገበኝ ቅርስ ከሆነ በእርሱ ላይ ከግንባታ እና በተለያዩ ጌጦች ከመዋብ ከፍ መደረጉ ፣ ይፋ ከመሆን ፣ በእርሱም ላይ ጽሑፍ ከመጻፍ ሰላም አይሆንም። ይህ ደግሞ የቀብርን ሸሪዓዊ ባህሪ ይቃረናል።
4. በመቃብሮች ላይ ድንበር ለማለፍ መዳረሻ ነው። ከበርካታ ቀብሮች እና መሻሂዶች ላይ እንደሚስተዋለው ከቢድዓ እና ከሽርክ ተግባራት ላይ ለመውደቅ መስመር ይከፍታል።
5. የበአል ቦታ አድርጎ ለመያዝ ፣ ወደርሷ ለመሰባሰብ እና ደጋግሞ ለመጎብኘት መንገድ ይከፍታል።
6. ከመጽሐፍ ባለቤቶች ፣ ከካህዲዎች እና ከጃሂልያ ባለቤቶች የጣዖት አምላኪ ሙሽረሪኮች ጋር መመሳሰል ነው።
7. ያለምንም ጥቅም እና በማያስመሰግን ሁኔታ ገንዘብን ለማጥፋት, እንዲሁም ለብክነት በር ይከፍታል።

**ቀብርን የአርኪዮሎጅ ህውልት አድርጎ መያዝ ሀራም ይሆናል።**

ግልጽ ከሆኑት ሀራሞች መካከል፡ ሸሪዓዊ የቀብርን ባህሪያት እንዲሁም የሸሪዓ አላማ የሆነውን ዚያራ የሚቃረን መሆኑ ነው።

ከአንዳንዶች ዘንድ ወደሽርክ የሚያደርስ ጸያፍ ተግባራት ተገኝቷል። በሸሪዓ ዚያራ የተከለከለው ከመስረቱ ዚያራ በመሆኑ አይደለም ነገር ግን ክልክል የሆነው ከቀብሩ ጋር በተጎዳኘ የሚፈጸሙ

የሽርክ መገለጫዎች ፣ የቢድዓ እንቅስቃሴዎች ናቸው። ከዚህ ተነጥሎ የሚወጣው ለሚዘይር ሰው ሸሪዓዊ ችሎታ ላለው ሰው ሙንከርን የመቀየር ወይም የማስወገድ ችሎታ ካለው መዘየር ይችላል።

**ማጠቃለያ**

የሸሪዓን ግልጽ መረጃዎች ተቃራኒ ሆኖ በመገኘቱ ከመቃብሮች ላይ የሚገነቡ መሻሂዶችን እና ዶሪሆችን አጠናክረው በሚሰሩ በሚያልቁ አካላት ላይ ሰለፎች ውግዘታቸው ብርቱ ነበር።

**ሶስተኛው ነጥብ፡ ሙስሊም መቃብሮችን እና መሻሂዶችን መጎብኘቱ**

ከሁለት ባህሪያት በማይወጣ መንገድ እንደቦታው ሁኔታ መለያየት የመቃብሮች እና የመሻሂዶች ዚያራ ብይን ይለያያል

1. **ሸሪዓዊ የሆኑ ቀብሮች፡** በእርሷ ላይ ግንባታ የሌላት እና ከሁለት ስንዝር በላይ ቀብሩ ከምድር ከፍ ይላል።

2. **ቢድዓዊ የሆነ መሻሂድ** ፤ በእርሱ ላይ መስጅድ የተገነባበት ወይም ቁባ ወይም ድንኳን ወይም ሌላም ግንባታዎች የተገነቡበት ነው።

**የመጀመሪያው ሁኔታ፡ ሸሪዓዊ የሆኑ የመቃብር ዚያራዎች ብይን**

መጀመሪያው እስልምና ላይ ቀብሮችን መዘየር ተከልክሎ ነበር ፣ ከዚያም መዘየር ተፈቀደ። አንዳንድ ዑለሞች የተከለከለበት ምክንያት ሙስሊሞች ገና አዲስ ሰለምቴዎች በመሆናቸው ፣ ወደሽርክ የሚወስደውን መስመር ለመዝጋት ሊሆን ይችላል የሚል ምክንያት ሰጠዋል። ከዚያም ተውሂድ በልባቸው ውስጥ የተመቻቸ ጊዜ ፣ ድንበር ማለፍ እና በአላህ ማሻረክ እንዳይከሰት ፣ በስርዓት ህጉ ባስቀመጠው መልኩ ፣ ልቦቻቸው ከቀብሮች እና ከቀብሮች ባለቤቶች ጋር ትስስር ሳይኖረው እንዲዘይሩ ተፈቀደ።

መጀመሪያው ላይ ክልከላው የመጣው ለወንዶችም ለሴቶችም ነበር። ከዚያም ፈቃዱ ለወንዶችም ለሴቶችም እንዲዘይሩ ሆነ። ከዚያም ክልከላው በሴቶች ላይ ጽኑ ሆነ ፣ ለወንዶች ብቻ ተፈቀደ። ምክንያቱም ሴቶች መቃብርን ሲዘይሩ ትዕግስት የላቸውም ፣ በጣም ያዝናሉ ፣ ሟቹን ያስታውሳሉ። የአላህ ጥበቡ ሆነና ከመቃብር ዚያራ ተከለከሉ። በጸጸት እና ቁጭት እነርሱ ፈተና ላይ እንዳይወድቁ ወይም በእነርሱ አማካኝነት ሰዎች እንዳይፈተኑ ለማድረግ መቃብርን ከመጎብኘት ተከለከሉ።

ሴቶችን አስመልክቶ አመዛኝ በሆነው የዑለሞች ንግግር ፣ መቃብር መጎብኘታቸው ያለምንም ገደብ ሀራም የሚለው ነው። ምክንያቱም ሀራምነቱ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው።

**ከነብዩ ﷺ የመጣው ሐዲስ የሚከተለው ነው ፡-**

**"لعن الله زائرات القبور"** صحيح ابن حبان

"መቃብር ዘያሪ ሴቶችን አላህ ረግሟቸዋል"

**በሌላ ዘገባ የሚከተለው ሐዲስ መጧል፡-**

**"لعن زوارات القبور"** حديث صحيح أخرجه الحاكم في مستدركه

"መቃብር ዘያሪ ሴቶችን ረግሟል"

**ወንዶች መቃብሮችን መጎብኘታቸው የተወደደ እንደሆነ የአብዛኛው ፉቀሀ (ዓሊሞች) ንግግር ነው። ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ሐዲስ ነው ፡**

قول النبي صلى الله عليه وسلم: **"نهيتكم عن زيارة القبور فزوروها ..."**حديث صحيح أخرجه الحاكم في مستدركه

"የመቃብሮችን መጎብኘት ከልክያችሁ ነበር ፣ (አሁን ግን) ጎብኗት"

**فعل النبي صلى الله عليه وسلم لما زار: قبر أمه ، وشهداء أحد ، ومقبرة بقيع الغرقد.**

ነብዩ ﷺ የእናታቸውን ቀብር ፣ የኡሁድ ሰማእታቶን ቀብር ፣ የበቂዕ ገርቀድ መቃብርን በመጎብኘት በተግባር አሳይተዋል።

**ሸሪዓዊ የሆነው የመቃብር ጉብኝት ሁለት ዓላማዎቹ አሉት ፡**

**የመጀመሪያው፡** ከሟቹ ጋር የተያያዘ ነው። ነብዩ ﷺ ለሶሃቦቻቸው የመቃብር ጉብኝት ስርዓትን ባስተማሯቸው መሰረት ለሟቹ ሰላምታ ማድረስ ፣ ዱዓ ማድረግ ነው።

የሚከተለውን ዱዓ እንዲያደርጉ ለሶሃቦች ያስተምሯቸው ነበር ፡

**"السلام عليكم أهل الديار من المؤمنين ، والمسلمين ، وإنا إن شاء الله للاحقون ، أسأل الله لنا ولكم العافية"** أخرجه مسلم في صحيحه.

"አስሰላሙ ዓለይኩም አህለዲያሪ ሚነል ሙእሚኒነ ፣ ወልሙስሊሚነ ወኢንና ኢንሻአሏሁ ላሒቁን ፣ አስአሉሏህ ለና ወለኩሙል ዓፊያ" *(ሙስሊም፡ 975)*

**ሁለተኛው፡** መቃብርን የሚጎበኝ በህይዎት የሚገኙ ሰዎች ጋር የተያያዘ ነው። እርሱም ሱናውን

በመከተል ፤ የነብዩን ﷺ ንግግር ተግባራዊ በማድረግ ነው ፡

"فزوروا القبور ، فإنها تذكر الموت" أخرجه مسلم في صحيحه

**የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-** "መቃብሮችን ጎብኙ ፣ እርሷ ሞትን ታስታውሳለችና" *(ሙስሊም፡ 976)*

ቀብር መጎብኘት ያስፈለገው ፡ ለመገሰጽ እና ለማስተንተን ፣ ሞትን እና አኼራን ለማስታወስ ፣ ነብይም ይሁን ወልይ ከፍጡራን አንድም በዚህ ዓለም ላይ የሚቀር አለመኖሩን ለማስታወስ ነው።

መቃብር እንዲጎበኝ ቅስቀሳ ያስፈለገበት ሚስጢሩ ይህ አንጅ ሌላ የለውም። ከዚህ ውጭ በሌላ ያመነ አላህን እና መልእክተኛውን የነቀፈ ነው።

አንድ ሙስሊም የመቃብር ጉብኝት ብይኑን እንዲሁም በእርሷ ዙሪያ ዝርዝር ማብራሪያዎችን የፈለገ ፤ ጉብኝቱ ሶስት ሁኔታዎች አሉት ፡ ሸሪዓዊ ፣ ቢድዓዊ እና ሽርካዊ ፡

**የመጀመሪያው፡ ሸሪዓዊ ጉብኝት፡** ይህ ጉብኝት ነብዩ ﷺ ለሙስሊሞች የፈቀዱት ጉብኝት ነው። ሸሪዓዊ ህጎችን እና ተውሒድን ጠብቆ ፣ እንዲሁም ቆንጆ በሆኑ ኢስላማዊ አደቦች ተሸልሞ ፣ ወደሽርክ የሚያደርሱ ነገሮችን ዘግቶ መጎብኘት ነው። ምክንያቱም የሙስሊሞች መቃብሮች ለሟቾች ቤት በመሆናቸው የተከበሩ ናቸው። ለዚህ ነው ሸሪዓዊ አዳቦች የተደነገጉት። ስለዚህ በጉብኝቱ ወቅት እነዚህን አዳቦች በመላበስ ከመዘየር በፊት ህጎቹን አጥብቆ መያዙ የግድ ነው።

**አንድ ሙስሊም ቀብር ከመጎብኘቱ በፊት አጥብቆ ሊይዛቸው ከሚገቡ የሸሪዓ ህጎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ ፡**

1. **ቀብሩ እንደበዓል ተደርጎ መያዝ የለበትም፡** ከእርሱ ዘንድ በመሰባሰብ ወይም ወደርሱ በመመላለስ ሊሆን ይችላል።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡

"لا تجعلوا بيوتكم قبورا ، ولا تجعلوا قبري عيدا ...حديث صحيح أخرجه أبو داود في سننه،

وفي رواية : "لا تتخذوا قبري عيدا" أخرجه الإمام أحمد بإسناد حسن.

"ቤቶቻችሁን መቃብሮች አታድርጉ ፤ ቀብሬን መመላለሻ አታድርጉት ..." (አቡዳውድ፡ 2042)

በሌላ ዘገባ፡ "ቀብሬን መመላለሻ (የክብረ በዓል) አድርጋችሁ አትያዙት" (አህመድ፡ 8804)

ቀብርን መስጅድ ፣ ከበአላቶች አንዱ ክብረ በአል አድርጎ መያዝ እና ለሶስቱ መስጅዶች የጉዞ ዝግጅት ተደርጎ እንቅስቃሴ እንደሚደረገው መንቀሳቀስ ወደሽርክ ከሚያደርሱ ከባድ ቢድዓዎች ነው።

1. **ቀብሮችን ለመጎብኘት ለጉዞ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ጭኖ መንቀሳቀስ አይገባም ፡** ለሶስቱ መስጊዶች ጉብኝት እንጂ ለጉዞ አስፈላጊ ነገሮችን ጭኖ መንቀሳቀስ አይፈቀድም።

**የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል ፡**

"لا تشد الرحال إلا إلى ثلاثة مساجد: المسجد الحرام، ومسجد الرسول ومسجد الأقصى"

"ወደሶስት መስጅዶች እንጅ (ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን) ጭኖ መንቀሳቀስ አይፈቀድም፡ የሀረም መስጊድ ፣ የረሱል መስጅድ እና የአቅሷ መስጊድ ናቸው" (ቡኻሪ፡ 1188, ሙስሊም፡ 827)

አንዳንድ ሰዎች የሚሰሩትን ማንቃት አስፈላጊ ነው። እንደነርሱ አባባል በታወቁ ቀናቶች ለጉዞ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ጭነው ወደነብያት መቃብሮች ይንቀሳቀሳሉ። **ከሁለት ነገሮች አኳያ ይህ ግልጽ የሆነ ስህተት ነው ፡**

1. መዲና የሚገኘው የነብዩ ሙሀመድ ﷺ መቃብር ሲቀር ፣ ወደነብያቶች የሚጠጉ መቃብሮች ሁሉ ትክክል አይደሉም። የኢብራሒምን ቀብር አስመልክቶ ይህ ነው ብሎ ለመወሰን የመጡ ትክክለኛ ዘገባዎች ባለመኖራቸው በእርሱ ዙሪያ በርካታ ውዝግብ አለ።

በዚህ ዙሪያ ከተወሩ ወሬዎች የመጨረሻው -ተቀባይነት እንዲያገኝ አንዳንድ ሙብተዲዖች ብኸታ የሚፈጥር ማስረጃ ቢያቀርቡም- "አሳሩን ሙእዶላት" (የተቆረጡ) ወደርሱ ፊት ሊያዞሩባቸው የማይገቡ ደካማ ሰነዶች ናቸው።

የነብያቶች መቃብር ተለይተው መታወቃቸው በሸሪዓ የሚያስጠቅመው ፋይዳ የለውም። ዲንን የመጠበቂያ መንገድም አይደለም። የዲን አካል ቢሆን ኖሮ ሌሎችን የዲን አካላት እንደሚጠብቀው እነርሱንም ይጠብቃቸው ነበር።

በአብዛኛው በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ የሚያቀርቡት ከእርሱ ዘንድ ሶላት ለመስገድ ፣ በእርሷ ዱዓ ለማድረግ እና የመሳሰሉ ክልክል የሆኑ የቢድዓ ተግባራት ለመፈጸም ነው።

2. አሁን በተወሳው ማስረጃ መሰረት ማንኛውም ቀብር ቢሆን ለጉዞ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ጭኖ መንቀሳቀስ አይፈቀድም። የነብዩ ቀብር ከቀብሮች ሁሉ የተላቀ መሆኑ ያለምንም ጥርጥር ይታወቃል። ረሡል ﷺ ከነብያቶች ሁሉ የተላቁ ፤ የሩሡሎች ሁሉ አለቃ ናቸው። ያለምንም ገደብ የሰው ልጆች ሁሉ በላጭ ናቸው። ይህ ከመሆኑ ጋር ሌሎች ቀብሮች ሁሉ ለሰላምታ ፣ ለመገሰጽ ፣ ሞትን ለማስታወስ እና አኼራን ለማስተንተን እንደሚጎበኙት ሁሉ ይጎበኛል።

ይህን ተግባር ከነብዩ ቀብር ላይ ሙስሊሞች የሚተገብሩት ከሆነ ከሌሎች ደጋግ የአላህ ባሮች ቀብሮች ላይ በተመሳሳይ መፈጸማቸው ደግሞ በጣም ተገቢ ነው።

**መቃብር የሚዘዩር ሰው ሊከለከላቸው የሚገቡ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው ፡**

1. ከመቃብር ላይ መቀመጥ ወይም መቃብሩን መደገፍ
2. በእርሱ ላይ መራመድ ወይም እርሱን መርገጥ
3. ስለቅርቢቱ አለማዊ ህይዎት ማውራት
4. ድምጽን ከፍ ማድረግ
5. በመቃብሩ ላይ ቆሻሻ ወይም ነጃሳ ነገሮችን መድፋት

**የኢስላማዊ ሸሪዓ ውበትን እና የሙሉነቷን መገለጫ ከሚያሟሉና ከሚጠቁሙ ክልክል ነገሮች መካከል፡**

1. የሟቾችን መኖሪያዎች ልቅና መስጠት
2. ሙስሊም በዚህ አለም ሲኖር ክብር እንደነበረው ሁሉ ሲሞትም በተመሳሳይ በቀብርም

ክብር ሊሰጠው ይገባል። ምክንያቱም መቃብሮች የሙታን መኖሪያዎች ናቸውና።

ሸሪዓዊ የቀብር ጉብኝት ማለት የተቀበረውን ማላቅ ማለት አይደለም። ጉብኝታው ከሟቹ ምንም ዓይነት ጉዳይ የለውም። መጠየቅም ፣ በእርሱ መዳረስም የለበትም። ይልቁንም ጉብኝው ለእርሱ ዱዓ በማድረግ ፣ ለእርሱ አላህ ይዘንልህ በማለቱ ሟቹን ይጠቅማል። ይህ የሽርክ እና የቢድዓ ከሆነው ዚያራ ተቃራኒ ነው።

**ሁለተኛው ባህሪ፡** ቢድዓ የሆነው የመቃብር ጉብኝት ነው፡ እርሱም ቀብሮችን እና መሻሂዶችን ከእርሷ ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል ብሎ ተስፋ በማድረግ ፣ ወደአላህ ለመቃረብ ለሶላት ፣ ከእርሷ ዘንድ ዱዓ ለማድረግ ነው። ይህ በሙስሊም መሪዎች ስምምነት ቢድዓ ተግባር ነው። ያለምንም ክርክር ሀራም ይሆናል። በተመሳሳይ መቃበሩን መሳም ፣ በእርሱ መተሻሸት ፣ በሞተው ልቅና ወደአላህ መዳረስ እና ሌሎችም ካሳለፍነው የሸሪዓ የቀብር ዚያራ ስርዓትና  ህግ የወጡት ሁሉ ሀራም ናቸው።

**ሶስተኛው ባህሪ፡ ሽርክ የሆነው የቀብር ዚያራ ነው፡** መቃብሮችን እና መሻሂዶችን አላማ አድርጎ በተለያዩ ዒባዳዎች ወደመቃብር ባለቤቶች  ለመቃረብ ፣ ዙሪያውን መጦወፍ ፣ ሀጃውን እንዲፈጽሙ ፣ ጭንቀቱን እንዲገላግሉት ወደሞተው መጠጋት ፣  መማጸን ፣ እርዳታን መጠየቅ እና ሌሎችም የጣዖት አምላኪዎች ከጣዖቶቻቸው ዘንድ የተቸገሩትን ሰዎች ከጭንቅ ለመገላገል በጣዖቶቻቸው ተስፋ እንደሚያደርጉት  ሁሉ በሞቱ ሰዎች ተስፋ አድርጎ መማጸን ናቸው። ይህ የሽርክ ዚያራ ነው፡ ውጤቱ ረሡል ﷺ ኡመታቸውን ያስጠነቀቁት የሆነው ድንበር ማለፍ ነው።

**በቀዳዳው ለመመልከትና ለመዝናናት መቃብሮችን መዘየር፡** ይህ በሸሪዓ የማይፈለግ አዲስ የተፈጠረ ድርጊት ነው። ለዚህ ማስረጃው የአላህ መልእክተኛ የእናታቸውን ቀብር ለመዘየር በፈለጉ ጊዜ የተናገሩት ሐዲስ ነው፡

"استأذنت ربي في أن أستغفر لها فلم يؤذن لي ، واستأذنته في أن أزور قبرها فأذن لي ، فزوروا القبور ، فإنها تذكر الموت"

“ከአርሷ (ከእናቴ) ይቅርታ ከመጠየቅ ጌታዬን አስፈቀድኩ ፣ ከእኔ አልተፈቀደልኝም ፤ ቀብሯን ከመዘየር አስፈቀድኩ ፣ ከእኔ ተፈቀደልኝ ፤ መቃብሮችን ዘዩሩ - አርሷ ሞትን ታስታውሳለችና።”
(ሙስሊም፡ 976)

ፍላጎታችን በሞት ለመመከር ፣ ለመገሰጽ እና ለማስታወስ ከሆነ ሸሪዓው የሚፈልገው አላማ ነው። ጉብኝቱ ለእይታ እና ለመጎብኘት ከሆነ ግን ከሸሪዓው አላማ ጋር ይጻረራል።

**ቢድዓዊ የሆነውን መሻሂድ መጎብኘት ብይኑ**

ወንዶች መቃብርን መዘየር እንደሚችሉ ማብራሪያው ከዚህ በፊት አልፏል። ነገር ግን ሸሪዓዊ የሆነው የቀብር ዚያራ ባህሪ ሲጠፋና ከመቃብር ላይ ግንብ ሲገነባ ፤ አላህን ወደ ማጋራት የሚያደርስ አንዳንድ ጸያፍ ተግባር ሲፈጸም በሸሪዓ ዚያራው ይከለከላል። ይህ ሲባል ዚያራ ከመሰረቱ ክልክል ስለሆነ አይደለም - ድንገት የገባ ሀራም እንጅ። ቀብሩ የሽርክ መገለጫዎች ፣ የቢድዓ እንቅስቃሴ መገለጫዎች ስለተቆራኘው ነው። ከዚህ ህግ ነጥለን የምናወጣው ጸያፍ ተግባርን ለማውገዝ መጥፎ ነገሮችን ለመቀየር ችሎታ ኖሮት ወደቀብር ጉብኝት የሚያደርገው ሰው ነው።

**የቢድዓ መሻሂዶችን መጎብኘት ሀራም ለመሆኑ ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡**

1. **በመቃብሮች ላይ ግንባታዎችን መገንባት በሸሪዓ ሀራም ለመሆኑ የሙስሊም መሪዎች ተስማምተዋል።** የዚህ ማብራሪያ ከዚህ በፊት አልፏል። ራሱ ሀራም ከሆነ ፣ ወደርሱ መመልከቱም ሀራም መሆኑን ፉቀህዎች (ዓሊሞች) አረጋግጠዋል።

   መጥፎን ነገር መመልከት ልክ እንደመስማት ነው። መጥፎን ነገር መስማት ሀራም እንደሆነ ሁሉ መመልከትም እንዲሁ። በዚህ መሰረት መጥፎ ነገር ካለበት ቦታ መገኘት ሀራም ነው።

2. **መሻሂዶችን መጎብኘት ሀራም ነው፡** አንዳንዴ ወደትልቁ ማጋራት የደረሰች ጸያፍ ተግባርን መመልከት ጋር ቁርኝት ያላት በመሆኑ ነው። ጉብኝቱ ሀራም የሆነው እራሷ ሀራም በመሆኗ አይደለም። እርሷ ካለችበት ቦታ የሽርክ መዳረሻዎች ድንገት በመገኘታቸው ነው። በተመሳሳይ ጎብኝዎች በቢድዓ ተግባር ላይ የሚንቀሳቀሱ በመሆኑ ነው።

3. **መሻሂዶችን መጎብኘት የመቃብር አምላኪዎችን ቁጥር ማበራከት ነው።** የሀቅ ባለቤቶች እና የባጢል ባለቤቶች የሚለዮበት መንገዶች መለያየት ነው።

**አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚተከተለውን ተናግሯል፡**

﴿قُلْ هَـٰذِهِ سَبِيلِي أَدْعُو إِلَى اللَّهِ عَلَىٰ بَصِيرَةٍ أَنَا وَمَنِ اتَّبَعَنِي وَسُبْحَانَ اللَّهِ وَمَا أَنَا مِنَ الْمُشْرِكِينَ﴾

**"ይህች መንገዴ ናት።፡ ወደ አላህ እጠራለሁ። እኔም የተከተለኝ ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን። ጥራትም ለአላህ ይገባው። እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም" በል።"** (ዩሱፍ ፡ 108)

ሌላ ምንም አይነት ጉዳይ ሳይኖረው የባለቤቶቿን ቁጥር ለማባዛት መሻሂዶችን የጎበኘ ፣ የሽርክ ተግባር ባይፈጽም እንኳ ወንጀለኛ ነው።

4. **ከሁለት ነገሮች አኳያ መሻሂዶችን መዘየር ለፈተና ይፈራል**

**የመጀመሪያው አቅጣጫ፡** በተለይም መሪ ከሆነ ጃሂሎች በእርሱ ስለሚከተሉ ሌሎች በእርሱ ይፈተናሉ። ይህ ተግባሩ በራሱ ለጉዳት ኢላማ ይሆናል።

**ሁለተኛው አቅጣጫ፡** የሚጎበኘው አካል በራሱ በሚመለከተው ነገር ፈተና ላይ ይወድቃል። በመጀመሪያው እይታው ይጠላዋል ፣ ከዚያም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ቀልቡ መጥፎ ነገሮችን የማይጸየፍ ይሆናል። ምክንያቱም ቀልብ ንጹህ ከሆነች መጥፎ ነገር ሲከሰትባት ትጨናነቃለች። በተደጋገመ ቁጥር የማይቃወመው ከሆነ ከመጥፎ ነገር የማይሸሽ ተፈጥሮው ደደብ ይሆናል።

**ይህን** ጉዳይ ሙህዲሱ ኢብን ኑሀስ ﷺ "ተንቢሁል ጋፊሊን" በተባለው ኪታቡ ገጽ (105) እንደሚከተለው አንቅቶናል፡-

*"**እንዳንድ ጊዜ** መጥፎን በብዛት መመልከት የመለየትን እና መጥፎ ነገሮች ሲተገበሩ የመቃወሙን ብርሃን ልቦና ይነጠቃል። ምክንያቱም መጥፎ ነገሮችን በልብ ላይ በበዛና በመጣ ጊዜ እንዲሁም በአይን መመልከቱ ከተደጋገመ ከልቦች ውስጥ አንድ በአንድ ልቅናዋ ይወገዳል። የሰው ልጅ መጥፎው መጥፎ መሆኑ መመልከት ትዝ አስከማይለው*

*ደረሰ። ተደጋግሞ ስለተከሰተ እና ልብ እርሱን ስለለመደው ወንጀል ነው ብሎ አይመለከተውም።"*

5. በጃሂልያ ጊዜ ሲያመልኳቸው ከነበሩት ጣዖቶች አንዱን ጣዖት ፣ ወይም ከበአላቶች መካከል አንዱን በአል ባለበት ውስጥ የሚገኙ መሻሂዶችን መጎብኘት በቁርጥ የተከለከለ ነው። ለዚህ ማስረጃው በነብዩ ﷺ ዘመን አንድ ሰው ቦዋና በሚባል ቦታ ግመል ለማረድ ተስሎ ወደርሳቸው መጣና **"እኔ ቡዋና በሚባለው ቦታ ግመል ላርድ ተስያለሁ።"** አላቸው። "ከጃሂልያ ጣዖቶች የሚመለክ ጣዖት በቦታው አለን?" በማለት ጠየቁት። **"የለበትም"** አሉ። "በውስጡ ከበዓላታቸው አንዱ በአል አለን" አሉ ፤ **"የለም"** አሉ። "ስለትህን ሙላ ፤ አላህን በመንቀፍ ስለትን መሙላት የለም ፤ የሰው ልጅ ያልያዘው በሆነ ነገርም እንዲሁ" *(አቡዳውድ፥ 3313)*

**ከዚህ በፊት ያሳለፍነው መቃብርን እና መሻሂዶችን የመጎብኘት ብይን ጠቅለል ብሎ እንደሚከተለው ይቀርባል ፤**

1. ለመገሰጽ ፣ ለማስተንተን ፣ የነብዩን ሱና ተከትሎ በሙታን ላይ ሰላም ለማለት ፣ ለእነርሱም ዱዓ ለማድረግ ከሆነ ይህ ሸሪዓዊ የቀብር ዚያራ ነው። ዚያራው ለአላህ ብሎ የተፈጸመና የረሱልን ﷺ ሱና የተከተለ ከሆነ ሰሪው ይመነዳል።
2. በሙታኖች ወደአላህ ለመቃረብ እና ሰበብ አድርገው በመያዝ ፤ በእነርሱ ዱዓ ለማድረግ መቃብሮችን እና መሻሂዶችን መጎብኘት ቢድዓዊ ዚያራ ይሆናል። ሰሪው ከኢስላም ክልል አይወጣም እንጅ በዚህ ተግባሩ አመጸኛ ነው። ለጥላቻ እና ከአላህ ቅጣት ተገቢ ነው። ተግባሩ ወደሽርክ አድራሽ መንገድ ነው።
3. ወደሙታኑ ለመቃረብ ፣ እነርሱን ለመለመን በእነርሱ ለመማጸን ፣ ህጃዎችን ለመፈጸም ፣ ወደተቀበረው ለመዳረስ አላህ እንጅ ማንም የማይችለውን ነገር ለመፈለግ ከሆነ ይህ የቀብርና የመሻሂድ ጉብኝት በቀጥታ ሽርክ የሆነ ዚያራ ይሆናል። ሰሪው ተውሂድ ኡሉሁያና ተውሂድ ሩቡብያን በማፍረሱ እንዲሁም የሚያከፍር የሆነውን ትልቁን ሽርክ በመስራቱ

ከኢስላም ይወጣል።

የመቃብር ሀውልቶችን ህያው ማድረግን በተመለከተ ታዋቂ የሆኑ የኢስላም መሪዎች የሰጡትን ብይን እና ከዚህ በፊት ያሳለፍነውን የሀራም አይነቶች እንዲሁም ክልክልነቱን የሚያጠናክር መልእክት ከመሰረታዊ ኪታብ ከ ገጽ 319 – 331 መመልከት ይችላል።

ከዓኢማዎች ከዑለማዎች ፣ ከታሪክ ምሁራኖች የተለያዩ ንግግሮችን ያነበበ በማንኛውም መልኩ በቀብር ላይ ግንብ በመገንባት ህያው የሚያደርጉ አካላትን በሀይለኛው እንዳወገዙ ይብራራለታል። ዑለሞቹ በመቃብር ላይ ግንባታ - ግልጽ ለሆነ ጥመትና ፈተና እንዲሁም ወደሽርክ የሚያዳርስ በመሆኑ - ሸሪዓዊ ብይኑ ፈርሶ ከመሬት ጋር መስተካከሉ ግዴታ እንደሆነ እና ከመቃብር ላይ መገንባት የሀራም ተግባር እንደሆነ ሁሉም ተስማምተዋል።

መቃብሮችን እና መሻሂዶችን ሀውልቶች ህያው ማድረግ ፤ ለሙስሊሞች ድክመትና ውርደት ዋናው ሰበብ ነው። ይህ አሳዛኝ እና መራራ የሆነው ተጨባጭ ክስተት ይመሰክራል።

መሻሂዶች እና ዶሪሆች ከጥመት ተጣሪዎች ፣ ከመቃብር አምላኪዎች ላት እና ዑዛ ያላገኙትን ያክል ቅዱስነትና ትኩረት አግኝተዋል። ሌላኛዋ ሶስተኛዋ መናትም የእነርሱ አይነት እድል አላገኘችም። ሁበል በጃሂልያዎች እንደነዚህ አልተጣቀመም !

ማንኛውም ሙስሊም በዓለም ከሚገኙ የሙስሊም አገሮች በአንድ አገር ላይ አይወርድም ከመቃብር አፈሮች ላይ ቁባዎችን ወይም ከፍ ያለ ግንባታ የሚያገኝ ቢሆን እንጅ ወይም -እገዛን ከአላህ እንጠየቃለን- እነርሱ ወልይ ብለው ትልቅ ክብር ከሚሰጡት ሰው ቀብር ዘንድ የተገነባ መስጊድ የሚያጋጥመው ቢሆን እንጅ። ላ ሃውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ

አረባዊ በሆነችው የሳውዲ ግዛት አላህ ለሙስሊሞች የሰጠውን ጸጋ ማስታወስና መጠቆም ተገቢ ነው።

መቃብሮችን ከፍ ከማድረግ ፣ በእርሷም ላይ ከመገንባት ምድሯንም ሰዎቿንም አጽድታለች።

በዙሪያዋ የሚከናወን ወደሽርክ የሚያደርሱ ነገሮችን በር ሁሉ ቆልፋለች። በቅድሚያ በአላህ ችሮታ። ከዚያም  ሙጀዲድ በሆነው እና በማስረጃ ሀይል ትክክለኛ ዓቂዳና ተውሂድን ያሰራጨ በሆነው ኢማም ሙሀመድ ብን አብዱል ወሀብ ﷺ ዳዕዋ ችሮታ። እንዲሁም በስልጣኑ ሀይል ተውሂድ እንዲሰራጭ ያደረገው ኢማም ሙሐመድ ብን ሰዑድ ﷺ ችሮታ - ሁለቱንም እንዲሁም እነርሱን ተክቶ ያገዘ በእነርሱ ጎዳና ላይ የተጓዘን ሁሉ አላህ ይዘንላቸው። ይህ የላቀ የሆነው ቀሪ ጸጋው ነው። በእኛ እና በሙስሊሞች በአጠቃላይ ትልቁ ጸጋ ነው። ወደዚህ ጸጋ ግዴታችን እርሷን መንከባከብና መጠበቅ ነው። በእኛ ላይ እንድትዘወትር ማመስገን ነው።

በመቃብሮች ላይ መገንባት እንዲሁም መብራቶችን ማብራት ሀራም መሆኑ በቁርዓን ፣ በሱና እንዲሁም በዑለሞች ስምምነት የተረጋገጠ ነው። ነገር ግን አንዳንድ የአህለሱና ተቃራኒ የሆኑ አካላት የእነርሱን ሀራም ተግባራት ለመከላከል በነብዩ ﷺ መስጊዶች ዙሪያ ብዥታን ይቀሰቅሳሉ።

**ማጠቃለያ**

**በጥቅሉ ቅርሶች በአይነቷም ይሁን በብይኗ መለያየት ከሚከተሉት ሁኔታዎች አትወጣም ፡**

**አንደኛው ሁኔታ፡ ህያው መደረግ ያለባቸው ቅርሶች ናቸው ፤** ለሚከተሉት አላማዎች ሸሪዓው ለይቶ አስቀምጧቻቸዋል ፡

1. **በእርሷ አላህን ለመገዛት እና በእርሷም ወደአላህ ለመቃረብ የሚያገለግሉ ናቸው።** ምሳሌ፡ የተዘገቡ የነብዩ ﷺ ሀዲሶች ናቸው
2. **ለመገሰጽ ፣ ለማስተንተን እና አኼራን ለማስታወስ** ጥቅል በሆነ መልኩ ቀብሮችን መዘየር ለምሳሌ በተለየ ሁኔታ የነብዩን ﷺ እና የሁለቱን ጓደኞቻቸውን ቀብሮች መጎብኘት። ምንም አይነት የጉዞ ጣጣ ሳይኖር በቂዕ የሚገኙ ቀብሮች ፣ ኡሁድ የሚገኙ ሰማዕታቶችን መጎብኘት።

**ሁለተኛው ሁኔታ፡**

**ህያው እንዲደረግ የተረጋገጠ ማስረጃ ያልመጣባቸው ቅርሶች ናቸው።**

በሸሪዓ ልዩ ደረጃ ያልተደረገላቸው ፤ እንኳን ለእነርሱ ጉዞ የተለያዩ ዝግጅቶች ሊደረግ ቀርቶ በአምልኮም ይሁን በጉብኝት ምንም የሚታሰቡ ያልሆኑ ቅረሶች ናቸው። ምሳሌ

- የነብያት ቅዱሳን ቦታዎች ቅርስ
- ከእስልምና በፊት የነበሩ የጣዖታውያን ቅርሶች
- የጠፉ ህዝቦች ቅሪት ቅርሶች
- ቢድዓዊ የሆኑ የመሻሂድ ቅርሶች ናቸው።

## ቅርሶችን ህያው ማድረግ የሚያስከትላቸው የዓቂዳ ተቃርኖዎች

ከሁለት ነገሮች በአንዱ አይወገድም፡

**የመጀመሪያው፡** ቅርሱን ህያው ከማድረግ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ተቃርኖ ነው። ዛፍም ይሁን ፣ ዲንጋይ ወይም የአንድ ሰው ቅዱስነት፡

**ሁለተኛው፡** ቅርሶችን ከሚጎበኘው አካል ጋር ተያያዥነት ያለው ተቃርኖ ነው።

**የመጀመሪያው ጉዳይ፡** ቅርሱ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው ነው። ለምሳሌ፡ እርሱን ማነቃቃት ወይም በእርሱ ትኩረት መስጠት። በእርሱ ላይ በመገንባት ፣ ውበት በመስጠት ፣ መብራቶችን በማብራት እና እርሱን ወደማላቅ እና ቅዱስ ወደማድረግ የሚያደርሱ በሆኑ ሌሎች ነገሮች ውበት መስጠት ናቸው።

**ሁለተኛው ጉዳይ፡** ቅርሶችን ከሚጎበኘው አካል ህያው ማድረግ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው። ከእርሱ ፍላጎት እና ከጉብኝቱ አላማ ጋር የተያያዘ ነው። ከዚያ ቅርስ ዘንድ ከጎብኝው የሚከሰቱ ንግግሮች ፣ ተግባሮች ፣ አካሄዶችና አመለካከቶች ናቸው።

**ከጎብኝው ፍላጎትና አላማ ጋር የተያያዘው ከሁለት ባህሪያት በአንዱ አይወገድም፡**

1. የጎብኝው አላማ ለመዝናናት ፣ ለቱሪስትነት ሊሆን ይችላል። ከቅርሶች አይነት ጋር በተያያዘ የተሰጠውን ብይን እና ማብራሪያ አሳልፈነዋል።
2. ቅርሱን የሚጎበኘው ሰው አላማ አምልኮ ወይም ወደአላህ መቃረብ ሊሆን ይችላል። በዚህ ዙሪያ ተቃርኖው የበረታ ነው። ከእርሷ በርካታው የተውሂድን መሰረት ወይም ሙሉነቷ የሚቃረን ቢድዓ ወይም የሽርክ ተግባር ከመሆን አይወገድም።

ዒባዳ መሰረቱ -ሸሪዓዊ ለመሆኗ ትክክለኛ መረጃ እስከሚቆምለት ድረስ- ከአላህ እና ከረሡል ﷺ በመጣው ብቻ የተገደበ እና ተአቅቦ የተደረገበት እንደሆነ ሁሉ ፣ ሁለት መስፈርቶች ካልተረጋገጡ አምልኮ ተቀባይነትን አያገኝም።

እነርሱም፡

1. አምልኮን ፍጹም ለአላህ ብቻ ማድረግ

2. ነብዩን ﷺ ብቻ ተከትሎ መተግበር

**ነብዩን ለመከተል የግድ ሁለት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው ፤**

1. በስራው ቅርጽ ተከታይ መሆን

2. በአላማውና በግቡ መከተል

**በዚህ ህግና መርሆ ላይ ሰዎች በአራት ይከፈላሉ።**

1. **ሱንይ የሆነ የተውሒድ ሰው፡** ለአላህ አጥርቶ የሚያመልክ ፣ የረሡልን ሱና የሚከተል፡

2. **ሙብተዲዕ፡** የረሡልን ሱና ሳይከተል ስራውን ለአላህ ብሎ የሚሰራ

3. **ሙሽሪክ፡** ስራውን ለአላህ ብሎ አጥርቶ የማይሰራ፤

4. **ሙብተዲዕ ሙሽሪክ ፤** ረሱልን አይከተልም ፣ ስራውንም ለአላህ ብሎ አይሰራም።

**አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿قُلْ إِنَّمَا أَنَا بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَى إِلَيَّ أَنَّمَا إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَاحِدٌ فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاء رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا﴾

**"እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወርድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ። የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው ፤ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ" በላቸው።** *(አል'ከህፍ ፡ 110)*

አንድ ባሪያ አምልኮቱን ፍጹም ለአላህ ብሎ በመፈጸም እና የረሡልን ﷺ ሱና በመከተል ካልሆነ በቀር ወደአላህ መድረስ አይችልም።

እነዚህ ሁለት መርሆዎች ከተረጋገጡ እና በእነርሱ ከተሰራ ግለሰቡ ከተቃርኖ ሰላም ይሆናል። በእውቀት እና የነብዩን ﷺ ሱና በመከተል ላይ ሆኖ አላህን ይገዛል። ሸሪዓዊ ተቃርኖዎች ሁሉ መሰረታቸው የተውሂድን ቃል መቃረን ነው።

አብዛኛው ቅርስን ህያው ከማድረግ ጋር የተቆራኙ የዓቂዳ ተቃርኖዎች ከዚህ በፊት ካወሳናቸው ሁኔታዎች ጋር ቁርኝት አላቸው። ተቃርኖው ከቅርሱ ጋር በቀጥታ የተያያዘም ወይም ከሚጎበኘው አካል ጋር። በመሰራጨት ፣ በመከሰት ፣ በቁጥር ብዛት እና ግልጽ በመሆን ከሚስተዋሉ ተቃርኖዎች ከፍተኛ የሆነውን የተውሂድን ቃል መቃረን ለወደፊት እንመለከተዋለን። ከበርካታ ጉዳዮች ጋር ትስስር ያላቸው ከእርሷ የሚከሰቱ ሌሎች ተቃርኖዎችም አሉ።

ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

1. **ተበሩክ**
2. **ተወሱል**
3. **ሌሎች የአምልኮ ተግባራቶች ናቸው።**

## የተውሂድን ቃል መቃረን

**የተውሒድ ቃል፡ "ላኢላሃ ኢልለሏህ"** ፣ የኢስላም መሰረት ስትሆን ፣ ትርጉሟ ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም ማለት ነው።

በውስጥ ያቀፈችው መልእክት ፡ አላህ ብቻ እንጅ ሌላ አካል ላይመለክ ነው። በአምልኮ ፣ እገዛን በመፈለግ ፣ በመውደድ ፣ በማላቅ ፣ በመፍራት ፣ ተስፋ በማድረግ ፣ በማላቅ ፣ በማክበር ልቦች የሚያመልኩት አምላክ እርሱ አላህ ብቻ ነው።

አይለመንም ፣ እገዛም አይጠየቅም ፣ የጭንቅ ሰዓት ድረሱልኝ አይባልም ፣ ጠብቀኝ አይባልም አላህ ብቻ እንጅ። በእርሱ ላይ እንጅ አይመኩም ፣ እርሱን እንጅ አይፈሩም። ምንም ሳያሻርኩ አርሱን ብቻ እንጅ ተስፋ አያደርጉም።

**አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاء رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا﴾

**"የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው ፣ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ" በላቸው።** (አል'ከህፍ፡ 110)

﴿وَأَنَّ الْمَسَاجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُوا مَعَ اللَّهِ أَحَدًا﴾

**"እንሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ።"** *(ጅን ፥ 18)*

**የተውሂድ ቃል ሸሪዓዊው መልእክት፡** ለእርሱ አጋር የሌለው ብቸኛ አምላክ ነው ብሎ ማመን ፤ በአምልኮ ብቸኛ ማድረግ ፤ ጥቅምን በማምጣትም ይሁን ጉዳትን በመከላከል ወደርሱ ብቻ ፊትን ማዞር ፣ አቻነትን ፣ ተመሳሳይነትን ከአካሉ እንዲሁም ከባህሪው ማራቆት ማለት ነው። በሙሉ ባህሪ የሚገለጽ ፤ በጌትነቱ በአምላክነቱ ሸሪክን ከእርሱ ላይ ማራቆት ማለት ነው። ፈጣሪ ፣ ሲሳይ ሰጪ ፣ ህያው አድራጊ ፣ ገዳይ እርሱ ብቻ እንደሆነ ሁሉ ፣ ምንም አይነት ተጋሪ ሳይኖረው ለአምልኮ ተገቢው እርሱ ብቻ ነው።

ፍጡራንን ሁሉ የተጣራ ወይም እነርሱን የተማጸነ ወይም ልዩ ከሆነው አምልኮቱ ከፍሎ ለእርሱ ይገባዋል ብሎ ያመነ ፣ ለተውሂድ ቃል ተቃራኒ ነው። በምላሱ ላኢላሃ ኢልለሏህ ቢልም በተግባሩ በአላህ አጋሪ ነው። ከሰባቱ አጥፊ ወልጀሎች ትልቁን ፤ ከበደሎች ሁሉ ትልቁን በደል ስለፈጸመ ፣ ለፍጡራን የማይገባውን ስለሰጠ እምነቱ የተውሂድን ቃል ዓላማና ፍላጎት የሚቃረን ነው። እርሱም ሸርክ ነው።

**አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿إِنَّ الشِّرْكَ لَظُلْمٌ عَظِيمٌ﴾

**"ማጋራት ታላቅ በደል ነውና"** *(ሉቅማን ፥ 13)*

ምክንያቱም አምልኮ የአላህ ሀቅ ብቻ ነው ፤ ለእርሱ ቢጤም ተጋሪም የለውም።

**አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿وَاعْبُدُواْ اللهَ وَلاَ تُشْرِكُواْ بِهِ شَيْئًا﴾

**"አላህንም ተገዙ ። በእርሱም ምንም አታጋሩ።"** *(አን'ኒሳእ፡ 36)*

የተውሂድ ቃል እውነታ አምልኮን በብቸኛነት ለእርሱ ሳያጋሩ በማጥራት ፣ ከእርሱ ውጭ ካለ አምልኮ በመጽዳት ይገለጻል። ይህ እውነታ ወደሁለት ነገር ይመለሳል።

1. **"ላኢላሃ"** ማለት ፡ ከአላህ ውጭ አምላክነትን ሁሉ ማራቆት ማለት ነው።

2. **"ኢልለሏህ"** ማለት ፡ ለእርሱ ሳያጋሩ አምልኮን ለአላህ ብቻ ማረጋገጥ ማለት ነው።

እርሷን በማወቅ ፣ እርሷን በማረጋገጥ ፣ በግልጽም ይሁን በስውር እርሷ በምትፈልገው ላይ በመቆም ፣ እርሷን በማጥራት ፣ ከሽርክ ከቢድዓ እና ከወንጀል ቅልቅል በማጽዳት ካልሆነ በቀር ትርጉሟ አይረጋገጥም። ይህም በንግግር ፣ በተግባር እና በኒያ ኢኽላስን (አምልኮን ፍጹም ለአላህ በማድረግ) በማሟላት ነው።

ያሳለፍነውን ስናጠቃልለው፡ የተውሂድ ቃል የሚረጋገጠው ፈርድ ነገሮችን ከመተግበር ጋር ሶስት ነገሮችን በመተው ነው። እነርሱም፡

1. ሽርክን በአይነቱ መተው ፣
2. ቢድዓን በአይነቱ መተው እና
3. ወንጀልን በአይነቱ መተው ናቸው።

አንድ ሙስሊም እነዚህን ነገሮች ከተጠነቀቀ ፣ የተውሂድን ቃል ሙሉነት አረጋግጧል።

**ለተውሂድን ቃል ተቃራኒ የሆነ አካል ከሚከተሉት ነገሮች በአንዱ ላይ ይወድቃል ፡**

1. **ትልቁ ሽርክ፡** የተውሂድ መሰረት ተቃራኒ ከሆነው ትልቁ ሽርክ ወይም
2. ሙሉነቱን የሚጻረር ከሆነው ትንሹ ሽርክ ወይም
3. ተውሂድን የሚያደፈርስ ፣ ሙሉነቱን የሚከለክል እና የእርሱ አሻራ ከመገኘት እንቅፋት ከሚሆኑ ቢድዓ እና ወንጀሎች ላይ ይወድቃል።

የተውሂድን ቃል በመቃረን ተከትለው የሚመጡ ብይኖች እንደተቃርኖው አይነት ይለያያሉ። የተቃርኖው ብይን ሽርክ ወይም ቢድዓ ወይም ወንጀል ሊሆኑ ይችላሉ።

**ከተውሂድ ቃል ለመጣመም ሰበቦች**

ከተውሂድ ቃል የመጣመም ሰበቦች በርካታ ናቸው። የተቃርኖው አይነትም እንዲሁ የተለያየ ነው። የጃሂልያን የጣዖት ቅርሶች ሰዎች በማላቅ መሸወዳቸው አንዱ የተቃርኖ አይነት ተደርጎ

ይቆጠራል።

**ጎልተው ከወጡ የመጣመም ሰበቦች መካከል፡** የተውሂድን ቃል ሸሪዓዊ ፍላጎት አለማወቅ ፣ ለዚህች ታላቅ ቃል ትክክለኛ ትርጉሟን በመገንዘብ ዙሪያ - የኡሉሁያን ተውሂድ እና የሩቡብያን ትርጉም እስከመቀላቀልና አንድ አይነት ትርጉም እስከመስጠት ደረጃ የሚያደርሱ - ክፍተቶች መፈጠሩ ነው።

**"ላኢላሃ ኢልለሏህ"** የሚለውን ቃል ተፈላጊ ትርጉሙን ፈጣሪ የለም ፣ አስተናባሪ የለም ፣ መጋቢ የለም ፣ ተጋሪ የሌለው አላህ እንጅ ህያው የሚያደርግ ፣ የሚገድል የለም ብሎ ትንታኔ መስጠት ጎደሎ የሆነ ትርጉም ነው።

የተውሂድ ቃል ተቃራኒ የሆኑ አካላት አምልኮን ከአላህ ውጭ አሳልፎ ቢሰጥም አላህ ፈጣሪ መጋቢ ህያው አድራጊ ገዳይ መሆኑን ካረጋገጡ በእርግጥ ላኢላሃ ኢልለሏህ የምትፈልገውን ሁሉ እንዳረጋገጡ አድርገው ይገምታሉ። በእነርሱ አባባል የተውሂድን ቃል አልተቃረኑም። ይህ ትክክል አይደለም ፣ ይልቁንም ይህ ጥመት ነው። የመጨረሻ ጥመት።

ሙሽሪኮች በሩቡብያ ተውሂድ አረጋጋጭ ናቸው። ይህ ተውሂድ በሰው ልጆች ነፍስ ውስጥ የተረጋገጠ ነው። ከህዲም ይሁን ሙስሊም በዚህ ጉዳይ አንድም የሚከራከር የለም።

**አላህ የሚከተለውን ተናገረ፡**

﴿وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ لَيَقُولُنَّ اللَّهُ قُلْ أَفَرَأَيْتُم مَّا تَدْعُونَ مِن دُونِ اللَّهِ إِنْ أَرَادَنِيَ اللَّهُ بِضُرٍّ هَلْ هُنَّ كَاشِفَاتُ ضُرِّهِ أَوْ أَرَادَنِي بِرَحْمَةٍ هَلْ هُنَّ مُمْسِكَاتُ رَحْمَتِهِ قُلْ حَسْبِيَ اللَّهُ عَلَيْهِ يَتَوَكَّلُ الْمُتَوَكِّلُونَ﴾

**"ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው "አላህ ነው" ይሉሃል። "ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸውን (ጣኦታት) አያችሁን ፣ (ንገሩኝ) አላህ በጉዳት ቢፈልገኝ እነርሱ ጉዳቱን ገላጮች ናቸውን?፣ ወይስ በችሮታው ቢፈቅደኝ እነርሱ ችሮታውን አጋጆች ናቸውን? ፣ በላቸው። "አላህ በቂዬ ነው። በእርሱ ላይ ተመኪዎች ይመኩ" በል።** *(አዝ'ዙመር፡ 38)*

“ሽሪካ የሌለው ብቸኛው አላህ እንጅ ፈጣሪ የለም ፣ አስተናባሪ የለም ፣ መጋቢ የለም ፣ ህያው የሚያደርግ የለም ፣ የሚገድል የለም” ብሎ የሚናገር አካል በዚህ ንግግሩ ሙስሊም ሊሆን አይችልም ምክንያቱም ይህ ቃል አይሁድም ፣ ነሷራም ፣ ሙሽሪኮችም የሚጋሩበት ንግግር ነውና።

ተውሒድ አርሩቡብያን አላህ በቁርኣን ውስጥ የሚያጣቅሰው ተውሂድ አልኡሉሁያ ግዴታነቱ እንዲጸና ፣ እንዲጠናከር ፣ እንዲረጋገጥ ማስረጃ ለማድረግ ነው።

**አላህ እንደሚከተለው ተናግሯል፡**

﴿يَا أَيُّهَا النَّاسُ اعْبُدُواْ رَبَّكُمُ الَّذِى خَلَقَكُمْ وَالَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ﴾

**“እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።”** *(አል’በቀራህ፡ 21)*

በተውሂድ አር’ሩቡብያ በትክክል አረጋጋጭ የሆኑ አካላት የግድ በተውሂድ አልኡሉሁያ ማረጋገጥ ይይዛቸዋል። ተውሂድ አሩቡብያ ከአላህ ውጭ ሌሎች አካላት እንዳይመለኩ ያስገድዳል ፤ እርሱ ብቻ ፈጣሪ እንደሆነ ሁሉ እርሱ ብቻ ለአምልኮ ተገቢ መሆኑን ያረጋግጣል።

ልክ እርሱ ብቸኛ ፈጣሪ ፣ መጋቢ መሆኑን አረጋግጠው እንዳመኑ ሁሉ አምልኮንም ለሌላ አካል ሳያጋሩ ፍጹም ለአላህ ብቻ ማድረግን ያስገድዳቸዋል።

የተውሒድ ቃል ተቃራኒ የሆኑ አካላት አላህ ብቻ ፈጣሪ ፣ መጋቢ ፣ ህያው አድራጊ ፣ ገዳይ ፣ አስተናባሪ.... መሆኑን እንመሰክራለን ይላሉ። ለመፍጠር ፣ ለመመገብ ወይም ለማስተናበር ጣዖታቶች አንዳች መብት የላቸውም ፤ ነገር ግን ከአላህ ዘንድ አማካኝ ፣ አዳራሽ ወይም አማላጅ በሚል ሽፋን ወደ ተቀበሩ አካላት ፣ ወደጣኦታት ፣ ወደሀውልቶች እና ወደሌሎች አካላት ይቃረባሉ። ወደአላህ እንቃረባለን በሚል ከቅርሶች ዘንድ የተለያዩ የአምልኮ ዓይነቶችን አሳልፈው ይሰጣሉ።

ይህ አላህ በቁርኣን ውስጥ ከነፍሱ ላይ ካራቀተው የማጋራት አይነቶች አንዱ መሆኑ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም።

﴿قُلِ ادْعُوا الَّذِينَ زَعَمْتُم مِّن دُونِ اللَّهِ لَا يَمْلِكُونَ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ فِي السَّمَاوَاتِ وَلَا فِي الْأَرْضِ وَمَا لَهُمْ فِيهِمَا مِن شِرْكٍ وَمَا لَهُ مِنْهُم مِّن ظَهِيرٍ۝وَلَا تَنفَعُ الشَّفَاعَةُ عِندَهُ إِلَّا لِمَنْ أَذِنَ لَهُ حَتَّىٰ إِذَا فُزِّعَ عَن قُلُوبِهِمْ قَالُوا مَاذَا قَالَ رَبُّكُمْ قَالُوا الْحَقَّ وَهُوَ الْعَلِيُّ الْكَبِيرُ﴾

**"እነዚያን ከአላህ ሌላ (አማልክት ብላችሁ) የምታስቧቸውን ጥሩ፡፡ በሰማያትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንንም አይችሉም፡፡ ለእነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም፡፡ ከእነርሱም ለእርሱ ምንም አጋዥ የለውም" በላቸው፡፡ ምልጃም እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ እርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም"** *(ሰበእ፡ 22-23)*

**ከእርሱ ውጭ ፍጡራንን ከሚጠሩ አካላት የተገኘው የሽርክ አይነት ማብራሪያው የሚከተለው ነው**

ከንግስናው የብናኝ ክብደት ያክል (መፍጠር) አይችሉም

1. በሰማያትም ይሁን በምድር ተጋሪነት የላቸውም

2. ከእነርሱ መካከል አንድም አጋዥ እና ለአላህ ረዳት የለም

3. ማማለድም አይችሉም፡፡ (የምልጃ) ባለቤቷ አላህ ነው፡፡ እርሱ ለፈቀደው እና ለወደደው እንጅ ማማለድ አይችሉም፡፡ ከአላህ ውጭ አማላጅ አድርጎ የያዘ ሙሽሪክ ነው፡፡

**አላህ የሽርክን አይነቶች ከነፍሱ ላይ አራቁቷል፡** በባለቤትነት ፣ በሽሪካነት ፣ በረዳትነት ፣ ምልጃ ከእርሱ ፈቃድ በኋላ እንጅ እንደማትሆን፡፡

ይጠቅማሉ ይጎዳሉ የሚል እምነት የለንም ፤ አማካኝ ፣ አማላጅ ፣ ወደአላህ አዳራሽ አድርገን ያዝናቸው እንጅ አልተገዛናቸውም ፤ ስለዚህ እኛ በአላህ ላይ አላጋራንም ብለው ማስረጃ ያደረጋሉ፡፡ ይህ ሙሽሪኮች የሚያቀርቡት ማስረጃ ነው፡፡

"በቀብር ስንዞር ይጠቅማሉ ፣ ይጎዳሉ የሚል እምነት ኖሮን አይደለም ፤ የምንፈልገውን ነገር በራሳቸው ያደርጉልናል ብለን አይደለም ፤ እኛ የምንፈልጋቸው መዳረሻ እና አማካኝ እንዲሆኑን ነው" ይላሉ፡፡

**አላህ ስለነርሱ የሚከተለውን ነግሮናል፤**

﴿وَيَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللّهِ مَا لاَ يَضُرُّهُمْ وَلاَ يَنفَعُهُمْ وَيَقُولُونَ هَـؤُلاء شُفَعَاؤُنَا عِندَ اللّهِ﴾

**"ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውን ይግገዛሉ። "እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው" ይላሉ።"** *(ዩኑስ፡ 18)*

**እነርሱ የሚናገሩትንም አላህ እንደሚከተለው ነግሮናል፤-**

﴿مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَى﴾

**"ወደአላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም" (ይላሉ)** *(ዙመር፡ 3)*

እምነታቸው ጣዖቶቹ አይጎዱም አይጠቅሙም የሚል ቢሆንም ተስፋ የሚያደርጉት ግን የሚቹን ወይም የጣዖቱን ምልጃ ወይም ሽፋዓ ነው። ይህ ነው ከኡሉሁያ ሽርክ ላይ የጣላቸው። ይጠቅማሉ ይጎዳሉ የሚል እምነት ቢኖራቸው ኖሮ የሩቡብያ ሽርክ ይሆን ነበር። እነርሱን ከተገዟቸው ፣ ይጠቅማሉ ይጎዳሉ ብለው ካመኑባቸው ደግሞ ከሁለቱ ሽርክ ላይ ወደቁ። ሽርከል ሩቡብያ እና ሽርከል ኡሉሁያ። እነርሱ የሚገኙት በሽርክ እና በሁለት ሽርኮች መካከል ነው። እነርሱ በእርግጠኛነት ከትልቁ ሽርክ ላይ ወድቀዋል። የተውሂድ አልኡሉሁያን ትርጉም ያቀፈ ከሆነው - አላህ ለእርሷ ሲል መልእክተኞችን የላከበት ፣ መጽሐፎችን ያወረደበት ፣ አጠቃላይ ፍጡራንን በእርሷ ላይ የፈጠረበት ከሆነው- የተውሂድ ቃል በመቃረናቸው ከዲኑ መሰረት አዘንብለዋል።

**ኢብን አልቀይም አልጀውዝይ ﵀ "ጀዋቡል ካፊ" በተባለው ኪታቡ ገጽ (138) ስለተውሂድ ቃል የሚከተለውን ተናግሯል፤**

*"እርሷ ሰማያትና ምድር የቆመባት አጠቃላይ ፍጡራንን በእርሷ ላይ የፈጠረባት ቃል ነች። እምነቶች የተመሰረቱት ፣ ቂብላ የተመሰረተው ፣ የጅሀድ ሰይፎች የተመዘዙት በእርሷ ላይ ነው። በባሮቹ ላይ የተጣለች ጥርት ያለች የአላህ ሀቅ ነች። በዚህ አለም ደምን ፣ ገንዘብን ፣ የዘር ሀረግን የምትጠብቅ ቃል ነች። ከቀብር ከእሳት ቅጣት አዳኝ ነች። እርሷ በእርሷ ካልሆነ ጀነት*

*የማይገባበት ማህተም ነች። አጥብቆ ካልያዛት ወደአላህ የማይደርስባት ገመድ ነች። እርሷ የኢስላም ቃል ነች ፤ የሰላም አገር መክፈቻ ነች። በእርሷ ምክንያት ሰዎች ጠማማ እና ስኬታማ ተብለው ይከፈላሉ። አላህ የሚቀበለው አለ ፣ የሚባረርም አለ። በእርሷ ምክንያት የክህደት እና የኢስላም አገር ፤ የጸጋ እና የጥመት ወይም የውርደት አገር በሚል ተለዩ። እርሷም ፈርድንም ሱናንም ተሸካሚ የሆነች ምሰሶ ነች።"*

**የተውሂድን ቃል መቃረን ፍጻሜው እና እርሷን በማረጋገጥ የሚገኙ ፍሬዎች**

ባእድ አምልኮዎችና ተረት ተረት የሆኑ አዳዲስ ፈሊጦች መጥፎ ተጽኖዎች ፤ በነፍስ ወከፍም በማህበረሰብ ደረጃ አክሳሪ ፍጻሜዎች ይገጥማቸዋል።

የተውሂድን ቃል መቃረን ከሚያስከትላቸው ተጽዕኖዎችና መጥፎ ፍጻሜዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡

1. በሙስሊሙ አንድነት ላይ ድክመት ፣ ውርደት ፣ መከፋፈልና መሰነጣጠቅን ያመጣል።
2. ከአላህ ውጭ በማምለኩ ምክንያት ጭንቀት ፣ መዋዠቅ ፣ ከአጋሪው ልቦና ጋር የማይላቀቅ የዘላለም ፍርሀት ያመጣል።
3. ለአላህ ፣ ለነፍሱ እና ለሙስሊሞች ጠላት መሆን
4. ሽርኮች ፣ ቢድዓዎች ፣ ኩራፋቶች (ተረት ተረቶች) ክብር ከሚሰጡ ነገሮች አርቀው ፣ ወራዳ ወደሆኑ ማንኛውም ተግባራት ቅስቀሳ ያደርጋሉ ፤
5. በሙብተዲዕ ላይ የአላህ ቅጣት ይሰፍራል ፣ ከነብዩ ﷺ ሀውድ መራቅና ከእርሱ መጠጣትን ያስከለክላል ፤ ከትልቁ ማጋራት ላይ የወደቀ ሰው በእሳት ውስጥ ዘላለም እንዲዘወትር ያደርጋል።
6. በአላህ የሚያጋራ ሰው በነፍሱ ላይ የአላህን ፣ የመላኢካን እና በአጠቃላይ የሰው ልጆችን እርግማን ያስከትላል።

**በተቃራኒው የተውሂድን ቃል ሳይጻረር፣ እርሷ የምትፈልገውን ሁሉ ያረጋገጠ ምስጉን ተጽዕኖዎችን**

**፣ ከእርሷ ታላላቅ ፍሬዎችን ይለቅማል።**

ተውሂድ በሁለት ምንጭ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ይታወቃል። ሙስሊም ዓቂዳውን ከእነርሱ ይጎነጫል። እነርሱም ሙስሊሞች በደጋግ ቀደምቶች ግንዛቤ የዚህችን ትልቅ ቃል ዝርዝሮች ሁኔታዎች የሚያረጋግጥባቸው ኪታብ እና ሱና ናቸው።

በተጨማሪ ከሸሪዓ ማዕዘናቶች አንዱ የሆነውና በእርሷ ላይ ትክክለኛ ዓቂዳ የሚገነባበት የነብዩ ﷺ ሱና ሐዲሳዊ የዘገባ ቅርስ ሕያውነት የሚረጋገጥበት ይሆናል።

**ይህን ትልቅ ቃል በማረጋገጥ ከሚገኙ ግልጽ የሆኑ ፍሬዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡**

1. **በአላህ ገመድ መጠበቅ፡** በእርሷ የሙስሊሞች ጥንካሬ የሚረጋገጥበት ፣ በጠላቶቻቸው ላይ እርዳታና ድጋፍ የሚያገኙበት የቃል አንድነትና መሰባሰብ ይገኛል።

   **አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡**

   ﴿وَاعْتَصِمُواْ بِحَبْلِ اللّهِ جَمِيعًا﴾

   **"የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ።"** *(አል'ዒምራን፡ 103)*

2. ሰላምና ጸጥታ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ይሟላል። የነፍስ እንዲሁም የአዕምሮ መረጋጋት ይረጋገጣል። ምክንያቱም አንድ ባሪያ አንድን ጌታ ብቻ ያመልካል ፣ ፍላጎቱን ያውቃል ፣ እርሱ የሚወደውን ይሰራል ፣ የሚቆጣበትን አውቆ ይጠነቀቃል።

   **አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡**

   ﴿الَّذِينَ آمَنُواْ وَلَمْ يَلْبِسُواْ إِيمَانَهُم بِظُلْمٍ أُوْلَـئِكَ لَهُمُ الأَمْنُ وَهُم مُّهْتَدُونَ﴾

   **"እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ እነዚያ ለእነርሱ ጸጥታ አላቸው። እነሱም የተመሩ ናቸው።"** *(አል'አንዓም፡ 82)*

3. **ከፍተኛ ደረጃ ፣ በዱንያም ይሁን በአኼራ ልቅና ለተውሂድ ባለቤቶች ነው።**

   **አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

   ﴿وَمَن يُشْرِكْ بِاللَّهِ فَكَأَنَّمَا خَرَّ مِنَ السَّمَاء فَتَخْطَفُهُ الطَّيْرُ أَوْ تَهْوِي بِهِ الرِّيحُ فِي مَكَانٍ سَحِيقٍ﴾

   **"ለአላህ ታዛዦች በእርሱ የማታጋሩ ሆናችሁ (ከሐሰት ራቁ)። በአላህም የሚያጋራ ሰው**

፣ ከሰማይ እንደ ወደቀና በራሪ እንደምትነጥቀው ፣ ወይም ነፋስ እርሱን በሩቅ ስፍራ እንደምትጥለው ቢጤ ነው፡፡" (ሀጅ፡ 31)

4. አለቃነትን እና በምድር ላይ ትክክ መሆንን ያስገኛል

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡

﴿وَعَدَ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنكُمْ وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ لَيَسْتَخْلِفَنَّهُم فِي الْأَرْضِ كَمَا اسْتَخْلَفَ الَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ وَلَيُمَكِّنَنَّ لَهُمْ دِينَهُمُ الَّذِي ارْتَضَىٰ لَهُمْ وَلَيُبَدِّلَنَّهُم مِّن بَعْدِ خَوْفِهِمْ أَمْنًا يَعْبُدُونَنِي لَا يُشْرِكُونَ بِي شَيْئًا وَمَن كَفَرَ بَعْدَ ذَٰلِكَ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الْفَاسِقُونَ﴾

"አላህ እነዚያን ከእናንተ ያመኑትንና መልካም የሰሩትን እነዚያን ከእነሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ላይ በእርግጥ ሊተካቸው ፣ ለእነሱም ያንን የወደደላቸውን ሊያደላድልላቸው ፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጥላቸው ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል፡፡ በእኔ ምንንም የማያጋሩ ሆነው ይግገዙኛል፡፡ ከዚያም በኋላ የካደ ሰው እነዚያ እነርሱ አመጸኞች ናቸው፡፡" (አን'ኑር፡ 55)

5. ክብር ፣ ደም ፣ ገንዘብ እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል ፡

"أمرت أن أقاتل الناس حتى يقولوا لا إله إلا الله ، فمن قالها فقد عصم مني ماله ونفسه إلا بحقه ، وحسابه على الله"

"ላኢላሃ ኢልለሏህ እስከሚሉ ሰዎችን ልጋደል ታዝዣለሁ፡፡ እርሷን ያላት ፣ በሀቅ ሲቀር ከእኔ ገንዘቡን እና ነፍሱን ጠበቀ፡፡ ምርመራው በአላህ ላይ ነው፡፡" (ቡኻሪ፡ 1400, ሙስሊም፡ 21)

ይህ ታላቅ የሆነችውን ቃል በማረጋገጥ ከሚገኙ ፍሬዎች መካከል ጥቂቱ ነው፡፡

እንደ ተውሒድ ቃል ታላቅ ፣ ውጤቱ የላቀ ፣ ምስጉን ፍሬዎች የሚለቀምበት አንድም ነገር የለም፡፡ እርሷ የዱንያ እና የአኼራን መልካም ሁሉ የሰበሰበች ነች፡፡

ተበሩክ ሲባል የተፈለገው ምንድን ነው?

**በቋንቋ፤** ተበሩክ ማለት በረከትን መፈለግ ማለት ነው። በአንድ ነገር ተባረከ ሲባል በእርሱ አማካኝነት በረከትን - መልካም ነገር መጨመርን ፣ መራባትን እና መዘውተርን ፈለገ ማለት ነው።

**በቅርሶች በረከትን የመፈለግ ክፍሎቹና ብይኖቹ:** በረከት ከተለያዩ ነገሮች አኳያ በበርካታ ክፍሎች ይከፈላል።

**ከአይነቱ አኳያ በሁለት ይከፈላል፤**

1. **ሸሪዓዊ ተበሩክ**

በረከትን መፈለግ ፣ ከአላህ ተስፋ ማድረግ። ሸሪዓዊ በሆኑ መዳረሻዎች ፣ በተለየ አኳኋን በአካል ወይም በንግግር ወይም በተግባር ወይም በዘመን ወይም በቦታ በሸሪዓ ህግ አውጭው ፈቃድ እርሷን መፈለግ ማለት ነው።

**ምሳሌው፤** አንድ ሙስሊም ሸርዑ በፈቀዳቸው ነገሮች ውስጥ በተፈቀደው ገደብ በረከትን መፈለጉ ነው። ቁርኣን በመቅራት ወይም በረመዷን ወር አምልኮን በማብዛት እና በሌሎችም በረከትን እንድንፈልግባቸው በቁርኣን እና በሐዲስ በመጡ ነገሮች በረከትን መፈለግ ነው።

እንድ ነገር በቁርኣን ፣ በሀዲስ አምልኮ መሆኑ መረጃ ከመጣለት ፡ ዋና መስረቱ ከኢኽላስ ጋር በአላማው እና በስራው ቅርጽ ረሡልን ﷺ መከተልን ተስማምቶ መገኘት አለበት።

**ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያ** "መጅሙዕ አልፈታዋ" (1/281) ላይ በአላማ ወይም በኒያ መከተሉ ፣ በስራው ቅርጽ ከመከተል ይበልጣል በማለት ጥቆማ አድርጓል።

2. **ክልክል የሆነው ተበሩክ (በረከት)**

በረከት እንደሚገኝበት በሸሪዓ የጸደቀ የማስረጃ ድጋፍ ሳይኖረው ከአንድ ነገር በረከትን እና መልካሙን መፈለግ ማለት ነው።

ከዱንጋዩ ወይም ከዛፉ ወይም ከአንድ ግለሰብ አካል ጋር ትስስር ባለው ወይም ከአካሉ በተነጠለ ወይም ግለሰቡ ባለፈበት ቦታ ወይም በተቀመጠበት ወይም እርሱ የተቀበረበት ቦታ ላይ በረከትን መፈለግ ነው።

**ለምሳሌ፡** አንድ ሙስሊም ሸሪዓው በረከት እንደሚገኝበት ባላጸደቀው ነገር ላይ በረከትን ሊፈልግ ወይም ሸሪዓው በረከት እንደሚገኝበት ከፈቀደው ድንበር አልፎ ወዳልተፈቀደው መሸጋገር ነው። በነብያቶችና በሷሊሆች ወይም በቅዱስ ቦታዎች በረከትን መፈለግ። በቁርኣን እና በሐዲስ በረከት እንደሚገኝባቸው ማስረጃ ባልመጣላቸው ነገሮች በዱንጋዮች ወይም በዛፎች በረከትን መፈለግ።

ሸሪዓው በረከት እንደሚገኝበት ከፈቀደው ድንበር አልፎ ወዳልተፈቀደው መሸጋገር። ሸርዑ በረከት ያደረገባቸው ቦታዎችን ለምሳሌ ፡ ሶስቱ መስጅዶች ፣ የሀረም መስጊድ ፤ በዙሪያው ባሉ የአምልኮ ቦታዎች ፣ ከዕባ ፣ ጥቁሩ ዱንጋይ ፣ መቃሙ ኢብራሂም እና የመሳሰሉ ቦታዎች ላይ ድንበር ማለፍ።

**ከብይኑ አኳያ ክልክል የሆነው ተበሩክ (በረከት) በሁለት ይከፈላል**

**የመጀመሪያው ክፍል፡ ትልቁ ሽርክ ፡** ፍጡር ራሱን ችሎ በረከትን የመስጠት ፣ የመለገስ አቅም አለው ብሎ ማመን። በዚህ ምክንያት ከፍጡራን በረከትን ይፈልጋሉ። በረከት በውስጧ ይዛለች በመሆኑም ራሷን ችላ ትለግሳለች ወይም ከአላህ ዘንድ በረከት ለማግኘት አማካኝና አዳራሽ ነች ብሎ ማመን።

ከአሻራው ላይ የሚገኘውን በረከት ለማግኘት መተሻሸቱን ፣ መንከባለሉን ፣ ከሰውነቱ ጋር ማጣበቁን ከአላህ ጋር ያማልዳል ወይም ወደአላህም ያቃርባል ብሎ ያምናል። ይህ ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ ይዟል። ከኢስላም የሚያስወጣ ትልቁን ሽርክ ፈጽሟል። በረከት እናገኛለን ያቃርቡናል ፣ ያዳርሱናል ብለው ዛፉን ዱንጋዩን ቀብሩን ከሚገዙ ጃሂልያዎች ጋር ይመሳሰላል። ከእርሷ ዘንድ ይሰባሰባሉ ፤ ይተሻሻሉ። ይህ ተግባር በቀጥታ ከአላህ ጋር ሸሪካን ወይም ባላንጣን ወደመያዝ ይመለሳል።

**አላህ የእነርሱን ባህሪ በሚከተለው ቁርኣን ግልጽ አድርጎታል**

﴿مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَى﴾

**"ወደአላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም"** *(አዝ'ዙመር፡ 3)*

**ሁለተኛው ክፍል፡ ትንሹ ሽርክ**

አንድ ሙስሊም በሸሪዓ በረከት እንድንፈልግበት ባልታዘዝንበት በረከት መፈለጉ ወይም በእርሱ ውስጥ በረከት አላህ ያደረገበት መሆኑን እያወቀ ህግ ጥሶ ወዳልፈቀደው መሄድ ነው።

**ማለትም፡** አሻራዎች ወደአላህ ያደርሳሉ ያቃርባሉ እንጅ በቀጥታ በረከት ይሰጣሉ የሚል እምነት ሳይኖረው በረከት ለመገኘት ሰበብ ናቸው ብሎ ካመነ ይህ ሰው ከትንሹ ሽርክ ላይ ወድቋል። አንዳንድ ዑለሞች **"ተበሩኩል ቢድዕይ"** ብለው ይጠሩታል።

በሸሪዓ ባልታዘዘ ነገር ከአላህ በረከትን የፈለገ ወይም በረከት ለመገኘቱ ሰበብ ነው ብሎ ያመነ ለምሳሌ፡ አላህ ይንን የቀብር አፈር በረከት አድርጎበታል ብሎ በማመን አፈሩን ያዘና ከእራሱ ላይ በተነው። በሸሪዓ አላህ ሰበብ ያላደረገውን ሰበብ ነው ብሎ ከማመኑ አኳያ ይህ ትንሹ ማጋራት ይሆናል።

**የተበሩክ (የበረከት) ብይን እና የሽርክ ደረጃዎቹ ፣ በረከት ከሚፈልገው አካል አኳያ ሁለቱም ጥምረት ይፈጥራሉ ፡**

በረከት ይገኝበታል ከሚባለው ነገር አኳያ ክልክል የሆነው ተበሩክ በሶስት ይከፈላል። እነርሱም ፡

1. በነብያቶች ቅዱሳን አሻራ በረከትን መፈለግ
2. በደጋግ የአላህ ባሮች አሻራዎች እና ቅዱሳን ቦታዎች በረከትን መፈለግ
3. በዲንጋዮች ፣ በዛፎች ፣ በቦታዎች እና በመሳሰሉት በረከትን መፈለግ

**የአፈጻጸም አይነቶቹ፡** ከነብያቶች ቅዱሳን አሻራዎች ወይም ከወልዮች አካሎች ፣ ከሷሊሆች ቀብሮች ወይም ከጣዖታት ሐውልቶች በረከትን መፈለግ።

ሶላት ለመስገድ ፣ ዱዓ ለማድረግ ፣ ከእርሷ ዘንድ ለመሰባሰብ ፣ በረከተን ፣ መራባትን ለማግኘት በሚል በአፈሯ በግድግዳዋ ለመተሻሸት ስንቅና የማቴሪያል ዝግጅት አድርጎ ወደጣዖቶች መጓዝ።

በረከት ከአላህ የሚገኝ መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው። ከእርሱ እንጅ ከማንም አይፈለግም። ከእርሱ ውጭ ከአንድም አካል አይፈለግም። ለፈለገው ሰው ይሰጣል ፣ ይለግሳታል። ከፈለገው አካል ላይ ይከለክላታል።

**አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፤**

﴿تَبَارَكَ الَّذِي بِيَدِهِ الْمُلْكُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ﴾

**"ያ ንግስና በእጁ የሆነው አምላክ ችሮታው በዛ። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።"** *(አል'ሙልክ፡ 1)*

﴿وَأَوْرَثْنَا الْقَوْمَ الَّذِينَ كَانُوا يُسْتَضْعَفُونَ مَشَارِقَ الْأَرْضِ وَمَغَارِبَهَا الَّتِي بَارَكْنَا فِيهَا﴾

**"እነዚያንም ደካሞች የነበሩትን ህዝቦች ያችን ከውስጧ በረከት ያደረግንባትን ምድር ምስራቆቿንም ምዕራቦቿንም አወረስናቸው።"** *(አል'አዕራፍ፡ 137)*

﴿وَهَٰذَا ذِكْرٌ مُّبَارَكٌ أَنزَلْنَاهُ أَفَأَنتُمْ لَهُ مُنكِرُونَ﴾

**"ይህም (ቁርኣን) ያወረድነው የሆነ ብሩክ መገሰጫ ነው። ታዲያ እናንተ ለእርሱ ከሀዲዎች ናችሁን?"** *(አል'አንቢያእ፡ 50)*

﴿فَإِذَا دَخَلْتُم بُيُوتًا فَسَلِّمُوا عَلَىٰ أَنفُسِكُمْ تَحِيَّةً مِّنْ عِندِ اللَّهِ مُبَارَكَةً طَيِّبَةً﴾

**"ቤቶችንም በገባችሁ ጊዜ ከአላህ ዘንድ የሆነችን የተባረከች መልካም ሰላምታ በነፍሶቻችሁ ላይ ሰላም በሉ።"** *(አን'ኑር፡ 61)*

ከአላህ ውጭ በረከትን የፈለገ ወይም አላህ ሰበብ ያላደረገውን አሻራ ለበረከት ሰበብ ነው ብሎ ያመነ ከሽርክ ላይ ወደቀ። ምክንያቱም በረከት የሚገኘው ከአላህ ብቻ ነው። ተቆጣጣሪዋ ፣ ሰጭዋ እርሱ ብቻ ነው። ከሌላ አካል አትፈለግም።

ከሸሪዓ ማስረጃ ውጭ በአሻራዎች በረካን መፈለግ ክልክል ነው። በትክክለኛ መረጃ ካልሆነ በቀር አንድ ነገር ለበረከት መገኘት ምክንያት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም የዚህ መሰረቱ

ከአላህ የወረደው መመሪያ ወይም ሸሪዓ ነው።

በረከት የማግኛው መንገድ ሸሪዓዊ ሊሆን ይገባል። በዚህ ዙሪያ ቀደምቶች ያልሰሩትን ሁኔታ እና መንገዶችን ሊፈጥር አይገባም። በአላማም ይሁን በተግባራዊ አፈጻጸሙ ረሡልን ﷺ ተከታይ ሊሆን ይገባል። የሰለፍን መንሐጅ የሚቃረን ተግባር አይስራ ፣ አዲስ ነገር አይፍጠር።

**ሸይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያ ﵀ (መጅሙዕ አል'ፈታዋ 1/198) የሚከተለውን ተናግሯል**

*"መከተል ማለት ፡ ረሡል ﷺ በሰሩት መልክ መስራት ማለት ነው። ረሡል በዒባዳ መልኩ አንድን ተግባር ከፈጸሙ ፣ በዒባዳ መልኩ እንድንሰራው ለእኛ ተደንግጓል ማለት ነው። አንድን ቦታ ወይም ዘመን በአምልኮ ከለዩት ፣ እኛም በዚያው መልክ እንለየዋለን ማለት ነው።"*

ይህ ክልክል ለመሆኑ ማስረጃው የአቢ ዋቂድ አልለይስይ ﵁ ሐዲስ ነው። አቡ ዋቂድ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፡-

"ከረሡል ﷺ ጋር ወደሁነይን ተጓዝን። ከክህደት ወጠን አዲስ ሰለምቴዎች ነበርን ፤ በአንዲት ዛፍ በኩል አለፍን" ፤ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ ! ለእነርሱ የማንጠልጠያ ባለቤት እንዳላቸው ለእኛም የማንጠልጠያ ባለቤት አድርግልን" አልናቸው። ከሐዲዎች በእርሷ ዙሪያ የሚሰባሰቡባት ፣ መሳሪያቸውን የሚያንጠለጥሉባት የቁርቁራ ዛፍ ነበረቻቸው። **"ዛት አንዋጥ"** ብለው ይጠሯታል። "አኳሁ አክበር ! ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ የኢስራኢል ልጆች ከሙሳ የተናገሩትን አይነት ንግግር ነው ነው የተናገራችሁ" በማለት ረሡል ﷺ ተናገሩ።

﴿اجْعَل لَّنَا إِلَـٰهًا كَمَا لَهُمْ آلِهَةٌ قَالَ إِنَّكُمْ قَوْمٌ تَجْهَلُونَ﴾

**"ለእነርሱ (ለሰዎች) አማልክት እንዳሏቸው ለእኛም አምላክን አድርግልን ፤ አሉት። እናንተ የምትሳሳቱ ህዝቦች ናችሁ" አላቸው** *(አል'አዕራፍ፡ 138)*

ከእናንተ በፊት የነበሩትን ማህበረሰቦች መንገዶች በእርግጥ ትጓዛላችሁ።" *(አህመድ፡ 21897, ቲርሚዚይ፡ 2180)*

**በአቡዋቂድ አልለይሲይ ﵁ ሐዲስ ውስጥ በአሻራዎች ተበሩክ ማድረግ ሀራም የሆነበትን ምክንያት በሚከተለው መልኩ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል፡**

1. ይህ ሐዲስ በአሻራዎች በረከትን መፈለግ ሀራም ለመሆኑ መሰረት ነው። ምክንያቱም ከማንጠልጠያ ባለቤት በሆነችው በረከትን የፈለገን አካል የአላህ መልእክተኛ በከባድ ሁኔታ በማውገዛቸው ነው። ረሱል ﷺ **"አሏሁ አክበር"** በሚል ቃል ድርጊታቸውን አውግዘዋል። ይህ ብቻ አይደለም ተግባራቸውን ከበኒ ኢስራኤል ልጆች ተግባር ጋር አመሳስለውታል። ፍላጎታቸው ከባድ በመሆኑ አዲስ ሰለምቴ በመሆናቸው ይቅርታ አልተደረገላቸውም።

2. **ክልከላው የመጣው ከአሻራዎች ዘንድ መሰባሰብን በተመለከተ ነው። "ኡኩፍ"** ማለት አንድን ነገር አጥብቆ መያዝ ፣ ቦታውን በማላቅና በመቃረብ መልኩ ማዘውተር ማለት ነው።

**ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፡**

﴿مَا هَٰذِهِ التَّمَاثِيلُ الَّتِي أَنتُمْ لَهَا عَاكِفُونَ﴾

**"ይህች ቅርጻ ቅርጽ ያቺ እናንተ ለእርሷ ተገዢዎች የሆናችሁት ምንድን ናት" ባለ ጊዜ (መራነው)።** (አል'አንቢያእ፡ 52)

**"ዛት አንዋጥ"** ከምትባለው ዛፍ በእርሷ በረከትን ለማግኘት እንደተሰባሰቡ በሀዲስ መጧል።

**ዓምር ብን አውፍ** ﵁ ባስተላለፈው ሌላ ዘገባ ደግሞ ፡ የሚከተለው አለ "መሳሪያ ስለሚያንጠለጥሉባት "ዛት አንዋጥ" በሚል ስያሜ ተጠራች ፤ ከአላህ ውጭ የምትመለክ ነበረች ....."

**በሁለቱ መካከል ለማስማማት፡** በረከትን ፈልጎ ከእርሷ ዘንድ መሰባሰብ አምልኮ ውስጥ ያስገባል። ይህ ነው ሸይኽ ሱለይማን ብን ዓብዲላህ "ተይሲረል ዓዚዚል ሀሚድ" በተባለው የኪታቡ ተውሂድ ማብራሪያ ገጽ (1/230) ገለጻ ያደረጉት።

3. **ተውሂድ መጥፋቱ ፡** በዛፍ በረከትን መፈለግ ፣ እርሷንም አምላክ አድርጎ መያዝ ግልጽ የሆነ ሽርክ ነው። የአላህ መልእክተኛ ይህ እነርሱ የፈለጉት ነገር ማለትም ከእርሷ ዘንድ ለመሰባሰብ ዛፏን መያዛቸው እና በረከትን ለመፈለግ መሳሪያቸውን ማንጠልጠላቸው በኒ ኢስራኢሎች "ለእነርሱ አምላክ እንዳላቸው ለእኛም አምላክ አድርግልን" በማለት ሙሳን ከጠየቁት ጥያቄ ጋር መመሳሰሉን ግልጽ አደረጉ። በሁለቱም ፍላጎቶች ውስጥ የተውሂድ

ተቃርኖ እንዳለው ግልጽ ሆነ ማለት ነው።

4. **ሽርክ ላይ መውደቅ** ፤ ከማምለክ እና ከመጠየቅ ነጻ ሆነው በረከት ለመፈለግ ብቻ ዛፍ ላይ መሳሪያን ማንጠልጠል ፤ ከእርሱ ዘንድ መሰባሰብ ከአላህ ጋር አምላክ አድርጎ እንደመያዝ ተደርጎ ተቆጥሯል።

በቀብር አምልኮ ሙታኖችን መጣራት ፣ እነርሱን በቀጥታ ድረሱልን ማለት ፣ ማረድ ፣ ለእነርሱ መሳል ፣ ቀብሮችን መጦዎፍ ፣ ምሰሶዋን ግድግዳዋን መሳም ፣ በእርሱም መተሻሸት ፣ ከእርሷ ዘንድ ለዒባዳ መዘውተር ፣ አገልጋዮችን ፣ መጋረጃዎችን ማድረግ ምን ይሆን ግምትህ!?

በዚህ እና ከዛፍ ላይ መሳሪያ በማንጠልጠል በረከትን መፈለግ ምን ይሆን ዝምድናው?!

5. **በጃሂልያ ማህበረሰብ መመሳል ተከልክሏል፥**

"ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ ልክ በኑ ኢስራኢሎች የተናገሩትን አይነት ንግግር ነው የተናገራችሁት" በማለት ረሡል ﷺማውገዛቸው።

ማንኛውም ሀቅን ያልተገነዘበ ፣ የጃሂልያን ተግባራት የፈጸመ ሁሉ እርሱም የጃሂልያ ባለቤት ነው።

6. **ነብዩ ﷺባለፉ ህዝቦች ተጎታች መሆን እና የእነርሱን መንገድ መከተልን ማስጠንቀቃቸው፥**

"ከእናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን መንገዶች በእርግጥ ትከተላላችሁ" በማለት ነብዩ ﷺ መናገራቸው።

ይህ ፣ ይህች ማህበረሰብ ከዚህ በፊት የነበሩ ጃሂልያዎች በተፈተኑበት አይነት ልትፈተን እንደምትችል የነብዩ ﷺ ማንቂያ ነው። በመቃብር አምልኮ ፣ በዛፍ አምልኮ በእርሷም ተበሩክ በማድረግ ኡመታቸው ሽርክ ላይ እንዳይወድቁ ነብዩ ﷺ እያስጠነቀቁ ነው።

**ማጠቃለያ**

በዱንጋዮች ፣ በዛፎች ፣ በመሻሂዶች ፣ በቦታዎች እና በመሳሰሉት አሻራዎች በረከትን መፈለግ በሸሪዓ አልተደነገገም። ምክንያቱም በረከትን መፈለግ ዒባዳ ነው። ከአላህ ውጭ አምልኮቶችን ለሌላ አካል ማዋል ከአላህ ጋር ሌላን አካል አምላክ አድርጎ መያዝ እና በእርሱም ማጋራት ነው።

**የተበሩክ እና ጥንታዊ ቅርሶች ጥመት ምክንያቱ**

በማንኛውም ነገር ከሐቅ ለማዘንበል የራሱ የሆነ ቀስቃሽ እንዲሁም ወደርሱ የሚያደርሱ ምክንያቶች ይኖሩታል። በዚህ ቦታ ጥቅል በሆነ መልኩ ለጥመት ምክንያቶች አሉ። ሌሎች ደግሞ በተወሰኑ ጉዳዮች ልዮ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው። በዚህ ትምህርት የተፈለገውም ይህ ነው።

የበረከት ጉዳይ የሚያፈነግጥበት ምክንያት በትርጉሙ ውስጥ ግራ መጋባት በመኖሩ ነው። አጭበርባሪዎች ቃሉን በማስዋብ ጠማማ ትርጉሙን ማስልጠን እና በትክክለኛ ትርጉሙ የተቀበለውን ህዝብ ለማታለል ነው። ይህ ግራ መጋባት እውነትን መደበቅ ያስከትላል።

**በቁርኣን ውስጥ ይህን አካሄድ የሚያስጠነቅቅ መጧል**

﴿وَلَا تَلْبِسُواْ الْحَقَّ بِالْبَاطِلِ وَتَكْتُمُواْ الْحَقَّ وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ﴾

**"እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ ፤ እናንተም የምታውቁ ስትሆኑ እውነትን አትደብቁ።"**

*(አል'በቀራህ፡ 42)*

﴿يَا أَهْلَ الْكِتَابِ لِمَ تَلْبِسُونَ الْحَقَّ بِالْبَاطِلِ وَتَكْتُمُونَ الْحَقَّ وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ﴾

**"የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! እውነቱን በውሸት ለምን ትቀላቅላላችሁ እውነቱን እናንተ የምታውቁ ስትሆኑ ለምን ትደብቃላችሁ"** *(አል'ዒምራን፡ 71)*

በቅርሶች በረከትን መፈለግ የጥመት ባለቤቶች ይጠቀሙበታል ፣ በማጭበርበር ያምታቱበታል ፤ በውስጡ ሽርካቸውን ይደብቁበታል። ምክንያቱም ውስጡ ሸሪዓዊ ትርጉም ፣ ቢድዓዊ ትርጉም እና ሶስተኛውን ሽርካዊ ትርጉም አቅፏል።

እነርሱ የፈለጉት - የትክክለኛውን የሸሪዓ ትርጉም ማስረጃ አልብሰው ጠማማ ትርጉሟን ነው። በዚህ ምክንያት ሰዎች በተምታታ ነገር ላይ ይወድቃሉ።

በዚህ መልኩ አጭበርባሪዎች ወደጃሂሉ ህብረተሰብ በመግባት የእነርሱ ግንዛቤ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያደረጉት። አላማቸውን ግልጽ ቢያደርጉት ኖሮ ከሰዎች ዘንድ ውግዘት ይደርስባቸው

ነበር። አላህ የሻበት ካልሆነ በቀር አንድም አካል ሸርክ ላይ መውደቅ የሚፈልግ የለም። ወደዚህ ተንኮለኝነት ገብተው ውሸትን በእውነት መልክ ያሳያሉ።

ይህ ሆን ተብሎ ክልክል የሆነውን ተበሩክ ፣ ሸሪዓዊ ከሆነው ተበሩክ ጋር ለመቀላቀል ነው። በተበሩክ ህግ የደጋግ የአላህ ባሮችን አሻራ ከነብዩ ﷺ ሸሪዓዊ አሻራ ጋር ለማነጻጸር ወይም ነብያዊ በሆነው አካላዊ አሻራ ወይም ከአካላቸው በተነጠለው አሻራ ተበሩክ ማድረግን በተለያዩ የቦታ ቅርሶች ተበሩክ ጋር ለማነጻጸር የሚደረግ ጥረት ነው። የቦታዎች አካላዊ በረከት ሊሸጋገር ይችላል ብሎ በማመን ከተነጠሉ የነብዩ የአካል ክፍሎች አሻራዎች በረከት ጋር ለማነጻጸር የሚደረግ ሙከራ ነው።

**በአሻራዎች በረከት ጉዳይ ወደጥመት ካደረሱ ጉልህ ከሆኑ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፣**

**አንደኛው ምክንያት፡** የተበሩክን ሸሪዓዊነት መሰረት በማድረግ የደጋግ የአላህ ባሮችን አሻራ እና አካላቸውን ከነብዩ ﷺ አካል እና አሻራቸው ጋር ማነጻጸር።

የአካላት በረከት አላህ ለለገሰው ካልሆነ በቀር ሊሆን አይችልም። እነርሱም፡ ነብያቶች እና ሙርሰሎች ናቸው። ከሌሎች ደጋግ የአላህ ባሮች በረከታቸው የስራ በረከት ነው። ማለትም ፡ ከኢልማቸው ፣ ከተግባራቸው ፣ እነርሱን ከመከተል ከሚመነጨው እንጅ ከአካላቸው አይደለም።

የነብያት አካላቶች አሻራዋ ወደሌሎች የሚሸጋገር የሆነ አካላዊ በረከት አላት። ይህ እነርሱ ብቻ የተለዩበት ነው። የሷሊሆች በረከት ግን በትክክለኛ ሐዲስ ከነብዩ ﷺ እንደመጣው በስራቸው ነው።

"إن من الشجر لما بركته كبركة المسلم ..."

“ከዛፎች መካከል በረከቱ ልክ እንደሙስሊም በረከት የሆነ አለ ...” *(ቡኻሪ፡ 5444)*

ሁሉም ሙስሊም ወደኢማን ፣ በልቡ ውስጥ ወደሚገኘው እርግጠኛነት ፣ ወደእውቀት ፣ ወደተግባር ፣ አላህን ወደማላቅ ፣ ለእርሱ ልቅና ወደመስጠት እና ረሡልን ﷺ ወደመከተል የሚመለስ የሆነ በረካ አለው።

**ተጨማሪ ከሆኑት የሷሊሆች በረከት፡** ሰዎችን ወደመልካም መጥራት ፤ ለእነርሱ ዱዓ ማድረግ ፣ ለፍጡራን መጥቀም ፣ በጥሩ ኒያ ለእነርሱ በጎ መስራት ናቸው።

በተጨማሪ በአላህ ባሮች ስራዎች አማካኝነት ከመልካም ነገሮች አላህ የሚያመጣው ፤ በእነርሱ መስተካከል እና ሌሎችን በማስተካከላቸው ምክንያት ከቅጣቱ እና በፍጡራሉ ላይ አጠቃላይ የሆነ መቀጣጫ እንዲወገድ ያደርጋል።

**አላህ በቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿وَمَا كَانَ رَبُّكَ لِيُهْلِكَ الْقُرَى بِظُلْمٍ وَأَهْلُهَا مُصْلِحُونَ﴾

**"ጌታህም ከተሞችን ባለቤቶቻቸው መልካም ሰሪዎች ሆነው ሳሉ በመበደል የሚያጠፋቸው አልነበረም።"** *(ሁድ፡ 117)*

ደግ የሆነ ሙስሊም በረከት ወደሌላ አካል አትሸጋገርም። በሷሊህ ሰዎች ያለው የተበሩክ ትርጉም በደግነታቸው እነርሱን መከተል ማለት ነው። የኢልም ባለቤቶች ተበሩክ ከእውቀታቸው መቅሰም ፣ ከእነርሱም መጠቀም ማለት ነው።

አንዳንድ ሰዎች የሷሊሆች አካል በረካ አለው ብለው ስለሚያምኑ በአካላቸው ይተሻሻሉ ፣ ከነርሱ የተረፈውን ይጠጣሉ ፣ እጃቸውን ይስማሉ። ይህ ደግሞ በሚከተሉት ምክንያቶች በሸሪዓ ክልክል እና ሀራም ነው።

1. ሷሊሆች እና ነብዩ እንኳን በደረጃ እና በበረካ እኩል ሊሆኑ ቀርቶ በደረጃ ፍጹም አይቀራረቡም።
2. ከነብዩ ውጭ በአሻራቸው በረካ መፈለግን የሚፈቅድ መረጃ አልመጣም። ይህ ደግሞ በነብዩ

ብቻ የተለየ መሆኑን ያጠናክራል። ይህ ከተረጋገጠ የሌሎች አካላት ብይን ከነብዩ ብይን ጋር የተለያየ መሆኑ ይታወቃል ማለት ነው። ይህ ደግሞ የዑለሞች ስምምነት ያለበት ነው።

3. ሶሃቦች በነብዩ ህይዎት ዘመንም ከሞቱም በኋላ አንዱ ከአንዱ በረካ አልፈለገም። ሌላውን ትተው በረሡል ﷺ ብቻ መለየታቸው ከእነርሱ የሆነ አጠቃላይ ስምምነት ነው።

4. ልክ እንደዚሁ ታብዒዮችም በሶሃቦች ጎዳና ላይ ነው የተጓዙት። ከሶሃቦች በረካን ፈለጉ የሚል አንድም የመጣ መረጃ የለም። በእውቀትም በዲንም መሪዎች እንዲሁም ደረጃቸው ከፍ ያለ ከመሆኑ ጋር ታብዕዮችም ይህን ተግባር ፈጸሙት የሚል መረጃ የለም።

**ሸሪዓዊ ቢሆን ኖሮ ሶሃቦችም ታብዕዮችም ወደዚህ ነገር ይሽቀዳደሙ ነበር ፤ እኛንም በዚህ ተግባር ይቀድሙን ነበር። ይህን ተግባር በመተው ላይ አይስማሙም ነበር። መልካም በመስራት ከሰዎች ሁሉ በጣም ጉጉት የነበራቸው ነበሩ።**

**ይህን የሚያጠናክረው ኢማም አሸሻጢብይ ﵀ "ኢዕቲሷም" በተባለው ኪታባቸው** (1/482) የተናገሩት ነው፡

*"ነብዩ ﷺ ከእርሳቸው በኋላ በኡመቱ ውስጥ የእርሳቸው ምክትል ከነበረው አቡበክር ሲዲቅ ﵁ የበለጠ ሌላ ሰው አልተውም። ከዚህ ምንም አይነት ነገር በእርሱ አልተሰራም። ዑመርም ﵁ በኡመቱ ውስጥ ከእርሱ በኋላ እንዲሁ። ከዚያም ዑስማን ﵁ ፣ ከዚያም ዓልይ ﵁ ፣ ከዚያም ሌሎች ሶሃቦች በኡመቱ ውስጥ አንድም በደረጃ ከእነርሱ የበለጠ የለም። ከዚያም በትክክለኛና በታወቀ መንገድ ከእነርሱ አንድም አልተረጋገጠም በዚያ መልክም ይሁን በተመሳሰለው በአንድም ላይ በረካ ለመፈለግ ተበሩክ አደረገ የሚል አልተረጋገጠም። ይልቁንም እነርሱን በመከተል ፣ በስራቸው ፣ በንግግራቸው ነብዩ ﷺ በተጓዙበት በመጓዝ ነው ያሳጠሩት። ስለዚህ ይህን ነገር በአጠቃላይ መተዋቸው ከእነርሱ የሆነ ስምምነት ነው።"*

**ሀፊዝ ብን ረጀብ ﵀ "አልሁክም አልጀዲራ ቢልዒዛዓት"** በተባለው ኪታብ ገጽ 46 ይህን ጉዳይ አጠናክሮ እንደሚከተለው ተናግሯል፡

*“በአሻራዎች ተበሩክ ማድረግ ልክ እንደዚሁ ነው ፤ ሶሃቦች በነብዩ ﷺ ተበሩክ ባደረጉበት ወቅት እርስ በርሳቸው አልተገበሩትም ነበር። ታብእዮችም እንዲሁ ደረጃቸው ከፍ ያለ ከመሆኑ ጋር ከሶሃቦች ጋር አልሰሩትም።”*

5. ወደሽርክ የሚወስደውን መንገድ ለመዝጋት ሲባል ከነብዩ ጋር በማነጻጸር በደጋጎች አሻራ ተበሩክ ማድረግ አይፈቀድም።

**ኢማም ሻጢብይ ﵀ “ኢዕቲሷም” በተባለው ኪታባቸው (1/482) የሚከተለውን ተናግረዋል ፡-**

*“መስመሩን ለመዝጋት ሲባል በደጋጎቹ ተበሩክ አይፈቀድም። በማለት የሚከተለውን ተናገረ ፡ ተራው ህብረተሰብ ከተወሰነ ድንበር ላይ አያቆምም ፣ ይልቁንም በርካታ ድንበሮች ይጣሳሉ ፤ በረካን ፍለጋ በሚለው ማህይምነቱ ከፍ ብሎ በረካ ለሚፈለግበት አካል የሌለ ነገር እምነት እስከሚይዝ ድረስ ከልኩ የወጣ ክብር ይሰጠዋል። ተበሩክ ማለት ደግሞ የአምልኮ መሰረት ነው።”*

ተበሩክ በደረጃ ከፍ ለሚያደርገውም ፣ ከፍ ለሚደረገውም አካል ፈተና ነው።

ሀፊዝ ብን ረጀብ ﵀ “አልሁክሙ' ልጀዲር ቢልኢዛዓቲ” በተባለችው መልእክቱ ተበሩክ በነብዩ ﷺ ብቻ የተገደበ መሆኑን እና በእርሱ ላይ ሷሊሆችን ማነጻጸር ተገቢ እንዳልሆነ በገለጸበት ቦታ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

*“በደረጃ ከፍ ለሚያደርገውም ከፍ ለሚደረገውም ፈተና ነው። በቢድዓ ውስጥ ገብቶ ድንበር ማለፍ ስለሚያስፈራ ፣ አንዳንድ ጊዜ አድጎ ከሽርክ አይነትም ስለሚያደርስ።”*

**የተቃራኒዎችን ሀሳብ ወስደን በደጋግ የአላህ ባሮች አሻራ በረከት መሻት ይቻላል ብንል ለዚህ የሚከተለውን የመከራከሪያ ሀሳብ እናቀርባለን፡**

1. ደግ የአላህ ባሪያ መሆኑ አለመረጋገጡ። ደግነት በልቦና እንጅ አይረጋገጥም። ይህን ደግሞ ግልጽ በሆነ መረጃ እንጅ መመልከት አይቻልም። ሶሃቦች ለዚህ እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

አላህ እና ረሡል አወድሰዋቸዋል ወይም በደጋግነታቸው ኡመቱ የመሰከረላቸው ታብዕይ እና የሙስሊም ኢማሞች እና ሌሎችም ናቸው። እነርሱ ደግሞ በአካል የሉም። ሌሎችን በተመለከተ የመጨረሻው ውሳኔያችን ደጋግ የአላህ ባሮች ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ግምታችንን ማስቀመጥ ነው። ይህንንም ለእነርሱ ተስፋ እናደርጋለን።

2. ሰውየው ደግ ሰው ነው ብለን ብንጠረጥር እንኳ ፣ መጨረሻው በመጥፎ ሊቋጭ ይችላል ምክንያቱም ስራዎች የሚታዩት በፍጻሜያቸው ነውና። ይህ ከሆነ እነርሱ በተናገሩት መሰረት ይህ ሰው የተበሩክ ባለቤት አይሆንም።

በዚህ መሰረት ሶሃቦች ከነብዩ በረካን እንደፈለጉት ሁሉ በሌሎች ደጋግ የአላህ ባሮች ተበሩክ አይነጻጸርም - ምክንያቱም ተበሩክ በነብዩ ﷺ ብቻ የተለየ በመሆኑ። እንዲሁም አንድም አካል በደረጃ ከነብዩ ﷺ ጋር መቀራረብ ባለመቻሉ ነው። በበረካ እና በደረጃ እንዴት ይስተካከላሉ!

**ሁለተኛው ሰበብ፡** ተሸጋጋሪ ያልሆኑ የቦታዎችን በረከት እና አካላዊ እንዲሁም ተሸጋጋሪ የሆነውን የነብያቶች በረካ በአንድ ላይ መቀላቀል ወይም ሁለቱን አለመለየት።

አካላዊ እና ተሸጋጋሪ የሆነውን የነብያት በረከት በተመለከተ ማብራሪያዋ እና ማረጋገጫዋ ከዚህ በፊት አልፏል። የቦታዎችን በረከት አስመልክቶ በተከበረው ቁርኣን መጧል።

አላህ በአንዳንድ መሬቶችና ቦታዎች ላይ በረከት አድርጓል።

**በይተል ሀራምን በተመለከተ አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-**

﴿إِنَّ أَوَّلَ بَيْتٍ وُضِعَ لِلنَّاسِ لَلَّذِى بِبَكَّةَ مُبَارَكًا وَهُدًى لِّلْعَالَمِينَ﴾

**"ለሰዎች (መጸለያ) መጀመሪያ የተኖረው ቤት ብሩክና ለዓለማት ሁሉ መመሪያ ሲሆን ያ በመካ ያለው ነው።"** *(አል'ዒምራን፡ 96)*

**መስጅደል አቅሷን አስመልክቶ አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿سُبْحَانَ الَّذِى أَسْرَى بِعَبْدِهِ لَيْلاً مِّنَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ إِلَى الْمَسْجِدِ الأَقْصَى الَّذِى بَارَكْنَا حَوْلَهُ﴾

**"ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኬደው (ጌታ) ጥራት ይገባው።"** *(አል'ኢስራእ፡ 1)*

**መሬቱ በረካ አለው ሲባል፡** ለሰዎች እርሻ ፣ ለቀለባቸው ፣ ሲኖሩበትም ፣ አዝመራ ሲዘሩበትም ቋሚ እና ዘውታሪ በረከት አለው ማለት ነው። እርሷን አጥብቆ በመያዝ እንዲበረታቱና ወደርሷ ዱዓ እንዲያደርጉ ነው። መሬት በረካ አለው ሲባል በመሬቷ እና በአጥሯ መተሻሻት በሚል መገንዘብ የለብንም። ምክንያቱም በረከቷ የማይታይ ስውር ከመሆን አኳያ ቋሚ እንጅ ወደሌላ የምትሸጋገር አይደለችም።

በአንድ በኩል ከዕባ የተባረከ ነው። ልቦች በእርሷ ይንጠለጠላሉ። ለፈለጋት ፣ ወደርሷ ለመጣ ፣ በእርሷ ለዞራት ከእርሷ ዘንድ አላህን ለተገዛባት ለእርሱ መልካሙ ይበዛለታል።

ጥቁሩ ዲንጋይ ወይም ሀጀረል አስወድ የተባረከ ዲንጋይ ነው። በረካው የሚገኘው ግን በዒባዳ ምክንያት ነው። ለአምልኮ ነብዩን ﷺታዞ እርሱን የሰለመ ወይም የሳመ ረሡልን ﷺ የመከተል በረካ ያገኛል።

ጥቁሩን ዲንጋይ መሳም ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ በቅርጽም በይዘትም ረሡልን ﷺ በመከተል ተፈጻሚ የሚሆን ፍጹም አምልኮ ነው። በመሳም ፣ በመሳለም ፣ ከዚያም ከእርሱ የሚዳሰስ በረካ አገኛለሁ ብሎ በመገመት ሌላውን የሰውነት ክፍል በሚያሸው ተቃራኒ የምንዳውን በረካ ለማግኘት ተግባራዊ የሚደረግ የአምልኮ ክፍል ነው።

**የአማኞች አሚር ዑመር ብን አልኸጧብ ﷺ ሀጀረል አስወድን ሲስም የተናገረው ንግግር በቡኻሪና በሙስሊም ተዘግቦ ይገኛል፡-**

"إني أعلم أنك حجر لا تضر ولا تنفع ، ولولا أني رأيت النبي صلى الله عليه وسلم يقبلك ما قبلتك"

*"እኔ የማትጎዳ የማትጠቅም ዲንጋይ መሆንህን አውቃለሁ ፤ ነብዩ ሲስሙህ ባልመለከት ኖሮ አልስምህም ነበር"* (ቡኻሪ፡ 1597, ሙስሊም፡ 1270)

ይህ ማለት እርሱን ለሳመው አካል ምንም ጥቅም አያስገኝለትም ፣ ከጉዳትም አይከላከልም ማለት ነው። ሐጀረል አስወድን ለመሳም ያነሳሳው አላህን ለመገዛት ፣ የአላህን መልእክተኛ ﷺ

ለመከተል ብቻ እና ብቻ ነው። ለዚህ ነው ዑመር ﷺ **"...የአላህ መልእክተኛ ሲስሙህ ባልመለከት ኖሮ አልስምህም ነበር"** የሚለውን ንግግር የተናገረው።

በእነርሱ ላይ አላህን በዘውታሪነት እና በብቸኛነት እስካልተገዛባቸው ድረስ በረካ ሊኖራቸው አይችልም። ቦታዎች አላህ በረካ ለመስጠት ምክንያቶች ናቸው። መስጅዶች የተባረኩ ናቸው። ይሁን እንጅ ከእርሷ ላይ አላህን መታዘዝ ከተወገደ በረከቷ አይዘወትርም።

ይህ ነው የቦታዎች በረከት ትርጉሙ። የበረከቱ ዘውታሪነት ከትርጉም አንጻር እንጅ በአካል የሚሸጋገር አይደለም። እርሷ የምትዳሰስ ሳትሆን ልትዳሰስ እና ልትጨበጥ የማትችል ነገር ነች። አሻራዎችን በረካ አገኛለሁ ብሎ ማበስ ፣ መሳም ከእርሱ ወደከበደ ነገር ያዳርሳል። ወደሽርክ ወይም ከአላህ ውጭ ወደሆነ አካል ለአምልኮ ወደሚያደርስ ድንበር ማለፍ ፣ ማላቅ ፣ እንደቅዱስ መመልከት ያደርሳል።

ሊቃውንት እና የሙስሊም መሪዎች ሰይጣን ከማሳመርና በረካ ይገኝበታል ከሚባለው ሰው ዘንድ የሚስተዋሉ ደግነቶች እና መልካም ነገሮች ምክንያት ሰዎች መሸወድ እንደሌለባቸው እና ከእነርሱ ፈተና መጠበቅ እንዳለባቸው አስጠንቅቀዋል። በተበሩክ ስም ከሀቅ እድል የሌለው ከአላህ ውጭ በማምለክ ይገለበጣል ፣ ነጻ አይወጣም።

**ሀፊዝ አቡ ሻማ** ﷺ "አልባኢሱ ዓላ ኢንካሪል ቢደዒ ወልሃዋዲስ" በሚባለው ኪታብ (25-26) የሚከተለውን ተናግሯል ፡-

*"መከራው በሰፊው ያዳረሰው ሰይጣን ለማህበረሰቡ የሚሸላልመው ነው። በየአገሩ ልዩ በሆኑ ቦታዎች አጥሮችን ፣ ምሰሶዎችን እና መብራቶችን ይፈጥራል። (በእነርሱ አባባል) ፈርድና ሱናዎችን የሚዘናጋ በደግነት ፣ በወልይነት የሚታወቅ አንድ አካል በመናም እንደታየ ፣ ያንን እንደሚሰሩ ፣ በእርሱም ላይ እንደሚጠብቁ የሚያወሩ አካላትን አዘጋጅቷል። በዚህም ተቃረብን ብለው ይጠረጥራሉ። ከዚያም ይህንን አልፈው ወደማላቅ ደረጃ ይደርሳሉ። ያንን ቦታ በልቦቻቸው ውስጥ ያልቁታል። በሽተኛቸውን ማዳንን ከእርሱ ተስፋ ያደርጋሉ ፤ ለእርሷ ስለት በመሳል*

*ሀጃቸው እንደሚወጣ ይገምታሉ። እርሷም በምንጮች ፣ በዛፍ ፣ በአጥር በዲንጋይ መካከል ነው ያለችው"*

**ኢማም አቡበክር አጦርጡሽይ ﷺ "አልሀዋዲስ ወልቢደዕ" በመባል በሚታወቀው ኪታቡ (ገጽ 38-39) ላይ ማንኛውም ሰው ክብር የሚሰጠውን ቅርስ ሁሉ ሰባብሮ የሚጥል ንግግር እንደሚከተለው ተነናግሯል ፦**

*"አላህ ይዘንላችሁና ተመልከቱ ፣ ቁርቁራ ወይም ሰዎች ለጉዞ አላማ የሚያደርጓት ፣ የሚያልቋት ፣ ከእርሷ በኩል ፈውስ ማግኘትን ተስፋ የሚያደርጉባት ፣ በእርሷ ምስማሮችን እና የተቀደዱ ጨርቆችን የሚያንጠለጥሉባት ዛፍ ካገኛችሁ ፣ እርሷ ዛቱ አንዋጥ ነችና ቁረጧት።"*

**በአሻራዎች ተበሩክ የማድረግ ፍጻሜዎች**

በአሻራዎች ተበሩክ ማድረግ በሸሪኣ የተከለከለ ነው። ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። አክሳሪ የሆኑ ክፋቶች ፣ አደገኛ የሆኑ ተጽዕኖዎች ናቸው። ከእነዚህ ፍጻሜዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የተውሂድ ሙሉነቱን ወይም ተቃራኒው ከሆነው ሽርክ ላይ ይጥላል።
2. በዲን ውስጥ አዲስ ፈሊጦችን መፍጠር - ምክንያቱም በአሻራዎች ተበሩክ ማድረግ ህጋዊ መሆኑን የሚጠቁሙ የቁርኣንም ይሁን የሐዲስ ምንም አይነት መረጃዎች ስላልመጡ። የቀደምት ሰለፎቻችን ደጋጎቹ ተግባርም አልነበረም።
3. ክልክል ነገሮችን ወደመጣስ ያደርሳል። ከበርካታ ጉዳቶች እና መጥፎ ነገሮች ላይ ይጥላል። ለምሳሌ ፡ ቀብሮችን የሚዘየሩ ቦታዎች ፣ መሻሂዶች ፣ ሰዎች ለክብረ በዓል የሚመላለሱበት ቦታ በማድረግ ህያው ማድረግ።
4. ሱናዎች ውድቅ ይደረጋሉ። ሰዎች አንድ ቢድዓ አይፈጥሩም ከሱና የእርሷ ተመሳሳይ የሚወገድ ቢሆን እንጅ። ልቦች በቢድዓ አይጠመዱም ከሱና የራቁ ቢሆን እንጅ። ምክንያቱም ልብ በሁለት ተቃራኒ ነገሮች አይጠመድም።

5. የቢድዓ በፍጥነት መሰራጨት እና መበተን። ቢድዓ ልክ እንደእሳት ነች። በቀላሉ ቃንቄ ሆና ትጀምራለች ከዚያም ግዙፍ ትሆናለች።

6. በሚከተሉት መንገዶች ጃሂሎችን ለማታለል ፣ ትውልድን ለማጥመም ቅጥፈትና ውሸት ላይ መውደቅ።

- ክልክል የሆኑ የተበሩክ ዓይነቶችን ሸሪዓዊ ለማስመሰል ደካማ እና በረሡል ላይ የተዋሹ ሐዲሶችን ማስረጃ አድርጎ ማቅረብ ፤
- ሸሪዓዊ የሆኑ ግልጽ ማስረጃዎችን ያለትርጉማቸው አጣሞ መተርጎም ፤
- በቅጥፈትና በውሸት የተበሩክ ቦታዎችን መለየትና መገደብ ፤
- አንዳንድ የቀብር አገልጋዮች እንደሚያሰራጩት ከቀብሩ ዘንድ መተሻሸት በረካ ያስገኛል ፣ ከእርሱ ዘንድ ዱዓ ማድረግ ተቀባይነት ያስገኛል ብሎ ለጃሂሉ ህብረተሰብ መሞገት ፤

ልምዶች እና ወሬዎች ትክክለኛ ወደሆነው ሀይማኖታዊ እና ሸሪዓዊ ተግባራትን ለማወቅ የማያደርሱ መሆኑ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። ብቸኛውና ተቀባይነት ያለው መንገድ ቁርኣን እና ሐዲስን መሰረት ባደረገው ሸሪዓ መዳኘት ነው።

ባጢል የሆኑ ነገሮችን ህጋዊ ለማድረግ ልምድን ማስረጃ ማድረግ ትክክል አይሆንም። ሀይማኖታዊ አምልኮቶች የሚጸድቁት በራስ ልምድ ሳይሆን በሸሪዓ ማስረጃዎች ብቻ እና ብቻ ነው።

**ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያ ﵀ ለዚህ ጉዳይ (መጅሙዕ አልፈታዋ) በተባለው ኪታቡ** (27/115) **ምላሽ ሰጧል፡**

*“በአንዳንድ የቅርስ ቦታዎች -በረሡል ቀብር ወይም በአንዳንድ ደጋግ የአላህ ባሮች ቀብር የወልዮች መሻሂዶች- ዱዓ ተቀባይነት አስገኝቷል ፣ መድሀኒትነታቸው በልምድ ተገኝቷል ብለው የሚሞግቱ አሉ። በዚህ ውስጥ የሚካተተው ወደነብዩ እና ወደሌሎች የተጠጉት የቅጥፈትና የሀሰት ወሬዎች ናቸው። ብይኑ የሁሉም አንድ ነው?*

**አላህ ይዘንለትና የሚከተለውን ምላሽ ስጠ፡** *“በአንዳንድ ወቅቶች ጉዳዮቻችን ተፈጽመው እናገኛቸዋለን” በማለት የተናገረው አካል ፤ ይህ አላማዋን ለእነርሱ ያጸድቃልን?*

**ለእነርሱ ይባላል፡** ይህ ለሚከተሉት ምክንያቶች አላማቸውን የሚያጸድቅ አይደለም፡

**አንደኛዋ፡** ሙሽሪኮች እና የመጽሐፍ ባለቤቶች ከጣዖቶቻቸው ፣ ከሚያልቋት ቦታዎች እና ቅዱሳን -ከሚሏቸው- ሀውልቶቻቸው ዘንድ ጉዳዮቻቸው ብዙ ጊዜ ይፈጸምላቸዋል። በኢስላም ዘመን እርሷን ማላቅ ሀራም ነው።

“በሀራምነቱ ሙስሊሞች የተስማሙበትን እንዲህ አይነቱን ተግባር ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው” ይላል እንዴ አንድ ሙስሊም? የልብ ወለድ እና የቢድዓ ባለቤቶች ሰበብ ናት ብለው የፈጠሯትን አንድ ተግባር አታገኝም ፣ ከሙሽሪኮች እና ከመጽሐፍ ባለቤቶች ዘንድ የምታገኛት ቢሆን እንጅ። ይህ ተግባራቸው ነው ከክህደት ላይ የጣላቸው። እንዴውም ከእርሱ የበረታ። ይህን ያስተነተነ ሰው በአብዛኛው ቢድዓ ከክህደት የተያዘ መሆኑን ይገነዘባል።

**የኢማን ሙሉነት፡** አላህ እና ረሡል ያዘዙትን መስራት ፤ አላህ እና ረሡል የከለከሉትን መከልከል ነው። ከታዘዙት ነገር የተወሰነውን ትተው ፣ ክልክል በሆነው ከተኩት በዚያው መጠን እምነት ይጎድላል።

**ሁለተኛው፥** ይህ ክፍል በጣም ውሸት ይበዛበታል። ቁርኣን በበርካታ ቦታዎች ውሸት ከሽርክ ጋር የተቆራኘ ፣ እውነት ደግሞ ከኢኽላስ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ይጠቁማል። ሙእሚኖች የእውነትና የኢኽላስ ባለቤቶች ናቸው። ከሀዲዎች ደግሞ የውሸት እና የሽርክ ባለቤቶች ናቸው። በመሻሂዶች (በቀብር አምልኮቶች) ውስጥ ሽርክ ይገኛል። ከእርሷ ጋር በርካታ ውሸት ተቆራኝቶባታል።

**ከእርሱም መካከል-** ይህ ቀብር ልቅና ያለው እከሌ የተባለ ወይም መሪ ቀብር ነው ብሎ መሞገት። በዚህ ውስጥ በርካታ ውሸት አለ

**ከዚህ መካከል**-ስለሁኔታው ውሸት በውስጡ የበዛበት ወሬ ይወራል

**ሶስተኛው፡** ከእርሱ ዘንድ ሀጃችን ወጣልን ብለው መናገራቸውን ምን ብዙ አደረገው! በቀብሩ

የሚያልቁት አካል የሚፈልጉትን ጉዳይ እንዳሳካ ፣ የተለየ ተዓምር እንደሰራ የተለያዩ የውሸት መላዎችን እየፈጠሩ ተራውን ህብረተሰብ ያምታታሉ። እንዲህ አይነት እውነት የሌላቸውን ወሬዎች የሚያወሩትን ሰዎች ቁጥር ምን ብዙ አደረገው! እንዲህ አይነት ነገር በርካታ ነገሮችን ተመልክተናል።

**አራተኛው-** ከእነእከሌ ጋር ዝምድና አለኝ ብሎ መናገሩ፡ በርካታው ሰው ለምሳሌ በልጅነትም ይሁን ከልጅነት ውጭ ከዚያ ቀብር ባለቤት ጋር ዝምድና እንዳለው ይሞግታል። ውሸት ከመሆኑ ጋር ለቀብሩ አገልጋይ ሆኖ ለመሾም የኢብራሂም ኢብን አድሀም ልጅ እንደሆነ የሚሞግት አካል ተመልክቻለሁ። የነብዩ ዘር እንደሆነ የሚሞግተውን ሰው ለመግለጽ በጣም ብዙ ነው።

**አምስተኛው-** በዚህ ኡመት ውስጥ ገደብ በሌለው ሁኔታ ውሸት በመዋሸት የሚታወቁት ራፊዷ ናቸው። ድንበር በማለፍና በሽርክ ከሚታወቁ ሙስሊም ነን ብለው ከሚሞግቱ ቡድኖች ትልቆቹ ናቸው። ከእነርሱ መካከል የረሡልን ቅርብ ዘመድ አምላክ ነው ብሎ የሞገተ ፣ ከእነርሱ መካከል ከነብዩ ውጭ ነብይነትን የሞገተ አለ። ዓልይ ነብይ ነው ብሎ እንደሞገተ ፣ ሙኽታር ብን አቢ ዑበይድ ነብይ ነኝ ብሎ ሞግቷል። ከዚያም ጃሂሎች ተከታይ ሆነዋል። የሸይኾች ተከታዮች ተፈጥረዋል ፣ በባህታዊ ጠማሞች ላይ ድንበር የሚያልፉ አካላት ተከስተዋል። እነርሱ ከራፊዷዎች ቀጥሎ በመቃብር ላይ ድንበር በማለፍ ከሰዎች ብዙ ናቸው። ከውሸት በኩል ከቡድኖች ብዙዎች ናቸው። ሁሉም ቡድን ከነሷራ ጋር መመሳሰል አለው። የነሷራ ውሸት ፣ ሽርካቸው ፣ ድንበር ማለፋቸው ከተራው ማህበረሰብም ይሁን ልዩ ከሆነው ማህበረሰብ ዘንድ የታወቀ ነው። ከእነዚህ ቡድኖች ዘንድ አላህ እንጅ ማንም ቆጥሮ የማይዘልቀው ሽርክ እና ውሸት አለ።

**ሶስተኛው አቅጣጫ፡** የአንድ ሙስሊም ጉዳይ ተፈጻሚ ከሆነች ፡ ከቀብር ዘንድ ዱዓ በማድረጉ ሊሆን ይችላል ብለው ይሞግታሉ። ቀብር ከየት መጦ ነው የዚህን ሙስሊም ጉዳይ ለመፈጸም ተጽዕኖ የሚያሳድረው? ይህ ከቀብር ዘንድ ስለት ተስለው ጉዳያቸው ከሚወጣላቸው ሰዎች ጋር ተመሳሳይነት አለው....

**ስለት** ጥቅም ለማስገኘት ወይም ጉዳትን ለመከላከል ከተያያዙ ጉዳዮች ጋር ሰበብነት የለውም.....

**አራተኛው አቅጣጫ፡ ልክ** ፈላስፋዎችም ይሁን የእነርሱን መንገድ የተጓዙ አካላት እንደሚሉት ቀብሮች በዚያ ነገር ላይ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም አላቸው ብንል ፤ ማለትም ከአካል የተለየችው ሩህ ከተጣሪው ጋር ግንኙነት ይኖራታል ፣ በዚያም ታጠናክራለች ፣ ....መቃብሮችን በመጎብኘት ፣ ወይም ለሌላ ነገር ምክንያት ትሆናለች ብንል ፣

**ለእርሱ የሚከተለውን ምላሽ እንሰጣለን ፤** ማንኛውም የሰው ልጅ ጉዳዮ የተፈጸመበት ሰበብ ሁሉ ሸሪዓዊ ነው ወይም ይበቃል ማለት አይደለም። ሸሪዓዊ የሚሆነው ከመጥፎው መልካሙ ሲበዛ ነው። መጥፎው ከበዛ ሸሪዓዊ ሊሆን አይችልም። ይልቁንም አንዳንድ ጥቅሞች እንኳ ቢገኙም አደጋ ነው የሚሆነው ...

በዚህ ውስጥ የሰው ልጆች ጉዳያቸው የሚፈጸምባቸው ጥቅል የሆኑ ምክንያቶችን አስመልክቶ ማንቂያ አለው"

ካሳለፍነው ትምህርት ተፈላጊው ነገር መገኘቱ ሽርክ የሆኑ ሰበቦች ትክክለኛ ናቸው ለማለት ማስረጃ አይሆንም። ይህን ጉዳይ ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያ ﴾ አሳምሮ እና ጥቅም በሚሰጥ ሁኔታ ግልጽ እንዳደረገው ፣ ልምድን ማስረጃ በማድረግ የሽርክ አዳራሾችን ህጋዊ ማድረግ አይቻልም።

**በጥንታዊ ቅርሶች መዳረስ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ ተቃርኖዎች**

**በጥንታዊ ቅርሶች መዳረስ ሲባል የተፈለገው፡**

**ተወሱል፡** የሚለው ቃል በቋንቋ ጉጉት እና ፍላጎት ማለት ነው።

የቋንቋ ባለቤቶች ወደፍላጎት መዳረስ፣ እርሱን ለማረጋገጥ መገስገስ በሚል ጥቅል የሆነ ትርጉም ሰጠውታል።

**ተወሱል (መዳረስ) የሚለው ሸሪዓዊ ትርጉም ፤** በአምልኮ እና እርሱን በመታዘዝ ﴾ ነብያቶችን እና መልእክተኞችን በመከተል ወደአላህ መቃረብ ማለት ነው። አላህ ያዘዘውን በመተግበር ፣

ክልክል የሆነውን በመተው ከአላህ ውዴታ እና ጀነት እስኪደርሱ ድረስ ከአምልኮዎች በደነገገው ፣ ነብዩ ሙሐመድ በመጡበት ፤ አላህ በሚወደውና በሚቀበለው ተግባር ሁሉ - ዋጅባትም ይሁን ፣ ሸሪዓዊ የሆኑ ተወዳጅ ነገሮች - ወደአላህ ይዳረሳሉ።

**በሚከተለው ቃሉ አላህ እንዳዘዘው፥**

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ اتَّقُواْ اللّهَ وَابْتَغُواْ إِلَيهِ الْوَسِيلَةَ وَجَاهِدُواْ فِي سَبِيلِهِ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ﴾

**“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ወደርሱም መቃረቢያን (መልካም ስራን) ፈልጉ። ትድኑ ዘንድም በእርሱ መንገድ ታገሉ።”** *(አል’ማኢዳህ፡ 35)*

አሁን ከተወሳው ሸሪዓዊ ትርጉም ጋር የሚቃረኑ የተለያዩ ትርጉሞች ወደኋላ ከመጡ አካላት ተገኝቷል። ከዚህ በፊት ያወሳሁት የተወሱል ትርጉም ትክክለኛ የሸሪዓ ትርጉሙ ነው። በጥንታዊ ቅርሶች መዳረስ ቢድዓዊ በሆነው ሌላ ትርጉም እና ሶስተኛው ሽርካዊ ትርጉም ስር የሚካተት ይሆናል። ሁለቱ የሚከተሉት ናቸው፥

1. አላህን በሚለምን ሰው መሐላ -አላህን በመጠየቁ ፣ በተማጽኖው ፣ ወይም ደግ በሆነው ባሪያው ሀቅ ፣ በደጋጎች በረከት በማለት አላህን መማጸን ከኋለኞች የመጣው ቢድዓዊ መዳረስ የተፈለገው ይህ ነው።
2. ዱዓን በመፈለግ ፣ በመተናነስ ፣ ወደሚዳረሱበት አካል በመማለድ ወደሙታኖች መቃረብ ፣ በእነርሱ ወደአላህ መቃረብ ነው። ዱዓው ተቀባይነት እንዲያገኝ ፣ በእነርሱ ለመታገዝ ፣ ከጭንቅ ለመገላገል መዳረሻ አድርጎ መያዝ። ቋምጦ እና ፈርቶ እነርሱን መማጸን። ለእነርሱ ማረድ ፣ ለእነርሱ መሳል። የፍጡራንን ሀቅ አስመልክቶ አላህ ባልደነገገው መልኩ እነርሱን ከፍተኛ ደረጃ መስጠት። ከቀብር አምላኪዎች ዘንድ የተከሰተው ሽርክ አዘል የሆነው መዳረስ ይህ ነው።

## የተወሱል (የመዳረስ) ክፍሎች እና ሸሪዓዊ ብይኑ

ዑለሞች ከሸሪዓዊ ብይን አኳያ በሁለት ክፍል ከፍለውታል፥

1. **ሸሪዓዊ የሆነ መዳረስ፡** በኢማን ፣ በመታዘዝ ፣ ውብ በሆኑ መልካም ስራዎች ወደአላህ መቃረብ ማለት ነው። እርሱም የተለያየ አይነት ነው ፦

- በአላህ መልካም ስሞች እና ከፍተኛ በሆኑት ባህሪያቶቹ መዳረስ ፤ ለምሳሌ ፤ ከሀሳብ እና ከሀዘን (ነጻ እንዲያደርገው) ዱዓ ማድረግ
- **በኢማን እና በተውሂድ መዳረስ፡**
  **አላህ በተከበረው ቁርኣን እንደተናገረው፡**

﴿رَبَّنَا آمَنَّا بِمَا أَنزَلْتَ وَاتَّبَعْنَا الرَّسُولَ فَاكْتُبْنَا مَعَ الشَّاهِدِينَ﴾

**"ጌታችን ሆይ! ባወረድከው አመንን ፤ መልእክተኛውንም ተከተልን ፤ ከመስካሪዎችም ጋር መዝግበን" (አሉ)።** *(አል'ዒምራን፡ 53)*

- **በመልካም ስራዎች መዳረስ** ፤ ከተራራ ላይ ቋጥኝ ወርዶ የዋሻውን ቀዳዳ የደፈነባቸው ሰዎች ታሪክ ለዚህ ምሳሌ ነው።
- **ዱዓቸው ተስፋ በሚደረግ ፣ በህይዎት ያሉ ፣ አሁን የተገኙ ሷሊሆች ዱዓ መዳረስ** ፤ እርሱ ስለሚያከብራቸው ዱዓቸውን እና ሸፈዓቸውን አላህ ይቀበላቸዋል ከሚል አኳያ ሶሃቦች የነብዩን ﷺ ዱዓ እና ሸፈዓቸውን በመፈለግ መዳረሳቸው ለዚህ ምሳሌ ነው። በተጨማሪ የሙእሚኖች አሚር ዑመር ብን አልኸጧብ ﵁ በረሡል አጎት ዓባስ ﵁ ዱዓ መዳረሱም ለዚህ ሌላው ምሳሌ ነው።

ይህ ክፍል በጥንታዊ ቅርሶች መዳረስ የሚለውን አያካትትም። በጥንታዊ ቅርሶች መዳረስ ቀጣይ በምንመለከተው ሁለተኛው ክልክል ከሆኑት የመዳረስ ዓይነቶች የሚካተት ነው።

2. **ክልክል የሆነው ተወሱል፡** ሸሪዓ ካጸደቀው ትክክለኛ መዳረሻ ውጭ ወደአላህ መቃረብ ነው። ቁርኣንም ይሁን ትክክለኛው የነብዩ ﷺ ሱና ያልጠቀመው የሆነ መቃረብ ነው። ከሸሪዓው ብይን አኳያ ሁለት ቅርንጫፎች አሉት፡

**አንደኛው አይነት ፤ ቢድዓዊ መዳረሻ ፤** እርሱም ሸሪዓ ምንም አይነት ሐሳብ ባልሰጠበት መዳረስ ማለት ነው። ምሳሌ

1. አላህ ባልደነገገው ቢድዓ እና አዲስ ፈጠራ ወደአላህ መዳረስ። ባለቤቷ መልካም ስራ ናት ብሎ ያምናል። ነገር ግን እርሷ ምንም አይነት መረጃ የሌላት አዲስ ፈጠራ ነች።
2. በልቅና ፣ በክብር ፣ በበረካው እና በሐቁ አላህን መማጸን። **"አላህ ሆይ በነብይህ ክብርና ልቅና እንዲህ እንዲህ አይነት (ጉዳይ እንድትፈጽምልኝ) ...እጠይቅሀለሁ"** በሚለው አላህን መማጸኑ ለዚህ ምሳሌ ይሆናል። ወይም "አላህ ሆይ! በከሌ ሀቅ ይሁንብህ ምህረት አድርግልኝ" ወይም በሁርመቱ ወይም በአካሉ ወይም በእርሱ አሻራ እና ሌላም ምክንያቶችን በመዘርዘር ወደአላህ መዳረስ ወይም መረጃ በቁርኣንና በሐዲስ ያልመጡ መዳረሻዎችን ተጠቅሞ አላህን መማጸን።

**ይህ ቢድዓዊ የመዳረሻ አይነት ከአብዛኛው ኡለማ ዘንድ ሀራም ነው። ለሚከተሉት ምክንያቶች ይህ አይነት መዳረሻ ወደሽርክ ያደርሳል። ከእነርሱ መካከል ፦**

1. እርሷ አላህ እና ረሡል ﷺ ያልደነገጓት የሆነች ቢድዓዊ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት የሌላት አምልኮ ነች።
2. ሶሃቦች በአላህ ሸሪዓ ፣ በረሡል ﷺ ሱና ከሰዎች ሁሉ በጣም አዋቂዎቹ እነርሱ ናቸው። በኢማንም ፣ በመውደድም ፣ በመከተልም በጣም እውነተኞች ናቸው። ሸሪዓዊ ቢሆን ኖሮ በእርሱ ለመስራት እኛን ይቀድሙን ነበር። በተለይም ወደዚህ ነገር የሚያነሳሱ ጉዳዮች ከተገኙ።
3. በአላህ ላይ አውቃለሁ ብሎ ፍርድ መስጠት ነው። አደበ-ቢስነት ፣ የእምነት ቅለት ነው። ካለበለዚያ የአንድ ሰው ልቅና ወይም አካል በአላህ ላይ ሐቅ ወይም አሻራ ያላት መሆኗን በምን ማወቅ እንችላለን? ወይም በአላህ ላይ ጉዳይ ለማስፈጸም አስገዳጅ መሆኗን በምን ማወቅ እንችላለን? ለፍጡር አላህ በነፍሱ ላይ ግዴታ ያደረገው ካልሆነ በቀር በአላህ ላይ ሐቅ የለውም። የደጋግ ሰዎች አካላት ፣ ልቅና እና አሻራ ከዚህ ውስጥ አይደለም።
4. ከፈጣሪ ዘንድ ያለው የደጋጎች ልቅና ፣ አካል እና አሻራ ፤ ልክ ከፍጡራን ዘንድ እንዳለው

የፍጡራን ልቅና እና አካል አይነት አይደለም።

2. በፍጡራን ልቅና ፣ ደረጃ እና በልቅናው ዱዓን መፈለግ መካከል ምንም አይነት ትስስር የለውም። ትስስሯ ትክክል የምትሆነው የዚህ ልቅና ባለቤት በቀጥታ ጌታውን እና ጠባቂውን አላህን መማጸኑ ነው።

**ሁለተኛው አይነት ፡ ሽርክ የሆነው መዳረስ፡** እርሱም ሸርዑ በከለከለው የመዳረሻ አይነት መቃረብ ነው። ለምሳሌ፡ የሚዳረሰው አካል በአምልኮ አይነቶች ወደዚያ ወደሚዳረስበት አካል መቃረቡ ነው። በፍጡር እና በፈጣሪ መካከል አሻራን እና አማካኞችን መያዝ አንዱ ምሳሌ ነው። ከአይነቶቹ የሚከተሉት ይገኙበታል ፡

- ከእነርሱ ሀጃዎችን በመፈለግ ወደ ጣዖታት ፣ ሀውልቶችና ቀብሮች ቅርሶች መቃረብ ፤
- የጃሂልያ ባለቤቶች በነበሩበት አይነት ሙታኖችን መጥራት ፣ የጭንቅ ሰዓት ድረሱልን ማለት ፣ ማረድ እና የመሳሰሉ የሽርክ ተግባራትን መፈጸም ፤

**እነርሱን አስመልክቶ አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مِن دُونِهِ أَوْلِيَاءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَى إِنَّ اللَّهَ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فِي مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي مَنْ هُوَ كَاذِبٌ كَفَّارٌ﴾

**"እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣኦታትን) ረዳቶች የያዙት "ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም" (ይላሉ)። አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህም እርሱ ውሸታም ከሐዲ የሆነን ሰው አያቀናም።"** *(አዝ'ዙመር፡ 3)*

**ማለትም ፡** እነርሱን በዱዓቸው ፣ በጥያቄያቸው ፣ ከእነርሱ ሸፈዓን በመፈለጋቸው መዳረሻ አድርገው ያዟቸው። በዚህም ተግባራቸው ወደአላማቸው መዳረሻ ፣ እነዚህ አማላክቶች ከአላህ ዘንድ አማላጅ ይሆኑናል ፣ ወደአላህ ማቃረብን ያቃርቡናል ብለው አሰቡ።

የሙሽሪኮችን ዲን አላህ ውድቅ አደረገባቸው። ወደአላህ ማቃረብን ያቃርቡናል በሚለው

ንግግራቸው በውሻታምነት አላህ ገለጻቸው። እነርሱን በመለመናቸው ፣ ድረሱልን በማለታቸው እና በመሳሰሉ ከአንዳንድ ጣዖቶች ዘንድ በመሄድ ከአላማችን ያዳርሱናል የሚል የሽርክ እምነት በማመናቸው ምክንያት በከሀዲነት ፈረጃቸው።

**እነርሱን አስመልክቶ አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿وَيَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللّهِ مَا لاَ يَضُرُّهُمْ وَلاَ يَنفَعُهُمْ وَيَقُولُونَ هَـؤُلاء شُفَعَاؤُنَا عِندَ اللّهِ قُلْ أَتُنَبِّئُونَ اللّهَ بِمَا لاَ يَعْلَمُ فِي السَّمَاوَاتِ وَلاَ فِي الأَرْضِ سُبْحَانَهُ وَتَعَالَى عَمَّا يُشْرِكُونَ﴾

**"ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውን ይግገዛሉ። "እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ። አላህን በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን በላቸው ። ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ ፤ላቀም።"** (ዩኑስ፡ 18)

ከአንዳንድ ቅርሶች ዘንድ የሚከሰተው ተወሱል እና በአላህ እና በእነርሱ መካከል አማካኝ አድርጎ መያዝ ከትልቁ ሽርክ ፣ ከኢስላም የሚያስወጣ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

**ሸይኹል ኢስላም ﵀ በመጅሙዕ አልፈታዋ ኪታብ (1/124) ላይ ለሚከተለው የአላህ ቃል ማብራሪያ ሰጧል፡**

﴿وَلاَ يَأْمُرَكُمْ أَن تَتَّخِذُواْ الْمَلاَئِكَةَ وَالنِّبِيِّيْنَ أَرْبَابًا أَيَأْمُرُكُم بِالْكُفْرِ بَعْدَ إِذْ أَنتُم مُّسْلِمُونَ﴾

***"መለእክትንና ነብያትንም አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ (አይገባውም)። እናንተ ሙስሊሞች ከሆናችሁ በኋላ በክህደት ያዛችኋልን?"*** (አል'ዒምራን፡ 80)

*"መላኢካን ፣ ነብያትን ጌታ አድርጎ መያዝ ክህደት ነው። መላኢካን ፣ ነብያትን ለመማጸን ፣ በእነርሱ ላይ ለመመካት አማካኝ አድርጎ መያዝ ፤ ጥቅሞችን እንዲያመጡለት ፣ ጉዳትን እንዲከላከሉለት መጠየቅ ፤ ለምሳሌ ፡ ወንጀሉ እንዲማር ፣ ልቦች ወደ ቅን ጎዳና እንዲመሩ ፣ ከጭንቅ እንዲገላግሉት ፣ የችግር (ቀዳዳዎች) እንዲዘጉ መጠየቅ ክህደት ለመሆኑ የሙስሊሞች ስምምነት ነው።"*

**በቅርሶች የመዳረስ ጥመት ምክንያቶቹ**

**"ተወሱል"** (መዳረስ) በትርጉሙ ዙሪያ ጥቅልነት ፣ መመሳሰል እና የመጋራት መቃረኖች ምክንያት በሰዎች ግንዛቤ ላይ ብዥታ መደበላለቅና መዋዥቅ የተከሰተበት የዲን ጉዳይ ሆኗል። ይህ የመጣው በቁርኣን እና በሀዲስ ፣ በሰለፎች ግንዛቤ እና በዓረበኛ ቋንቋ ዙሪያ የእውቀት ማነስ ምክንያት ሊሆን ይችላል ወይም ከአንዳንድ የጥመት ዳዒዎች በኩል ግለሰባዊ አላማን ለማሳካት ዝንባሌን በመከተል ሊሆን ይችላል።

በተወሱል ዙሪያ ጉልህ ከሆኑት የጥመት ሰበቦች መካከል ትክክለኛ ካልሆነ ንጽጽር በመነሳት እርሱን እና ሌላውን መስአላ መቀላቀል ነው። ይህ በሚከተለው መልኩ መታየት ይችላል ፡

1. ተወሱልን ሸሪዓዊ በሆነው ተበሩክ ማነጻጸር

2. ተወሱልን በኢስቲጋሳ ማነጻጸር

3. ተወሱልን ሸሪኣዊ በሆነው ሸፋዓ ማነጻጸር

እነዚህን ሶስቱን ተጨማሪ ዝርዝር እውቀት የፈለገ ከዋናው ኪታብ ከገጽ 510-515 ይመልከት።

**በጥንታዊ ቅርሶች ተወሱል ማድረግ ፍጻሜው**

በቅርሶች መዳረስ በሸሪዓ ክልክል መሆኑ ፣ ድርጊቱን በሚፈጽመው አካል ላይ አክሳሪ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ፣ አስከፊ መዘዝ እንደሚያመጣ ከዚህ በፊት ማብራሪያው አልፏል።

**ከእነዚህ ጉልህ ተጽዕኖዎች እና ፍጻሜዎች የሚከተሉት ናቸው፦**

1. ቢድዓዊ የሆነው ተወሱል ትልቁ ሽርክ ላይ ለመውደቅ መዳረሻ ነው። ይህ ከመቃብር አምላኪዎች ፣ ከቅርሶች ዘንድ ከሚሰባሰቡ ሰዎች ዘንድ ይታያል ፣ ይታወቃል። እነርሱ ሸሪዓዊ መዳረሻ በሚል የራስ አስተያየት በነብያቶች ፣ በዷሊሆች ፣ በታላላቅ ሰዎች ተወሱል ይበቃል ብለው መሞገታቸው እነርሱን ወደመማጸን ፣ በእነርሱ ይሁንብህ ብለው አላህን ወደመለመን ፣ በጭንቅ ሰዓት ድረሱልን ወደማለት እና ምንም ሳያሻርኩ ፍጹም አምልኮት

ለአላህ እንጅ ለማንም የማይደረገውን ዒባዳ አሳልፈው ወደመስጠት አድርሷል።

2. **መጥፎ ከሆኑ ቢድዓዎች ላይ መውደቅ ፡** ይህም ክልክል የሆነውን የመዳረሻ አይነት ሸሪዓዊ በሆነው መዳረሻ ስር በማስገባት ነው። ለምሳሌ ፡ በፍጡራኖች ልቅናና ክብር ወይም አሻራ መጠየቅ። ለአህለሱና ተቃራኒ ከሆኑ አካላት ዘንድ እንጅ ከማንም ያልመጣ ቢድዓ ነው። ይህ ወደአላህ ጥላቻ ፣ ቁጣ እንዲሁም አሳማሚ ቅጣት ያደርሳል ። ሰላምና አፊያን እንጠይቃለን።

**ቅርስን ህያው ማድረግን ተከትለው የሚመጡ አምልኮታዊ ተቃርኖዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡**

ንግግራዊ ፣ ተግባራዊ እና አምልኮታዊ እምነቶች ከሸሪዓው ጋር ጠንካራ ትስስር አላቸው። አንድ ሙስሊም ከቁርኣን እንዲሁም ከትክክለኛ ሱና ማስረጃ ይዞ እንጅ ከአምልኮ አይነቶች በአንድ የአምልኮ ዘርፍ አይሰማራም።

ያለሸሪዓዊ ማስረጃ ወደአንድ አምልኮ ከተሰማራ ያ ተግባር ለሱና ተቃራኒ ይሆናል። በቢድዓ ብይን ውስጥ ይገባል። ስህተቱ በዚያ ስራ ላይ ትክክል ባለመሆኑ እና ተቀባይነት በማጣቱ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ወንጀል እና ሀጢያትን ያስከትላል።

ከአንዳንድ ቅርሶች ዘንድ የአምልኮ አይነቶች የንግግር ፣ የተግባር ፣ የልባዊ አምልኮቶች ዓይነቶች ይከሰታሉ። እነዚህ ሁሉም በተለያየ አምልኮ እና ወደአላህ መቃረብ አይነቶች በአንድ ጊዜ ሊከሰቱ ይችላሉ። ይህ አምልኮ በሸሪዓ ያልጸደቀ ሊሆን ይችላል ወይም መሰረቷ ሸሪዓዊ በሆነ መረጃ ጸድቆ ነገር ግን በውስጧ ከሸሪዓ መልኳ በሚያወጣ መንገድ መቀያየር ፣ ድንበር ማለፍ ፣ መለዋወጥ የደረሰባት ሊሆን ይችላል።

በዚህ መሰረት ከእነዚህ ቅርሶች ዘንድ ወደአላህ መቃረቢያ በሚል የሚተገበሩት የቢድዓ ተግባራት ተደርገው ይቆጠራሉ። ወደ ሽርክም ሊደርሱ ይችላሉ።

**በሚወሩ የህዲስ አሻራዎች ዙሪያ ጎልተው የሚስተዋሉ አምልኮታዊ ተቃርኖዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡**

በወረቀት ፣ በቆዳ እና በመሳሰሉ ተጽፈው የተገኙ የተወሩ የሐዲስ አሻራዎች ናቸው። ለምሳሌ ፡ ዱዓዎች ፣ ዚክሮች እና የተፈቀዱ ዱዓዎች ናቸው። ወይም ተማኢም ወይም ሂርዝ ወይም ሀጅብ ተደርገው በረካ እየተፈለገባቸውና ከሰዎች አይን ፣ ከመጥፎ ነገሮች ትከላከላለች ወይም ሲያንጠለጥሏት መልካም እና በረካ ታመጣለች ተብሎ እየታመነባቸው ያሉ ሊሆን ይችላል።

**የአላህ መልእክተኛ የሚከተለውን ተናግረዋል ፡**

"من علق شيئا وكل إليه" حديث حسن أخرجه الحاكم في مستدركه

"አንዳች ነገር ያንጠለጠለ ወደርሱ ይጠጋል"

ኢማም አህመድ በሙስነድ ኪታባቸው በትክክለኛ ዘገባ የሚከተለውን ተናግረዋል ፡

"من علق تميمة فقد أشرك"

"ሂርዝ ያንጠለጠለ በእርግጥ አጋራ" *(አህመድ፣ 17422)*

እነርሱ መጥፎን ትከላከላለች ብለው ከአላህ ውጭ በመፈለጋቸው ነብዩ ﷺ ከሽርክ ወይም ማጋራት ቆጥረውታል።

ይህ የተሰራጨና ሀራም የሆነ አምልኮታዊ ተቃርኖ አይነት ነው። ጉዳትን ለመከላከል ሸሪዓዊ አሻራዎችን ማንጠልጠል ከተከለከለ ፣ ሽርክ አዘል የሆነው ዱዓ ድግምታዊ የሆነው ጦላሲም ክልክል መሆኑ የሚያነጋግር አይደለም።

**ከነብዩ አካል በተነጠሉ ወይም በተያያዙ አሻራዎች ምክንያት ከሚከሰቱ አምልኮታዊ ተቃርኖዎች መካከል ጉልህ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፤**

ጥቅም ታመጣለች ፣ ጉዳትን ትከላከላለች በሚል እምነት በእርሷ መዳረስ ፣ ለእርሷ መዋረድና መተናነስ ፣ እንደቅዱስ መመልከት ፣ በእርሷ መተሻሸት ፣ መሳም ፣ እርሷን መማጸን ነው። እንዲሁም ይህ አሻራ በትክክለኛ ሰነድ ያልተረጋገጠ ከመሆኑ ጋር ከጥፋት ታድናለች ፣ ከበሽታዎችና ህመሞች ትፈውሳለች ፣ ለሰይጣን መጠበቂያ ትሆናለች ፣ ለተጨናነቀ ጥቅም ትሰጣለች ፣ ከሽፍታ ታድናለች ፣ ከእርሷም በረካ ይገኛል ብሎ ማመን ነው።

**በነብዩ የቅዱሳ ቦታዎች አሻራዎች ላይ አምልኮተዊ ተቃርኖዎች መካከል ጉልህ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው ፡**

1. ቅዱሳን ቦታዎችን ከሌሎች በደረጃ ብልጫ እና በረከት ይገኝባቸዋል በሚል እቃ ጭኖ ለጉብኝት ሰፈር መውጣት።
2. የነብዩ ቅዱሳን ቦታዎች በሚል ከእርሷ ዘንድ ሶላት መስገድ እና ቁርአን መቅራት ።
3. ከነብዩ ጋር ትስስር አላቸው ብለው ከሚያስቧቸው ተራሮችና ዋሻዎች ላይ መውጣት። ኑር ፣ ሰውር ፣ ሂራእ እና የመሳሰሉ ተራራዎችና ዋሻዎች ውስጥ በረካ ይገኛል ፣ ከሌሎች ቦታዎች በደረጃ ይበልጣሉ በሚል እምነት ይተሻሻሉ ፣ ዱዓ ያደርጋሉ ፣ ይማጸናሉ ፣ በረከትን ተስፋ ያደርጋሉ።
4. በረካ እናገኛለን ፣ ጥቅም ያመጣሉ ፣ ከእኛ ላይ ጉዳትን ይከላከላሉ ፣ የምንፈልገው ጉዳይ ተፈጻሚ ይሆናል በሚል እምነት ከዛፎች ፣ ከዱንጋዮች ላይ ቁርጥራጭ ጨርቅ ፣ ክርና የመሳሰሉትን ይቋጥራሉ ፣ ያስራሉ።
5. ረሡል ﷺ በእነዚያ ቦታዎች ላይ አልፈውበታል ወይም ቆይተውበታል ወይም ሲያልፉ ሰግደውበታል ተብሎ በሚታሰቡ ቦታዎች ላይ መስጅዶችን መገንባት ፣ በቦታዎች ላይ ቁባዎችን መስራት።

**በጠፉ ህዝቦች ቅርሶች ላይ ከሚከሰቱ አምልኮታዊ ተቃርኖዎች መካከል ጉልህ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፡**

በቅድሚያ ከልብ ተግባራት ጋር ትስስር ስለሚኖራቸው -ለምሳሌ ፡ መውደድ ፣ ማላቅ ፣ መወዳጀት ፣ ከሽርክ እና ከባለቤቶች አለመራቅ እና የመሳሰሉትን- የአምልኮ አይነቶች ግልጽ ላይሆኑ ይችላል።

እነዚህ እምነቶች በልቦና ውስጥ ተደላድለው አይቀመጡም ፣ ለሸሪዓው ተቃራኒ የሆኑ የአምልኮ አይነቶችና ቅርጾች በአካል ላይ ይፋ የሚሆኑ ቢሆን እንጅ።

**ከጠፉ ህዝቦች ቅርሶች አምልኮታዊ ተቃርኖዎች ጉልህ ከሆኑት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡**

እርሷን ቅዱስ አድርጎ ወደመመልከት በሚያደርስ ሁኔታ ለማላቅ ፣ በእርሷ ላይ ለመገንባት ወደቦታዋ እቃ ጭኖ ለጉዞ መንቀሳቀስ።

ይህን ጉዳይ ሊከሰት የማይችል እንግዳ ወይም ሊሆን የማይችል አድርገን እንዳናስበው። የሀጀርይ ጃሂልያ ባለቤቶች ፡ ኢሳፍ እና ናኢላ የሚባሉ ጣዖቶችን አምልከዋል ! !

ሰዎች እነዚህን ሁለት ጣዖቶች አዋራጅ በሆነ ተግባራቸው አላህ ወደዲንጋይ በመቀየር የቀጣቸው እንደሆኑ በማስተንተን እና በመገሰጽ ነበር የሚመለከቷቸው። ነገር ግን ከጊዜ በኋላ አመለኳቸው።

**ከጃሂልያ እና ከጣዖት አምላኪዎች አሻራዎች አምልኮታዊ ተቃርኖዎች መካከል ጉልህ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው ፡**

1. የጃሂልያን ነጠኝነት ግልጽ ለማድረግ ፣ የቀደምት የታሪክ ስልጣኔን ህያው ማድረግ በሚል የጣዖትና የጃሂልያን ቅርሶች ከሞቱበት እንዲነሱ መቀስቀስ። ወደርሷ ፍቅር እና ታማኝነት መጥራት። በነፍሶች ውስጥ ኩራት ፣ እርሷን ማላቅ እና ክብር እንዲኖር ማነሳሳት።
2. ከመግባታቸው በፊት -ካሉበት ቦታ- ለጣዖቶች ቁርባን ማቅረብ ፣ ስጦታዎችን መስጠት። በካፊር አገሮች አዲስ ከተፈጠሩ ነገሮች ቱሪስቶች በኤግዝቢሽን መልኩ የእምልኮ ቦታዎችን ከሩቅ አገር ተነስተው ሊጎበኙ ሲመጡ ትንሽ እንኳ ብትሆን ስጦታዎችን በግዥ መልክ ገዝተው ያበረክታሉ። ከገዙ በኃላ ወደቦታው ሲገቡ ልዩ በሆነው ቦታ ያስቀምጡታል። ይህ ከኤግዚቪሽኑ ወይም ከአውደ-ርዕዩ ለቀሙት ጣዖቶች ወይም ሀውልቶች እንደልዩ ስጦታ መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል።
3. ፒራሚዶች ባሉበት ቦታ እንደተለመደው ጎብኚው ከመግባቱ በፊት ሳይወድ በግድ እንዲጎነበስ ለማድረግ የጣዖቱ መግቢያ በር ጠባብና ጣራው አጭር ተደርጎ የተሰራ ነው። ጎብኝዎች ሲገቡ ለጣዖቱ ዝቅ በማለት ፣ ለጣዖቱ የክብር ሰላምታ አድርገው ይገባሉ።

ሌሎችም ለተውሂድ መሰረትና ሙሉነት ተጻራሪ የሆኑ ልባዊ ወይም ንግግራዊ ወይም የአምልኮ መገለጫ አይነቶች አሉ።

**በቀብር እና በመሸሐድ አሻራ ላይ ከሚከሰቱ አምልኮታዊ ተቃርኖዎች መካከል ጉልህ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፤**

1. ቀብሮችን ማላቅ ፣ መሻሂዶችን እና የሚዘየሩ ቦታዎችን ማነቃቃት ፣ በቁሳዊና በሞራላዊ ድጋፎች መደገፍ።
2. የወልዮችን ፣ የሷሊሆችን ቀብሮች ይፋ ማድረግ እና ከፍ አድርጎ መስራት። እነዚህን ቦታዎች መስጅዶች ፣ መሻሂዶች ፣ የሚዘየሩ ቦታዎች አድርጎ መያዝ።
3. የታላላቆችን ቀብሮች ቁባዎች አጠንክሮ መስራትና በእርሱም ላይ መገንባት ፤ ማስረጃዎችን ማኖር ፣ በኖራ መለቅለቅ። ጽሁፎችን በእርሱ ላይ መጻፍ ፣ መብራትና ሻማዎችን ማብራት።
4. የጠፉ ቀብሮችን በቅርስ መልኩ ህያው ማድረግ ፤ ይፋ እንዲሆኑ መንቀሳቀስ እና ለእርሱም ትኩረት መስጠት።
5. የቢድዓ ቀብሮችን እና የሽርክ መሻሂዶችን ለመጎበኘት መቀስቀስ። በዚህ ላይ “ወልዮችን ማላቅ አለብን ፣ በሐቃቸው ልንቆም ይገባል” በሚል ሽፋን የጥመት ተጣሪዎች ከባድ ጥረቶችን ያደርጋሉ።

**መቃብር ከሚጎበኙ ሰዎች ዘንድ የሚከሰቱ አምልኮታዊ ተቃርኖዎች መካከል ጉልህ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፤**

1. በመቃብር ፣ በመሻሂድ ፣ ልቦች መተሳሰራቸው እና እነርሱንም ማላቅ። በተቀበሩት አካላት መዳረስ። በመቃብራቸው አፈር በረከት ይገኛል ብሎ ማመን ፤ በእርሱም መተሻሸት ፣ በረከት ለማግኘት ቦታውን መሳም።
2. ለአምልኮ የጉዞ ዝግጅት አድርጎ ወደመሻሂዶች መንቀሳቀስ። የአላህ ነብይ ሁድ መቃብር ነው ከሚባለው ቦታ እንደሚስተዋለው ቢድዓ በሆኑ የአምልኮ ስርዓቶች ላይ መሰማራት።

1. ከመቃብሮችና መሻሂዶች ዘንድ ወደቂብላ ዞሮ የዱዓን ስኬታማነት መጠባበቅ። ቦታዎቹ ለዱዓ ተቀባይነት ምቹ ናቸው ብሎ ማመን። ሶላት መስገድ ፣ ቁርኣን መቅራት ፣ ለእርሷ ወይም ወደርሷ ማረድ።
2. ለቀብር ባለቤቶች ቁርባን ፣ ስለቶች እና ስጦታዎችን ማቅረብ። በህይዎት ላለው እንደሚደርሰው ለሙታንም ይደርሳል ብሎ ማመን።
3. ሙታኖችን ድረሱልን ማለት። ከጭንቅ እንዲገላግሏቸው ፣ ወንጀላቸውን እንዲምሩ ፣ በጠላት ላይ እንዲረዱ ፣ መከራዎችን እንዲገፈትሩ እነርሱን መማጸን።
4. በመቃብሮች ዙሪያ መዞር ፣ ማልቀስ ፣ ራስን ማስተናነስ ፣ የሚፈልጉትን ጉዳይ መጠየቅ። በአጥሮቿ ፣ በመጋረጃዎቿ መተሻሸት። ጽሁፎችን ፣ ሰንሰለቶችን እና የመሳሰሉ ነገሮችን በቀብር ዙሪያ ማንጠልጠል።
5. የመቃብር ዚያራ ቀን መወሰን። ሸዕባን ግማሽ ሌሊት ፣ በዒድ ቀን መጀመሪያ ፣ በሸዋል ስምንተኛ ፣ ከጁሙዓ በኋላ እና አላህ ማስረጃ ያላወረደባቸው አዳዲስ የተፈጠሩ ክብረ በዓላት ማዘገጀት።

ይህ ከአምልኮታዊ ተቃርኖ አይነቶች መካከል ውስን የሆኑትን አጠር ባለ መልኩ ነው ያወሳሁት። ካለበለዚያ ከአላህ ውጭ ከመቃብሮች እና መሻሂዶች ላይ የሚመለኩ አምልኮዎችን እንዘርዝር ብንል በርካታ ናቸው። ሰዎች ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ጣዖታት ላይ ድንበር እስከማለፍ ደርሰዋል። በመቃብሮች መካከል መሻሂዶችን ፣ መስጅዶችን ገንብተዋል። ወደርሷ ይሰግዳሉ ፣ እርሷንም ያልቃሉ። ይህ ተግባራቸው ደግሞ ሽርክ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

የተቃርኖዎች ብይን በአንድ ደረጃ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባዋል። ደረጃቸው የተለያየ ነው። ከፊሎቹ ግልጽ እና ትልቁ ክህደት ሲሆን ሌሎች ደግሞ ከእርሱ በታች የሆኑ ቢድዓዎች ናቸው። ነገር ግን በዲን ውስጥ ማንኛውም ቢድዓ ትንሽ እንኳ ብትሆን በሸሪዓ ሀራም መሆኗን ማወቁ ግዴታ ነው። አንዳንዶች እንደሚገምቱት ቢድዓ ሀራም (እርም) እንጅ ከረሀ የሚባል የለም።

**ለዚህ ማስረጃው የረሡል ﷺ ቃል ነው።**

"كل بدعة ضلالة وكل ضلالة في النار" حديث صحيح

"ሁሉም ቢድዓ ጥመት ነው ፤ ሁሉም ጥመት ደግሞ የእሳት ነው" *(ሙስሊም፡ 867)*

በዚህ ምክንያት የቢድዓ ጉዳይ በጣም አደጋ ነው። አብዛኛው ሰው ከእርሷ በዝንጋታ ላይ ከመሆን አልተወገደም። በዚህ ላይ ለማወቅ ፍላጎት ያለው የለም በቁርኣን እና በሱና አጥብቀው የያዙ የእውቀት ባለቤቶች እንጅ።

አሁን የተወሱት የአምልኮት ተግባራት ዓይነቶች ረሡል ﷺ እንዲሁም ከሶሃቦች አንድም አካል ያልሰሩት የሱና ተቃራኒ ነው። ረሡልም ﷺ ይሁኑ የተከበሩት ሶሃቦች ለዲን ልቅና በመስጠት ብርቱዎች ናቸው። በእርሱም ላይ ከሰዎች በጣም ፍላጎት ያላቸው ናቸው። መልካም ቢሆን ኖሮ ወደርሱ ይቀድሙን ነበር።

**በርበህሪ ﷺ በሸርህ አስ'ሱና ገጽ (24) ስለቢድዓ እና አደገኛነቱ የሰጠው ማብራሪያ ምን ያማረ! ምን ጠቃሚ አደረገው!**

**የሚከተለውን ተናገረ፣**

*"ከነገሮች ትናንሽ ፈጠራዎችን ተጠንቀቅ ፤ አነስተኛው ቢድዓ ትልቅ ሆኖ ይመለሳል ፤ በዚህ ኡመት የተፈጠረች ማንኛዋም ቢድዓ በመጀመሪያ ሐቅ መስላ ትንሽ ሆና ጀመረች ፣ በውስጧ የገባው ሰው ተሸወደ ፤ ከዚያም ከእርሷ መውጣት አልቻለም ፤ ተለቀች ፣ በእርሷ የሚያምኑባት እምነት ሆነች ፤ በዚህ ምክንያት ቀጥተኛውን መንገድ ተቃረነ ፤ ከኢስላም ወጣ።*

*-አላህ ይዘንልህና- በዘመንህ ንግግሩን የሰማሃውን አካል ሁሉ ተመልከት ፣ አትፍጠን ፣ የአላህ መልእክተኛ ፣ ሶሃቦች በእርሱ ተናግረውታል የሚለውን እስከምትመለከትና እስከምትጠይቅ ከእርሱ በአንዳች ነገር አትግባ። ከእነርሱ ወሬ ካገኘህ በእርሱ አጥብቀህ ያዝ። ለአንዳች ነገር ብለህ አትለፈው። በእርሱ ላይ አንድንም አትምረጥ- እሳት ውስጥ ትወድቃለህና።*

*በሁለት መልክ ከመንገድ መውጣት እንዳለ እወቅ፣*

***አንደኛው ፡*** *መልካምን እንጅ ሌላን ሳይፈልግ ከመንገድ የተንሸራተተ ሰው ነው። በስህተቱ አይከተሉትም - እንህ እርሱ ጠፊ ነውና።*

***ሌላው ፡*** *ሀቅን እምቢ ያለ ፤ ከእርሱ በፊት የነበሩትን አላህን ፈሪዎች የተቃረነ ነው። እርሱ ጠማማ ፣ አጥማሚ ነው። በዚህ ኡመት አመጸኛው ሰይጣን ነው። ታሪኩን ለእነርሱ ግልጽ ማድረግ ፤ በእርሱ ቢድዓ ውስጥ ሌላው እንዳይወድቅ እና እንዳይጠፋ። እርሱን ሳወቀ ከእርሱ ሰዎችን ማስጠንቀቅ የተረጋገጠ ነው።*

*- አላህ ይዘንልህና - እወቅ። ተከታይ ፣ እውነት ባይ ፣ ሙስሊም እስከሚሆን ድረስ የአንድ ባሪያ እስልምናው አይሟላም። ከኢስላም የሙሀመድ ሶሃቦች ያልበቁን አንድ ነገር የቀረ (ያልተሟላ) አልለ የሚል አመለካከት ያለው በእርግጥ እነርሱን ውሸት አላቸው። እነርሱን በመተቸትና በመከፋፈል በእርሱ ይብቃ። ይህ ሙብተዲዕ ፣ ጠማማ አጥማሚ ነው። በኢስላም ከእርሱ የሌለን አዲስ ፈጣሪ ነው።"*

**ኢማም ማሊክ ﵀ የሚከተለውን ተናግሯል ፡**

***"لا يصلح آخر هذه الأمة إلا بما صلح به أولها فما لم يكن يومئذ دينا لا يكون اليوم دينا"***

*"የመጀመሪያው በተስተካከለበት እንጅ ፣ ይህን ኡመት የሚያስተካክለው የለም። ያን ጊዜ ዲን ያልነበረ አሁን ዲን ሊሆን አይችልም።"*

የሚከተለውን ንግግር ተናጋሪ በሆነው ወዳጃችን ነብያችን ላይ ሶላት እና ሰላምታ ይስፈን፡

**"ما تركت شيئا يقربكم من الجنة ويباعدكم عن النار إلا قد بينته لكم"** أخرجه عبد الرزاق في مصنفه ، ينظر : السلسلة الصحيحة (ح7/67/2866)

"ወደጀነት የሚያቃርባችሁ ፣ ከእሳት የሚያርቃችሁ አንድም ነገር አልተውኩም ፣ ለእናንተ ያብራራሁ ቢሆን እንጅ።"

**ቅርሶችን ህያው በማድረግ ለሚመጡ ጉዳቶችና እና የዓቂዳ ተቃርኖዎች ሰበቦች፡**

የቅርስ ህያው መሆን ፈተና ብቅ ያለው በኑህ ህዝቦች ነበር ከዚያም በጠፉ ማህበረሰቦች ሁሉ

ተሰራጨ። በዓድ ፣ በሰሙድ ፣ በመድየን ፣ ከዚያም በግሪክ ፈላስፎች ፣ በአይሁድ በነሷራ ፣ በዓረብ ባህረ ሰላጤ እስከሚደርስ ተሰራጨ።

በቅርስ ከተፈተኑ ህዝቦች ውጤቱ እና ስርጭቱ ከባድ የሆነው የመቃብሮችን ቅርሶች ህያው በሚያደርጉና የተቀበረውን በሚያልቁ አካላት በኩል ያለው ነው። የሙስሊሞችን ሶፎች ሳይቀር ጠራርጋ በምትጥለው ፈተና እንኳን የቢድዓ ተጣሪ ቀርቶ ተራውና ጃሂሉ ህብረተሰብ የተፈተነበት ነው።

በኢስላም ይህን በሽታ በመጀመሪያ ይፋ ያደረጉት በእርሱም የተፈተኑት የዚህ መከራ መሰረት የሆኑት ራፊዷ ናቸው። በጦሪቃዋ አማካኝነት በሱፍያ ውስጥ የተሰራጨውም በእነዚህ አማካኝነት ነው።

ከሚታዩ ቅርሶች ጋር በተያያዘ በፊረቆች ላይ የሚስተዋለው አብዛኛው ተቃርኖ በሚወሩ ሀዲሳዊና ነብያዊ ቅርሶች ላይ በሚፈጠረው ማጓደል ነው። ከጥመታቸው የመነጨ አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ነው። ልቦች በቢድዓ ከተጠመዱ ከሱና ማፈንገጣቸው የታወቀ ነው።

አላህ ሽቶለት በተውሂድ ላይ የዘወተረ ካልሆነ በቀር ይህ ፈተና በባሮች እና በየአገሩ አጽናፍ ተሰራጭቷል።

**ማጠቃለያ**

የቀጥተኛውን ጎዳና ተቃራኒ ሁኔታዎች ላስተዋለ በሚታዩ ቅርሶች ትኩረት ስለሰጡና ስለሚያልቋት ነው። በትክክለኛ ሁኔታ የተወሩትን ፋናዎች ቸል አሉ ፤ አራቆቱ። ጥርጣሬ ያለውን ምስላዊ ቅርስ ያጸደቀ በእርሱ ላይ ትኩረት አድርጎ እርግጠኛ የተወሩ አሻራዎችን ለተቃወመ እና ቸል ላለ ያስደንቃል !

**ቅርሶችን ህያው በማድረግ ለሚከሰቱ የዓቂዳ ተቃርኖዎች ምክንያቶች**

አላህ ሰዎችን ባሉበት መሰረት በተውሂድ ላይ ፈጠረ። ነገር ግን ሰዎች ከዚህ መሰረት በመንሻፈፋቸው ምክንያት ቢድዓ እና ሽርኮች ላይ ወደቁ። ቅርሶችን ህያው ማድረግ ጀመሩ ፣ ይህን ተከትሎ ጥመቶች እና ተቃርኖዎች ተከሰቱ። ከነዚህ የተቃርኖ ሰበቦች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡

1. ሩሡሎች የተላኩበትን -ተውሂድን የማረጋገጥ ፣ ሽርክን እና መዳረሻዎቻቸውን ቆርጦ የመጣል- እውነታ አለማወቅ። የዲን ህግጋቶችን ፣ የዓረብኛ ቋንቋዎች ሐቆች እና ስልቶችን ባለማወቅ የተነሳ ጃሂል የሆነው አካል ሙሽሪኮችን መመሳሰል ምንም ችግር የለውም ብሎ ይመለከታል።

   ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው ማህይምነት ለተቃርኖዎች ሁሉ ዋና መሰረት ሌሎቹ ደግሞ ቅርንጫፎቹ ሆነው እናገኛቸዋለን።

2. ዝንባሌን መከተል ፤ በግል አስተያየት ላይ መደገፍ በጥመት እና በስሜት መጓዝ መሰረቱ ነው። ከስሜታቸው ጋር የሚገጥመውን ይይዛሉ ፣ ያልገጠመውን ደግሞ ይተዋሉ። ዝንባሌን የተከተለ ሰው አላማው እስከሚሳካ ሸሪዓዊ መረጃዎችን ያጣምማል ፤ ዝንባሌውን መሰረት አድርጎ ብይንን ያጸድቃል። እርሱም የሸሪዓን ጉዳይ መገልበጥ ፣ መረጃን ከማስቀመጥ አኳያ የሻሪዑን (የደንጋጊውን) አላማ ማበላሸት ነው።

**አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡**

﴿وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّنِ اتَّبَعَ هَوَاهُ بِغَيْرِ هُدًى مِّنَ اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ﴾

**"ከአላህም የሆነ መመሪያ ሳይኖረው ዝንባሌውን ከተከተለ ሰው ይበልጥ የጠመመ አንድም የለም። አላህ በደለኞች ህዝቦችን አይመራምና።"** *(አል'ቀሶስ፡ 50)*

ጥመታቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ብዥታ የሚፈጥሩ መረጃዎችን አጥብቀው ይይዛሉ። የጨበጡት ነገር -ልክ ተቃራኒ አካል ማስረጃ አድርጎ የሚይዘው ደካማ እንደሆነው ሁሉ- ከድክመትና ከቀላልነቱ አኳያ ልክ እንደ ሸረሪት ቤት ማለት ነው።

*ማስረጃዎች ይሆናሉ የሚጋጩ ልክ እንደብርጭቆ*

*ሀቅ ናት ብለህ ትጠረጥራለህ ሁሉም ሰባሪ እንዲሁም ተሰባሪ ሆኖ*

1. በረሡል ﷺ ላይ የተዋሹ እና የተፈጠሩ ሸሪዓን የሚጋጩ ማስረጃዎች ላይ መደገፍ እና በእርሱም ላይ ማስረጃ ማድረግ

2. የጥመት ዳዒዎች በአብዛኛው በተራውና በአላዋቂው ህዝብ ውስጥ ቢድዓን እና ተረት-ተረት ወሬዎችን ማሰራጨትን ዋና አላማቸው ማድረግ፡

በትክክለኛ የቡኻሪ ሐዲስ የሚከተለው የረሡል ﷺ ሐዲስ እንደመጣው ፡

**“በጀሀነም በሮች ላይ ተጣሪዎች (ይጣራሉ) ፤ እሺ ብሎ ወደርሷ (አወንታዊ ምላሽ የሰጠ) በውስጧ ይጥሉታል ...**

ግልጽ የሆኑ መረጃዎችን አንገት መቆልመም ፣ ብዥታ የሚፈጥሩ ወደቢድዓ የሚቀሰቅሱ እንዲሁም ክብርና ገንዘብ የሚያገኙበትን ድብቅ ፍላጎታቸውን ሊያረኩበት የሚችሉባቸውን መረጃዎችን ልቦቻቸው መጠጣት።

1. በሸሪዓ ብይኖች ላይ በታሪኮች ፣ በተረት-ተረት ወሬዎች እና ሰይጣናዊ ህልሞች ላይ መደገፍ ፤

2. በተቃርኖዎች ላይ ቸልተኝነት ማሳየት ፤ ከመልካም ማዘዝ እና ከመጥፎ መከልከል አንዳንድ ኡለሞች ዝም ማለት እና ማፈግፈግ። ምክንያቱ ማህበረሰቡ መጥፎ ነገር እየተሰራ አሊም ዝም ካለ መጥፎውን በሸሪዓ እደተፈቀደ አድርገው ይገምታሉ ፤ አይቃወሙትም። የሱና ዓሊሞች ዝም ባሉ ቁጥር የቢድዓ ተጣሪዎች አንገታቸውን ቀና ያደርጋሉ። ለዚህ ነው የዑለማ ቁጥር ባነሰባቸው አገሮች ቢድዓዎች የሚበራከቱ።

3. ቢድዓ ጭፍን በሆነ ተከታይነት መቅረቱ ፣ በጣም አስቸጋሪ ወደሆነ ባህል መቀየሩ ፤

4. በአቅል ላይ ድንበር መተላለፍ ፤ የማይገባውን ደረጃ መስጠት ፤ እርሱን ሸሪዓ ደንጋጊ መደረጉ እና ከሸሪዓው ይልቅ እርሱን ማስቀደም ፤

1. በተበላሸ ትርጉም ቁርኣን እና ሱና መፈሰር። በመጥፎ ግንዛቤ ወይም በመጥፎ አላማ ሊሆን ይችላል። የደጋጎችን ቀደምቶችን የቁርኣን ትንታኔ መተው ፣ ተቃርኖዎች ላይ ለመውደቅ አንዱ ምክንያት ነው።

2. በደጋግ ሰዎች ላይ ድንበር ማለፍ። በዓቂዳ ተቃርኖ ላይ ለመውደቅ ትልቁ ሰበብ እርሱ ነው። የደጋግ መቃብሮችን ሕያው በማድረግ ልቅና ሰጧቸው። ከዚያም ድንበር አለፉባቸው። ድንበር ማለፍና አደጋው የተከለከለ መሆኑ በቁርኣን እና በሱና በግልጽ መጧል።

3. አላህ በሚከተለው ቁርኣን እንደተናገረው አባቶች ፣ ሸይኾች እና አያቶች የነበሩበትን ማስረጃ በማድረግ ፣ መረጃን በመተውና ሀቅን አሽቀንጥሮ በመጣል ለአስተያየት እና ለግለሰቦች ወገንተኛ መሆን።

﴿وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ اتَّبِعُوا مَا أَنزَلَ اللّهُ قَالُواْ بَلْ نَتَّبِعُ مَا أَلْفَيْنَا عَلَيْهِ آبَاءنَا﴾

**"ለእነርሱም "አላህ ያወረደውን ተከተሉ" በተባሉ ጊዜ "አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን" ይላሉ።"** *(አል'በቀራህ፡ 170)*

1. ረሡል ﷺ በሚከተለው ሐዲሳቸው እንደተናገሩት በከሀዲዎች መመሳሰል እና በአብዛኛው ጉዳያቸው በእነርሱ ተጎታች መሆን።

"ከእናንተ በፊት የነበሩትን (ሰዎች) መንገድ ስንዝር በስንዝር ፣ ክንድ በክንድ በእርግጥ ትከተላላችሁ። የአርጃኖ ጉድጓድ ቢገቡ እንኳ ትገባላችሁ።" በማለት ረሡል ተናገሩ። *"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አይሁድና ነሷራ ናቸው?"* በማለት ጠየቅናቸው። "እንግዲያ እነማን ናቸው?!" *(ቡኻሪ፡ 3456)*

እነዚህ በዓቂዳ እና ጥመቶች አብዛኛው ሰው ተቃርኖ ላይ የሚወድቅባቸው ጉልህ ምክንያቶች ናቸው። ከእነዚህ መካከል ቁንጮው **ቅርሶችን ህያው ማድረግ** ነው።

ትኩረት ከሚደረግባቸው ነገሮች አንዱ፡ ማንኛውንም መጣመም እና መቃረን ለመቋቋም መግቢያ በር አይኖረውም በእውቀት እና በዑለማ እንጅ። ዒልም እና ዓሊሞች ከጠፉ ቢድዓ እና ሽርኮች ይፋ መሆን እና ለጥመት እና ባለቤቶቹ መሰራጨት በር ይከፍታል።

**ማጠቃለያ**

ቅርሶችን ሕያው በማድረግ ሚመጡ ዓቂዳዊ ተቃርኖዎች ጉልህ ከሆኑት ሰበቦች አንዱ ማህይምነት ነው። እርሱም የተቃርኖው ሁሉ መሰረት እና ዋና ነው። ሌሎች የእርሱ ቅርንጫፎች ናቸው። ሌላው ዝንባሌን መከተል ፣ በራስ አስተያየት መደገፍ እና ለባለቤቶቹ ወገንተኛ መሆን ነው። የተቀጠፉ ወሬዎችን ፣ ታሪኮችን ፣ የተፈጠሩ ቂሷዎችን ማሰራጨት። ከእርሷ አብዛኛው የጥመት ዳዒዎች የራሳቸው አድርገው መያዛቸው። በሷሊሆች እንዲሁም በዓቅል ላይ ድንበር ማለፍ። ለግል አስተያየት እንዲሁም ለግለሰቦች ቡድንተኛ መሆን። በካፊሮች መመሳሰል ፣ በእነርሱ መጎተት ፤ ቢድዓ እና ተረት ተረቶች እስከሚሰራጩ ድረስ ከመልካም ማዘዝ እና ከመጥፎ መከልከል ወደኋላ ማፈግፈግ።

**ቅርሶችን ህያው በማድረግ ላይ የሚከተሉ ጉዳቶች**

ጥበበኛ ከሆነው ህግን ደንጋጊ ክልክልን የሚጠይቅ ጥበብ ከሌለ በዘፈቀደ አንድ ነገር አይከለክልም። የጃሂልያ የጣዖት ቅርሶችን በተለይም የመቃብሮችን ቅርሶች ህያው ማድረግ ፣ መስጅዶችን ፣ መሻሂዶችን ፣ ቁባዎችን መገንባትን ፣ በእርሷ ላይ መጋረጃዎችን ከፍ ማድረግ ፣ መብራት ማብራት ፣ ለእርሷ አገልጋዮችን ማድረግን ፣ ስለቶችን ለመቀበል ሳጥኖችን ማዘጋጀት ፣ በዙሪያው ለመዞር ማመቻቸትን ፣ (በእርሷ ዙሪያ) ለአምልኮ መሰባሰብን ፣ ከእርሷ ዘንድ ወደርሷ መስገድ እና ሸሪዓው የከለከላቸው ሌሎችም አደጋዎችን ስናስተውል በውስጣቸው አደገኛ ፍጻሜዎችን ፣ አክሳሪ ተጽእኖዎችን ፣ ቆጥረን የማንዘልቃቸውን ጉዳቶች እናገኛለን።

ይህ ሸሪዓው በከለከለው ሁሉ የተስፋፋ ጉዳይ ነው። ይህ ከተረጋገጠ ዓቂዳን በሚመለከት ሸሪዓዊ ተቃርኖዎች ጋር ከተያያዘ አደጋው ከባድ መሆኑን አወቅን። ከቅርሶች ዘንድ የሚከሰቱ ተቃርኖዎች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። አሁን እየተነጋገርንበት ያለው አጀንዳ እርሷን ህያው በማድረግ የሚከተሉ አደጋዎችን ነው።

**በአጠቃላይ ቅርሶችን ህያው ማድረግ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች**

1. ጣዖቶች ፣ ሀውልቶች የወል በሆኑ ቦታዎች ይፋ መሆናቸው ወደትልቅ ወንጀል እና ከበደሎች ትልቅ ወደሆነው በደል ወደሽርክ ያደርሳል።

   የሽርክ ምስሎችና አይነቶቹ በርካታ ናቸው። አብዛኛው ሰው አይገነዘበውም። ትክክለኛም ይሁን ትክክለኛ ያልሆኑ ቅርሶች ዘንድ የሚቆም ሰው ጃሂል የሆኑ ሰዎች በአፈሯ ሲተሻሹ ፣ በውስጧ በሚገኙ ዛፎች ወይም ዱንጋዮች ፣ ከእርሷ ዘንድ ሲሰግዱ ፣ ወደአላህ ያቃርባል ፣ ከአላህ ዘንድ ሸፈዓም ይሆናል ፣ ጭንቀትም ይገላግላል ብለው በመጠርጠር ወደርሱ የተጠጋውን ሲማጸኑ ይመለከታል። ነፍሶች ደካማ ናቸው። ይጠቅመኛል ብለው ከጠረጠሩት ነገር ጋር በመተሳሰር ላይ የተፈጠሩ ናቸው።

2. ወላእ (ለአላህ ብሎ መውደድ) እና በራእ (ለአላህ ብሎ መጥላት) ከሙስሊሞች ዘንድ

ይናጋል። ይህ የሚከሰተው የጃሂልያ ጣዖታትን -ፈርዖናውያን ፣ ባቢሎናዊያን እና ፊይኒቅያውያንን ስልጣን ለማላቅ በሚደረገው ጥረት እና እነርሱን ከኢስላም ቅድሚያ በሚሰጡበት መካከል ነው። የሙስሊሞች ልቦች -በእነርሱ አባባል- ለጃሂልያ ታሪክ ልቅና በምትሰጥበት መጠን ለእስልምና ልቅና አይሰጡም።

3. ሱናዎችን መግደል ፣ ቢድዓን ህያው ማድረግ።

4. ከእርሱ ዘንድ ትክክለኛ አስተምህሮ እና ቀጥ ያለ መንሐጅ የሌለው አካል የኢስላምን ሐይማኖት በመጥፎ ማጠልሸት።

5. በሙስሊሙ መካከል ጎጠኝነት እና ዘረኝነት መስፋፋት። ግልጽ ከሆነው የኢስላም ቀጥተኛነትና ስነምግባር ዘረኝነት እንዲሁም በሙስሊሞች መካከል መለያየት አለመገኘቱ ነው። ቅርሶችን ህያው ማድረግ ይህን ቀጥተኛነት ያናጋል ፣ ከስሩ ነቃቅሎም ይጥለዋል።

6. ከቅጥፈት ዓይነቶች ላይ መውደቅ

አንደኛው አይነት ፡ በረሡል ﷺ ላይ መዋሸት ፡ ይህ ዓይነቱ ውሸት የተለያየ አይነት እንዳለው ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። በሚከተለው መልኩ በረሡል ﷺ ላይ የውሸት አይነቶች ይቀርባሉ፡

- በተለያዩ ቅዱስ በሚሏቸው ቦታዎች የሚያደርጉትን ጉብኝት ሸሪዓዊ ለማስመሰል በረሡል ﷺ ንግግር ላይ መዋሸት። ከዚህ መካከል
  - የረሡልን ﷺ ቀብር መዘየር የሚያስገኘውን ደረጃ የሚጠቁሙ የተፈጠሩ ሐዲሶች ማቅረብ
  - ቁድስ ለሚገኝ ቋጥኝ ደረጃውን የሚጠቁሙ የተቀጠፉ ሐዲሶችን ማቅረብ
- ከረሡል ﷺ ላይ በተያያዙ እና በተለዩ የሰውነት አካላቸው አሻራ ጋር የተዋሹ ናቸው። የሚዳሰሱ እና የሚጨበጡ ቅርሶች ናቸው። ለምሳሌ ፡ ጸጉሮች ፣ ካፖርቶች እና ጥምጣሞች። እንዲሁም ለውዶ የታጠቡበት ውሃ ቅሪት ፣ በሰባት ዲንጋዮች ላይ ነብዩ ﷺ የረገጡባቸው የጫማዎቻቸው ፋናዎች ብለው የሚቀጥፏቸው እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

- ይህ ውሸት ለመሆኑ ግልጽ ማስረጃው በእነዚህ ቦታዎች የሚገኙት የጫማ አሻራዎች መጠናቸው የተለያዩ አንዱ ከአንዱ አለመመሳሰሉ ነው።

**ሁለተኛው የውሸት አይነት፡**

በሶሃባዎች ፣ በታብዕዮች እና ከእነርሱ በኋላ በእነርሱ ጎዳና ላይ የተጓዙ ደጋጎች ላይ የሚቀጠፈው ቅጥፈት ነው። ይህ ከሶስት አቅጣጫዎች ይታያል፡

1. በንግግር የተዋሸ ሊሆን ይችላል። የአንዳንድ ቦታዎችን ደረጃ በማውሳት ወደነርሱ የተጠጉ የውሸት ወሬዎች ቅጥፈቶች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።
2. በተግባር በእነርሱ ላይ የተዋሸ ሊሆን ይችላል። በአንዳንዶች ቀብር ላይ በተገኘ በረከት እና መልካም ነገሮች እንደምሳሌ ይጠቀሳል።
3. የቅርሱን ቦታ በመለየት የሚቀጠፈው ቅጥፈት፡ ይህ አይነቱ በቁጥር በርካታ ነው። በተለይም የአንዳንድ ነብያቶች ፣ የሶሃቦችን እና የሌሎችን ደጋግ የአላህ ባሮች የመቃብር ቦታዎችን ለይቶ በመናገር የሚደረገው ቅጥፈት ነው። እንደዚሁ ያለምንም ሸሪዓዊ ድጋፍ በረካ ይገኛል በሚል የሚጠቅሷቸው መስጅዶች ፣ መውሊዶች እና ሌሎችም ናቸው።

**ማጠቃለያ**

**ቅርሶችን ህያው በማድረግ በሚል ከሚከሰቱ ግልጽ ጥፋቶች መካከል፡** የሽርክ መገለጫዎች እንደገና ማቆጥቆጥ ፣ ከሙስሊሞች ዘንድ የወላእ እና በራእ መናጋት ፣ የኢስላማዊ ዲን ገጽታ መበላሸት ፤ ጎጠኝነት እና ዘረኝነት መሰራጨት ፤ በተለያየ ሁኔታ ውሸት መከሰት ፤ በሙስሊም አገሮች የሙስሊም ጠላቶች የበላይ መሆን ናቸው።

**የመቃብሮችና የመሻሂዶችን ቅርሶች ህያው ማድረግ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች**

1. እርሷን ከአላህ ዘንድ ከቦታዎች ሁሉ ተወዳጅ ከሆነው ማብለጥ። ለአንዳንድ ቅርሶች ልቅና ይሰጣቸዋል ፣ ይከበራሉ እንዲሁም ይፈራሉ። እንዲህ አይነቱ ልቅና ሙስሊሞችን ካላቸው ደረጃ ዝቅ እንዲሉ ፈተና ላይ ጥሏቸዋል። ይህ ደግሞ መስጅዶች ተንደው ፣ መሻሂዶች እንዲዋቡ አድርጓቸዋል።

   አንዳንድ ጎብኝዎች መሻሂዶችን (ቀብሮችን) መጎብኘትን የአላህን ቤት ሀረምን ከመጎብኘት ጋር ያመሳስሉታል። ይህ ብቻ አይደለም ሐጅ ከማድረግ መሻሂዶችን መጎብኘት ይበልጣል የሚሉም አሉ። “ዶሪህን መዘየር በይቱላሂል ሀራምን ሰባ ጊዜ ከመጎብኘት ይበልጣል” የሚሉ ድንበር አላፊ የሆኑ ሙብተዲዖችም አሉ።

2. ወደርሷ በመሰባሰብ የክብረ በዓል ቦታ አድርጎ መያዝ። እነርሱ በፈጠሯት የበዓል ወቅት ይመላለሱባታል።

3. ድርጊታቸው ሀራም ወይም የተጠላ መሆኑን የተቀበረው አካል ግልጽ ከማድረጉ ጋር ከቀብር ዘንድ በሚሰራው ስራ ባለቤቶቿን ማወክ፡ የሁለቱ ኢማሞች ቀብር ለዚህ ምሳሌ ይሆናል። አቡሀኒፋ ﷺ በባግዳድ ፣ ሻፍዕይ ﷺ ደግሞ በግብጽ።

4. መቃብር ላይ በሚሰሩት ስራ ከጣዖት አምላኪዎች ጋር ከሁለት ነገሮች አኳያ ይመሳሰላሉ፡

- **የሽርክ መዳረሻ አድርጎ መያዝ ፡** መስጊድ ፣ ቁባ እና የተለያዩ ነገሮችን በመገንባት ቀብሩን ውበት መስጠት። በወርቅ እና በብር መቀባት ፣ በመጋረጃዎች እና በእምነበረድ ማልበስ ፣ መብራት እና ሻማዎችን ማብራት እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። አገልጋዮችን ፣ ለስለት ሳጥኖችን ማዘጋጀት ፣ ዙሪያውን ለሚጎበኙ ሰዎች እና ለሌሎችም ነገሮችን ማመቻቸት።
- **ግልጽ የሆነ ሽርክ መተግበራቸው፡** በቀብር ዙሪያ መዞር ፣ ከእርሷ ዘንድ ለኢባዳ መሰባሰብ ፣ ለእርሷ መሳል ፤ መተሻሸት ፣ መሳም ፣ በእርሱ በረካ አገኛለሁ ማለት ፣ በእርሱ መማጸን ፣ ዱዓ ፣ ሶላት ፣ እና ሌሎችም ዒባዳዎችን ማድረግ።

5. በሙስሊሙ ዓለም መሻሂዶች መሰራጨታቸው፡ ይህ የኢስላም አካል ተደርጎ እስከሚቆጠር ድረስ በመሻሂዶች ዙሪያ ወደእውቀት ተጠጋን የሚሉ አካላት ቸልተኝነት በማሳየታቸው ምክንያት የተገኘ ውጤት ነው። ለምሳሌ፡ በሂንድ የሚገኘው የታጅ መሻሂድ በአለም ዙሪያ ታዋቂ የቱሪስት መኅብኛ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህ መሻሂድ ግዙፍ ቀብር እንጅ ሌላ አይደለም። በህይዎት ለተለየችው ሚስቱ ማስታወሻ ብሎ የቀድሞው መሪ እንደገነባው ተዘግቧል።

በአሁኑ ሰዓት በከተሞች ውስጥ ከባድ ፈተናዎች የሆኑት ደግሞ ግብጽ ከተማ የሚገኘው የአህመድ አልበደዊ ፣ ኢራቅ ውስጥ የሚገኙት የዓልይ ፣ የሁሰይን ፣ የዓብዱልቃድር ጀይላኒ መሻሂዶች ናቸው።

እነዚህ የቢድዓ መሻሂዶች እርዳታን እና ድጋፍን በመፈለግ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለሐጅ እና ለጉብኝት ይመላለሱባቸዋል።

ብዙ ጊዜ በህልም ወይም ይህ ታየኝ በሚል የአንድን ነብይ ወይም ወልይ ቀብር ቦታ ይወስናሉ። ይህን ምናባቸውን በመጽሐፍ መልክ ያዘጋጁታል። በጣውላ እንጨት ወይም በእንስሳት ሬሳ ላይ መሸሐድ ተብሎ ይገነባል። (የእርሱ ዝና) ተናጋሪው በማይታወቅ ወሬ አመላላሽ አማካኝነት መረጃው ከአንዱ ወደአንዱ እንዲሰራጭ ይደረጋል።

በዚህ መረጃ መሰረት ይህ ቦታ መስጊድ ተደርጎ ይያዛል። ከአላህ ውጭ የሚመለክ ጣዖት ይሆናል። በቅጥፈት ላይ የተገነባ ሽርክ ይሆናል።

አላህ በቁርኣን ውስጥ እውነት እና ኢኽላስን እንዳቀራኘው ፣ ሽርክ እና ቅጥፈትንም አቀራኝቶ ይናገራል።

﴿فَاجْتَنِبُوا الرِّجْسَ مِنَ الْأَوْثَانِ وَاجْتَنِبُوا قَوْلَ الزُّورِ۞حُنَفَاءَ لِلَّهِ غَيْرَ مُشْرِكِينَ بِهِ﴾

**"ከጣኦታትም ርክሰት ተጠንቀቁ ። ሐሰትንም ቃል ራቁ። ለአላህ ታዛዦች በእርሱ የማታጋሩ ሆናችሁ (ከሀሰት ራቁ)።** *(ሐጅ፡ 30-31)*

6. ወደርሷ ሰዎች ጉብኝት እንዲያደርጉ ከአላህ ውጭ የምትመለክ እንድትሆን ለማነሳሳት **“መናሲኩ ሀጅ አልመሻሂድ”** የሚል መጽሐፍ ተዘጋጅቶ ወደባለቤቱ እስከሚመለስ ድረስ ዕቃ ጭነው ወደርሷ ሐጅ ያደርጋሉ። አላማቸው ከበይቱሏሂ አልሀረም ቦታዎች ጋር ማመሳሰል ፣ አላህና ረሡልን ﷺመቃረን ፣ የኢስላምን ሐይማኖት መለያየት እና የጣዖት አምልኮ ወደኢስላም ለማስገባት እንደሆነ የሚደበቅ አይደለም።

7. ከመቃብር እና መሻሂድ ዘንድ አላማቸው እንዲሳካ -ዱዓቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ፣ ከጭንቀታቸው እንዲገላገሉ ፣ መልካም ነገሮች እንዲመጡላቸው ፣ መጥፎ ነገሮች ከእነርሱ ላይ እንዲወገድ በሚል ውሸትን መሰረት አድርገው ተረት-ተረት ወሬዎችን ያሰራጫሉ። ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው የሀራም ገንዘብ ለመሰብሰብ ለተራው ህብረተሰብ ከተፈጠሩ ጦሪቃዎች የጥመት ተጣሪዎች የውሸት አገልጋዮች በኩል የሚሰራጭ ነው።

ይህን ጉዳይ ግብጽ የሚገኝ አንድ የሱፍያ ጦሪቃ ሸይኽ አምኗል። በቅድሚያ እገዛ ያገኘው ከመንግስት ነው። ዓረብ በሆነችው የግብጽ ህዝባዊ መንግስት ደረጃ  በመስጅዶች ለስለት ከተዘጋጁ ሳጥኖች ከሚገኘው ገንዘብ አስር ፐርሰንት ያገኛል።  በዚህ ምክንያት ተወሱል እና ተበሩክን አላማ በማድረግ ሰዎችን በመውሊድ ያስታውሳሉ። ወደቀብሮች ፣ ወደመሻሂዶች እንዲጓዙ ያበረታታሉ።

ልክ እንደዚሁ በኢራቅ ከተማ የዓልይ መስጅድ አገልጋይ የሆነው ሰው ይህን ጉዳይ እንደሚከተለው ግልጽ አድርጓል፡ *“እኔ በአሁኑ ሰዓት በአገልጋይነት ስራ ተሰማርቻ ነው የምገኘው.... ዳጎስ ያለ ገንዘብ ከመንግስት ይከፈለኛል ይህም በቀጥታ ከአውቃፍ ሚኒስቴር ነው። ቤተሰቦቻችን በኢማም ዓልይ መስጊድ ከ170 አመት ጀምሮ በአገልጋይነት ተሹመው ይገኛሉ። ይህ ድርጊት የተፈጸመው በንጉሱ አማካኝነት በህጋዊነት መልኩ ነው። የሚጎበኙ ሰዎች የወርቅ ፣ የብር ፣ የደናኒር ቁራጮች በሆነች ዳስ ውስጥ እስከቅርብ ጊዜ የሚጥሉት በመስጊዱ ውስጥ መስጊዱን የሚንከባከቡ አገልጋዮች እያሉ ለአገልጋዩ ብቻ የሚሰጥ ነበር።*

ይህ ከመሆኑ ጋር አገልጋዩ በየወሩ ከመንግስት ደመወዝ ይከፈለዋል። አሁን ግን የመንግስት አስተዳደሩ በማህበራዊ ፍትህ አማካኝነት አንድ ሰው በየወሩ ወደ ሃምሳ ሽ ዲናር ብቻውን ማግኘት የለበትም በሚል ለበርካታ ሰዎች መከፋፈል እንዳለበት ውሳኔ አሳልፏል።"

8. ቻዩ ህያው የሆነው ባሪያ በሞተው እና ደካማ በሆነው ልቦናው መንጠልጠሉ። ይህ የተከሰተው የተቀበሩት አካላትን ብማጸን መከራዎች ከእኔ ላይ ይወገዳሉ ፣ በጠላት ላይ ይረዱኛል ፣ ከሰማይ ዝናብ ያወርድልኛል ፣ ጭንቀቶችን ከእኔ ላይ ያስወግዱልኛል ፣ ሀጃዎችን ይፈጽሙልኛል ፣ የተበደለን ይረዳሉ ፣ ፈሪ የሆነውን አካል ይጠብቃሉ እና የመሳሰሉ አገልጋዮች እና ዳዒዎቻቸው የሚያሰራጩትን ነገሮች ይፈጽማሉ ብሎ ስለሚያምን ነው።

ይህ ተረት - ተረት የሚያወሩ ሰዎችን አቋም ፣ የምናብ ወሬዎችን በመስማት ከተቀበሩ አካላት ጋር ልቡን በማስተሳሰር እነርሱን መለመን በእነርሱ መማጸን ቀብሮችን ህያው ማድረግ የሚያስከትለው ከባድ አደጋ ነው።

በልምድ ከቀብር ዘንድ ተፈላጊ ነገሮች ይገኛሉ ፣ ዱዓዎች አፋጣኝ ምላሽ ያገኛሉ የሚለው አባባል ውድቅ እንደሆነ ከዚህ በፊት ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያ ﵀ የሰጠውን በቂ ምላሽ (ከገጽ ፡ 111 - 112) ያለውን ተመልሶ ማንበብ ይቻላል።

እነዚህ እያንዳንዱ ሙስሊም ሊጠነቀቃቸው ፣ ሌሎችም ከእነርሱ ላይ እንዳይወድቁ ሊያስጠነቅቃቸው ፣ ወደርሱ የሚያደርሱ ነገሮችንም ሊርቃቸው የሚገቡ ቅርስን ህያው በማድረግ ከሚከሰቱ ጉዳቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

**ማጠቃለያ**

ለኢስላማዊ ማህበረሰብ አስፈላጊው ከአፈር ውስጥ የሚወጡ ቅርሶችና እነርሱን በአውደ - ትእይንት እና ኤግዚቪሽን እንዲታዩ ሳይሆን ፣ ህዝቡ ለሚስተካከልበት ፣ ስኬታማ ለሚሆንበት የነብዩን ﷺ ትክክለኛ ሐዲሶች ህያው ማድረግ ነው።




ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐደራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ሊንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq